# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

# የ2009 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሂሣብ

# ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

ሚያዚያ/2010

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የ2009 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ኦዲት

# የሥራ አመራር ሪፖርት

## መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት፣ የአስራ ሰባት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

## የሪፖርቱ አላማ

የዚህ ሪፖርት አላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት የባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መ/ቤቱን 18 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የመቀሌ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ ምዕራብ አዲስ አበባ፣ የሞያሌ፣ የድሬዳዋ፣ የኮምቦልቻ፣ የሀዋሳ፣ የባህር ዳር፣ የአዳማ፣ የጅማ፣ የሞጆ፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ የጅግጅጋ፣ የሚሌ እና ጋሊፊ ቅ/ጽ/ቤቶችንና የዋናው መ/ቤት) እንዲሁም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተጠቃለለ የ2009 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

<u>**ኦዲታችን የሚያካትተው፡-**</u>

- በዋናው መ/ቤት በተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተጠቃለለ የሂሣብ ሪፖርት ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

በዋናው መ/ቤት የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ በሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት ማድረግና በባለስልጣን መ/ቤቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## <u>የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች</u>

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤትና የ17 ቅ/ጽቤቶች እንዲሁም የ2009 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### I) <u>የገቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>

### 1) <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ</u>

### 1.1) <u>የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 9,737,113.73 መኖሩ ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/4 በተደነገገው መሰረት እቃዎች እስከ ኢትዮጲያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ በግብይት ዋጋ መካተት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃ እና ማስረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ በመመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4(ከ ሀ እስከ ሐ) በተደነገገው መሰረት እቃዎችን እስከ ኢትዮጲያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ 5 በመቶ፤ እቃዎችን እስከ ኢትዮጲያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የመጫኛ፣ የማራገፊያና የመንከባከቢያ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ 5 በመቶ፣ እቃዎችን እስከ ኢትዮጲያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የኢንሹራንስ ወጪ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ 2 በመቶ በመጨመር በቀረጥና ታክስ ዋጋ ላይ እንደሚካተት  በተጨማሪም በደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/492/08 በቀን 17 ህዳር 2008 ከጅቡቲ ወደብ እስከ መዳረሻ ደረቅ ወደብ ድረስ ለማድረስ በተላለፈው የወጪ ተመን ሰርኩላር መሰረት ወጪዎቹ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶቹ በዚህ አዋጅ መመሪያ መሰረት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን እያስተናገዱ መሆኑ

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዋጁና መመሪያው መሰረት ባለመሰራቱ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 9,737,113.73 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 1 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

የአሰራር ክፍተቱ መሰብሰብ ያለበትን የመንግስት ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ተገቢው ቁጥጥር የማይደረግለት ከሆነ መ/ቤቶቹ መመሪያን የተከተለ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት እንዳይኖራቸው ሊያደርገው ይችላል፡፡

**ማሻሻያ ሀሳብ**

ትክክለኛው የማስጫኛ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበው ቀረጥ ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከአስመጪዎች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት ያለባቸው ወጪዎች በትክክል የተካተቱ ስለመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶቹ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ**

***የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት***

C-6843/16 & C-4991/16 ግኝቱን ያልተቀበሉት ሲሆን C-4335/16 እና C-6341/16 ውሳኔ የወጣለት ሆኖ ክፍያው ያልተፈጸመ መሆኑን በደብዳቤ ቁጥር 8.0/46/15 በቀን 09/05/10 ቅ/ጽ/ቤቱ ለባለስልጣን መ/ቤት የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በላከው ደብዳቤ ላይ ምላሽ የሰጡትን ባለስልጣን መ/ቤቱ በቁጥር 1.0/186/10 በቀን 25/05/2010 በላከው ደብዳቤ መሰረት ምላሻቸውን ተመለክተናል፡፡

***የድሬዳዋ፣ የጅግጅጋና የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤቶች***

አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ የሚፈለግባቸውን ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰቡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የሞጆ ቅ/ቤት***

- C-6679/17 በተመለከተ ቀሪ ሂሳቡን ከአስመጪው የሚሰበስቡ መሆኑ፣
- C-20704/16 በተመለከተ የministry of education ሰነድ የሆነ እና የመንግስት ዕቃ በመመሪያ 111/08 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ እና ሐ)መሰረት ባቀረቡት የኢንቮይስ ዋጋ መሰረት የተስተናገደ ነው በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምለሽ ገልጸዋል፡፡

- የኢንሹራንስ ወጪ ማስረጃ ያላቀረቡትን 28 ዲክላራሲዮን በተመለከተ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ስለሰጡት የኢንሹራንስ አገልግሎት ሽፋን እስከየት ድረስ ስለመሆኑ ግልፅ ማብራሪያ በደብዳቤ ተጠይቀው በሚሰጡት መረጃ መሰረት እንዲታይ ተደርጎ ቀጣይ ውሳኔ እንሰጥበታለን በማለት በሰጡ ምላሽ ገልዋል፡፡

<u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

C-20704/16 በተመለከተ መመሪያው ፈጣን መስተንግዶ ከመስጠት አንፃር ባቀረቡት ኢንቮይስ ይስተናገዳሉ እንጂ ያቀረቡት ሰነድ በድህረ ዕቃ አወጣጥ እንደሚጣራ ስለሚያዝና የሚፈልግባቸውም ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ ስላለበት ምላሹን የማንቀበለው ይሆናል፡፡

<u>***የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

ግኝቱን አስመልክቶ ተሽከርካሪዎቹ በራሳቸው እየተነዱ የገቡ በመሆኑ የመጓጓዣ ዋጋ በDPV መካተቱ አግባብ ያልነበረና ሌሎች ወጪዎች (other cost) ከጎረቤት ሀገር ተገዝቶ የሚገቡ ዕቃዎች ላይ የግብይት ዋጋውን 5% ጨምሮ መውሰዱ አግባብ አይደለም በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

<u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

ተሽከርካሪዎቹ በራሳቸው እየተነዱ የመጡ ቢሆንም በቀረበው የዕቃው ፎብ (FOB) ዋጋ ላይ ትራንስፖርት፣ የኢንሹራንስ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ እና የመንከባከቢያ ወጪ ባለመካተቱ ከላይ በግኝቱ በተገለጸው መመሪያ መሰረት ከጎረቤት ሀገር ተገዝቶ በገቡት ዕቃዎች ላይ ለትራንስፖርት 5% ፣ለመጫኛና የማራገፊያ የመንከባከቢያ 5% እና የኢንሹራንስ 2% ተካቶ ሊሰላና ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

- ድክላሬሽን ቁጥር C-1271/2016 ብር 144,189.48 በተመለከተ ግኝቱ በስራ ሂደቱ ጭምር የተገኘ ስለሆነ የተሻሻለ ቦንድ ወይም ዋስትና እንዲያቀርቡ ከደንበኛው ጋር የተነጋገርን መሆኑ፣
- ድክላሬሽን ቁጥር C-1584/2016 ብር 23,240.88 እና C-1582/2016 ብር 46,756.58 በተመለከተ ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ በቀጣይ የምንሰበሰብ መሆኑን
- ዲ/ዩን ቁጥር C-1326/16፣ C-540/2017፣ C-1402/2016፣ C-283/2017፣ C-118/2017 ጠቅላላ ግኝት ብር 301,853.48 በተመለከተ ሰነዶቹ በመመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ

43/1 መሰረት የተስተናገዱ ሲሆን፣ በድህረ እቃ አወጣጥ ቡድን ታይቶ በቀጣይ ኦዲት ተደርጎ ውሳኔ የሚወጣ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት***

በግኝቱ የተያዘው ዲክላራሲዮን አስመጪው ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 43 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 121 እና 122 ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አምስት አመት ወደኋላ ኦዲት የማድረግ ስልጣን መሰረት ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተመራ ስለሆነ በሚገኘው ውጤት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ መሰረት ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ማስረጃ ይቀርባል የተባለ ቢሆንም ባለመቅረቡ በኦዲት ግኝቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

የባህር፣ የክሊራንስ እና የየብስ ትራንስፖርት በትክክል ለቀረጥና ታክስ ማስከፈያነት ባለመካተቱ ምክንያት ብር 835,631.82 ያልተሰበሰበ የቀረጥና ታክስ መኖሩን በተመለከተ መሰብሰብ ያለበት የሚሰበሰብ መሆኑን እና በቀጣይም በቀረጥና ታክስ መካተት ያለባቸው ወጪዎች መካተቱን ክትትል የሚደረግ መሆኑን ተቀብለናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 1.2) <u>በግብይት ዋጋ(FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ(marine insurane) ወጪ ባለመደመሩ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,586,237.87 መኖሩ፣</u>

**ግኝት**

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው (በኢንቮይሱ) የቀረበው የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ከስሪት ሀገር ሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ አንሶ ከተገኘ ዕቃው የተሰራበት ሀገር ሲገዛ ባለው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ መሰረት እንዲስተናገድ የሚደረግ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከጎረቤት ሀገር ተገዝተው በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በዚህ

መመሪያ መሰረት የሚስተናገዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ለናሙና ከወሰድናቸው ዲክላራሲዮኖች መካከል ከጎረቤት ሀገር ግዢ ተፈጽሞ ወደ ሀገር ለገቡት ዕቃ የተያዘላቸው የግብይት ዋጋ የስሪት ሀገሩ ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ በመሆኑ የስሪት ሀገር ሲ.አይ.ኤፍ ላይ ለመድረስ የባህር ትራንስፖርት እና የመጫኛ/ማራገፊያ ወጪዎች ደረሰኝ ሊቀርብላቸው ባለመቻሉ በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 ሀ እና ለ መሰረት ለእያንዳንዳቸው የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ 5 በመቶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ በመጨመር የተስተናገዱ ሲሆን የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ ወጪ(marine insurance cost) ከስሪት ሀገር ወደብ እስከ ጅቡቲ ወደብ ድረስ ላለው ሽፋን የተከፈለው የኢንሹራንስ ሰነድ ያልቀረበ በመሆኑ በንዑስ አንቀጽ 4/ሐ መሰረት በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋን 2 በመቶ ታክሎበት ያልተሰራ ሲሆን በFOB ዋጋ ላይ የተደመረው የኢንሹራንስ ወጪ ከጅቡቲ እስከ መዳረሻ ደረቅ ወደብ ወይም ቅ/ጽ/ቤት ድረስ ለተገባው የኢንሹራንስ ሽፋን ብቻ በመሆኑና የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ ወጪው በFOB ዋጋ ላይ ተደምሮ ያልተሰራ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,586,237.87

መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.15/5 ቀን 22/05/2010 ግኝት ቁጥር 1.1.1 ላይ ይገኛል)*

## ስጋት

ከጎረቤት ሀገር ግዢ ሲፈጸም ከFOB ዋጋው በተጨማሪ በሻጩ ለባህር ትራንስፖርት፣ ለመጫኛ/ማራገፊያና ለማሪን ኢንሹራንስ የተከፈለው ወጪ እንዲቀርብ ተደርጎ ወይም ሰነዱን ማቅረብ በማይቻለበት ጊዜ በመመሪያ 111/2008 አንቀጽ 14/4 መሰረት እየተሰላ ለቀረጥ ማስከፈያነት የማይወሰድ ከሆነ የመንግስት ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሃሳብ

ከጎረቤት ሀገር ግዢ ሲፈጸም የስሪት ሀገር ሲ.አይ.ኤፍ ከጎረቤት ሀገር ኤፍ.ኦ.ቢ. ጋር በማነጻጸር እኩል ወይም የጎረቤት ሀገር ኤፍ.ኦ.ቢ. የበለጠ መሆኑ እየተረጋገጠ መስተናገድ ይኖርበታል፡፡ የባህር ትራንስፖርት እና የመጫኛ/ማራገፊያ ወጪ ማስረጃ ገዢው ማቅረብ ካልቻለ በመመሪያ 111/2008 አንቀጽ 14/4/ሐ መሰረት የኢንሹራንስ ወጪው ተስልቶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ እንዲደመር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ያልተሰበሰበውም ቀረጥና ታክስ መቀጫና ወለድ ታክሎበት ቅ/ጽ/ቤቱ እንዲሰበሰበው ሊደረግ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ

***በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት***

*ግኝቱን የተቀበሉት መሆኑንና ያልተሰበሰበውንም ቀረጥና ታክስ የሚሰበስቡ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡*

### 1.3) እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,111,978.51 መኖሩ

### ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 102 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን በትክክለኛው የሀርሞናይዝረድ ሲስተም ቁጥር እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ እየመደቧቸው እንዲስተናገዱ የሚያደርጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,111,978.51 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 2 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### ስጋት

መንግስት ከገቢ ዕቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

### የማሻሻያ ሃሳብ

በአስመጪው የሚቀርቡ እቃዎች በትክክለኛው የሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲስተናገዱ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ያልተሰበሰበውም ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫውን በመጨመር ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ

### የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት

- ዲክላራሲዮን ቁጥር C-30045/2016 በተመለከተ በተደረገ ማጣራት ኢንቮይስ ተራ ቁጥር 1 /Radiator coolant/ በትክክለኛው ታሪፍ በ10% የተከፈለ ሲሆን ኢንቮይሱ ተራ ቁጥር 5 ና 6 Brake fluid/ ላይ መከፈል ያለበት ቀሪ ሂሳብ ብር 17,600.07 መሆኑን
- ቀሪዎቹ ዕቃዎች ደግሞ በ2701990 ላይ ተመድበው መስተናገድ የሚኖርባቸው መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

### የኦዲተሩ አስተያየት

ቀሪው ብር 342,708.71 ሌሎች በሚለው 27101990 መመደብ አለበት የተባለውን በተመለከተ National Performax Silver, National Brake Fluid የሚሉት የሞተርና መሰል ዘይቶች በ 27101940 ከተዘረዘሩት ውስጥ ከባድ ዘይቶች (Heavy Oils) በስሙ ያለ በመሆኑና አሳማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

### የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት

ከሚመለከታቸው ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚሰበሰብ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

### በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት

ከመውጫ ስብሰባ ውይይት ወቅት ከስብሰባ በኋላ ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### የኦዲተሩ አስተያየት

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃ ባለመቅረቡ በኦዲት ግኝቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት

- የሰዓት የተገኘው ልዩነት በእኛ እይታና ታሪፍ ላይ በተቀመጠው አገላለጽ መሰረት ትክክል አይደለም በ91012900 የሚመደበው ዉድ የሆኑ ብረቶች (preciouses metal) የሚል መሆኑ፣
- cassero enamail, umbrella, lip stick የሚለው የተገኘው ግኝት ትክክል በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

### የኦዲተሩ አስተያየት

ተ-ቁ1 ከከበሩ ሜታሎች ወይም በከበሩ ሜታሎች የተስሩ እጅ ሰዓቶች መመደብ ያለባቸዉ በ91012900 HS code መሆን ሲገባዉ በ91022900 ይመደባል ቢሉም ከብረት የተሰራ

ሰዓት የሚል በመሆኑ ብረቱ ከውድ ብረት የተሰራ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ባለመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

## 1.4) <u>የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ ብር 15,236,030.55 መኖሩ</u>

### <u>ግኝት</u>

የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2/መ መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የእያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ (ECVS) ውስጥ የሚገኙ የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ያለው ልዩነት በማነስ ከ10% በላይ ከሆነ የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ተቀባይነት እንደማይኖረው ተደንግጓል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን እያስተናገዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በአስመጪዎች በቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ እና በጉምሩክ ዳታ ቤዝ(ECVS) ውስጥ ያለው የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ልዩነታቸው ከ10% በላይ በመሆኑና በጉምሩክ ዳታ ቤዝ ውስጥ ባለው ዋጋ መሰረት እንዲስተናገዱ ባለመደረጉ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 15,236,030.55 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 3 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### <u>ስጋት</u>

በአስመጪዎች የሚቀርበው የግብይት ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ ከሚገኙ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የዕቃዎች አማካኝ ዋጋ ጋር ተነጻጽሮ በሚገኘው ውጤት መሰረት እንዲስተናገዱ የማይደረግ ከሆነ የሚሰበሰበው ቀረጥና ታክስ አነስተኛ ሊያደርገው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአስመጪዎች የሚቀርበው የግብይት ዋጋ የወቅቱ ትክክለኛ የዕቃዎች ዋጋ ስለመሆኑ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ ከሚገኙ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የዕቃዎች አማካኝ ዋጋ ጋር እየተነጻጸረ ሊስተናገድ ይገባል፡፡ ሳይሰበሰብ የቀረውም ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫውን በመጨመር እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## <u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>

***<u>የሞጆና የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች</u>***

በቀጣይ ተጣርቶ የቀሪ ሂሳብ ውሳኔ የሚወጣላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት***

በግኝት የተያዙት ዲክላራሲዮኖች የተስተናገዱት አስመጪዎች ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ በመሆናቸው በመመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 43 እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 121 እና 122 ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አምስት አመት ወደኋላ ኦዲት የማድረግ ስልጣን መሰረት ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተመራ ስለሆነ በሚገኘው ውጤት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**1.5) <u>ለቀረጥ ማስከፈያነት የሚያስፈልጉ አስፈላጊ መረጃዎች በዲክላራሲዮኑ ላይ ባለመሞላታቸው የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ብር 943,433.55 ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ</u>**

***<u>ግኝት</u>***

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ 5 አንቀጽ 25 ን.አ 2 ሰ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክላራሲዮን በመሙላት የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መግለጫና መረጃዎችን የተሽከርካሪ ስም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር/የሲሊንደር ጉልበት (cylinder capacity/cc) የመሳሰሉትን በመሙላት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ መመሪያ አንጻር በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በትክክል መረጃው በዲክላራሲዮኑ ላይ እየተሞላ ቀረጥና ታክሳቸው የሚሰላ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለቀረጥና ታክስ ማስከፈያነት ከሚያገለግሉ መረጃዎች ዋና የሆነው የሞተር ጉልበት መጠን ወይም የመጫን አቅሙ (carrying capacity or cc) በዲክላራሲዮኑም ሆነ በዕቃ ዝርዝር መግለጫ(VDD) ላይ ያልተገለጸ በመሆኑ ***በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት*** በዲክላረሲዮኖቹ የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 943,433.55 ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.19/8 ቀን 21/05/2010 ግኝት ቁጥር 1.3 ላይ ይገኛል)*

**ስጋት**

ወደ ሀገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ሲስተናገዱ የተሽከርካሪውን ሙሉ መረጃ በኢንቮይስ ወይም በፍሬ ነገር መግለጫ ላይ እንዲሁም በዲክላራሲዮኑ ላይ በአግባቡ የማይገለጽ ከሆነ ትክክለኛ ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ተሽከርካሪዎች ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት በመመሪያው መሰረት ተሽከርካሪውን ሊገልጹ የሚችሉትን አስፈላጊ መረጃዎች በሚገባ በዲክላራሲዮኑ ላይ የተገለጸ መሆኑና ትክክለኛነታቸው በሚገባ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አሁንም በገቡት ዲክላራሲዮኖች ያልተገለጸው ተጣርቶ ያልተሰበሰበ ሂሳብ ካለ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

በመውጫ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በተደረሰው ስምምነት መሠረት በዲክላራሲዮኖቹ በተገለፁትና በቀረቡት ሰነዶች መሠረት በማድረግ ትራንዚት የሚፈቀድላቸዉ ተሸካርከሪዎቹ ወደ አገር ዉስጥ ከገቡ በኃላ ያቀረቡት ሰነድ ትክክለኛ ለቀረጥና ታክስ ማስከፈያ የሚረዱን መረጃዎችን በመሆናቸው ቀረጥና ታክስ ለመተመን በቂ ናቸው በማለት የገለጹ ሲሆን የቀረበውን ሀሳብ ከመመሪያው አኳያ የሚያዩ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ወደ ሀገር የገቡት ተሽከርካሪዎች በግኝቱ ላይ እንደገለጽነው ቀረጥና ታክሳቸው ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ያልተገለጹ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቹም ከእነዚህ ተሽከርካሪዎች የሰበሰቡት ቀረጥና ታክስ ያለእነዚህ ማስረጃ ትክክለኛ ነው ብሎ ለመቀበል የሚያስቸግር በመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቶቹ የውስጥ ኦዲት አስመጪው ሙሉ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ በማስደረግ ትክለኛነቱን አረጋግጦ ሊያሳውቀን ይገባል፡፡

## 1.6) አስመጪው ለትራንስፖርት ያወጣው ወጪ ተሰርዞ ዝቅተኛ ክፍያ እንደከፈለ ተደርጎ በመወሰዱ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 432,485.07 መኖሩ

**ግኝት**

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 በአንቀፅ 27(3)(ለ) መሰረት እቃው ከተላከበት አገር ወደብ እስኪደርስ ድረስ የወጣው ትክክለኛ የመጓጓዣ ወጪ

ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቱ ትክክለኛ የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ መኖሩን እያጣራና እያረጋገጠ የሚያስተናግድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

የትራንስፖርት (freight) ክፍያዎች ከዲክላራሲዮኑ ጋር የቀረቡ ቢሆንም በትክክል ያልተካተቱ እና በክፍያ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው (የተከፈለው) የትራንስፖርት ወጪ በእጅ ተሰርዞ ሌላ ያነሰ ዋጋ በመጻፍ እንደትራንስፖርት ወጪ በመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** በድምሩ ብር 432,485.07 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF.05.18/12 *ቀን 14/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.2 ላይ ይገኛል)*

**<u>ስጋት</u>**

በቀረጥ ማስከፈያነት ዋጋ ላይ መካተት ያለበት ወጪ በትክክል የማይካተት ከሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች ሊሰበስብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ቅ/ጽ/ቤቶች በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለባቸው ወጪዎች በአግባቡ የተካከቱ ስለመሆኑ ማጣራት እና ሰነዱ ከመበተኑ በፊት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከሚመለከታቸው አስመጪዎች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

የትራንስፖርት ወጪ ተሰርዞ በመሰራቱ ብር 432,485.07 በሚመለከት ከዚህ በፊት ባያያዝንላችሁ ደብዳቤ መሠረት አየር መንገድ ተጠይቆ የገለጸልን ደብዳቤ የራሱን መልካም ስም ለመጠበቅ ሲል በትክክል ያልገለጸልን ቢሆንም በአያታ አባል ድርጅቶች መካከል የዋጋ ውድድር እንዳይኖር ይህም መረጃው እንዳይወጣበት ለማድረግ ደብዳቤውን ለማስተካከል የተቸገረበት ቢሆንም በቀጣይ በቂና አሳማኝ ምክንያት እንዲያቀርብ ካልሆነም አስመጪዎቹን ለማስከፈል ይሰራል፡፡ ከኦዲት ግኝቱ በኋላ ስርዝ ድልዝ የሆነ በሙሉ መከፈል እንዳለባቸው ማስታወቂያ ወጥቶ በዚህ ብቻ እንዲሰራ አመራር ተሰጥቶበታል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 1.7) <u>በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የአየር ትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ የማይካተት ስለመሆኑ፤</u>

### <u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ አንቀፅ 96/1/ሀ/5 ዕቃዎች በአየር የተጓጓዙ በሚሆኑበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለውን አንድ ሶስተኛ(1/3) ወጪ መወሰድ እንዳለበት እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 111/08 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14(1)(መ) መሰረት ሌሎች ወጪዎች ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበ ከሆነ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተካተው ቀረጥና ታክሱ እንደሚሰላ ይደነግጋል፡፡ ***የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** በዚህ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ገቢ ዕቃዎችን እያስተናገደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለናሙና ባየናቸው ዲክላራሲዮኖች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡት ዕቃዎች የትራንስፖርት ወጪው በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የተካተተው ከሌሎች ወጪዎች ጋር በመደመር እና የሁለቱንም ድምር አንድ ሶስተኛውን በመውሰድ ሲሆን ነገር ግን በአዋጁ መሰረት የትራንስፖርት ወጪን ብቻ አንድ ሶስተኛ ወስዶ በቀርጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መደመርና እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን ለብቻው ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተደምሮ እንዲሰራ ያልተደረገ ሲሆን ይህንን የአሰራር ክፍተት አስመልክቶ በ2007 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየታችን ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም ቅ/ጽ/ቤቱ ለአሰራር ክፍተቱ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ የቆየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ሪፖርት ደብዳቤ ቁጥር OFAGF.05.18/12 ቀን 14/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.3 ላይ ይገኛል)*

### <u>ስጋት</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ የአየር ትራንስፖርት ወጪ ብቻውን አዋጁ በሚያዘው መሰረት በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የማይካተት ከሆነ ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመውሰድ በኃላፊነት ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የአየር ትራንስፖርት ስሌትን በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ እንዴት መካተት እንዳለበት በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቱ በአብዛኛው በአየር ተጓጉዘው የመጡ እቃዎች አዋጁ ከሚያዘው ውጪ

እየተስተናገዱ መሆኑ አግባብ ባለመሆኑ አሰራሩ እንዲያስተካክል አሁንም በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት ዋጋ የተካተተ ባለመሆኑ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በሚመለከት ቀረጥና ታክሱ እንዲከፈል በማስታወቂያ ተጠይቀው ለማስከፈል እየተሰራ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**1.8) <u>ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎቹ ያገለገሉ ስለመሆናቸው ማስረጃ ባለመኖሩ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,792,857.1 መኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

በመመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ 3 አንቀፅ 19 (1) ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የእርጅና ቅናሽ የሚደረገዉ ተሽከርካሪዉ የምርት ዘመንና አገልግሎት የሰጠ መሆኑን ከሚያስረዱ መረጃዎች በመነሳት እስከ 3ኛ አመት መጨረሻ ድረስ ከፎብ ዋጋ ላይ በየአመቱ የሚደረግ 10% ተቀናሽ ሲሆን ከ30% እንደማይበልጥ ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርከርካሪዎች እና ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎት ወይም ጥቅም ላይ ሳይውሉ ከአንድ አመት በላይ የቆዩ ቢሆኑም የእርጅና ቅናሽ ሳይደረግባቸው አዲስ በነበሩበት ጊዜ ባለው ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል ብሎ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎች ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ ያገለገሉ/used በማለት እንዲስተናገዱ በመደረጉ እና ያለአግባብ የእረጅና ቅናሽ ከዋጋው ላይ እንዲቀነስ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** በድምሩ ብር 2,792,857.10 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF.05.18/12 *ቀን 14/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.4 ላይ ይገኛል)*

**<u>ስጋት</u>**

የእርጅና ቅናሽ ስሌቱ በመመሪያው መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

በቅ/ጽ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች በሚያስተናግዱበት ወቅት ያገለገሉ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብ የእርጅና ቅናሽ እናዳይደርግ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ያልተሰበሰበውም የቀረጥ እና ታክስ መጠን መቀጫና ወለድን ጨምሮ ከሚመለከታቸው አስመጪዎች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የእርጅና ቅናሽ ስሌቱ በመመሪያው መሰረት መሆን አለበት፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

አሳማኝ የማይመስሉ ጉዳዮችን በቀጣይ አጣርተን ቀሪ ሂሳብ እንዲሰበሰብ እናደርጋለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### 1.9) ለኦዲት ሊቀርቡ ባልቻሉ ዲ/ሲዮኖች የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ብር 245,631.91 ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለአለመቻሉ

**ግኝት**

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 17/1/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለመ/ቤቱ ኦዲተሮች ለምርመራ ጠቃሚና አሰፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻህፍት መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶች እና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎችን ሁሉ ሲጠየቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ መልኩ ወዲያውን ማቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ለኦዲት ምርመራ እንዲቀርቡ ከተጠየቁ ዲክላራሲዮኖች ውስጥ ***በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት*** 2 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰበሰበው ብር 245,631.97 ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF.05.8/4 ቀን 24/02/2010 ግኝት ቁጥር 1.5 ላይ ይገኛል)*

**ስጋት**

መንግስት ከቀረጥ ሊሰበስብ ያሰበውን ግብር ማስረጃው ቀርቦ ባለመረጋገጡ ቀረጡ በትክክል ተሰብስቦ ይሁን አይሁን ለማወቅ አያስችልም፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ለኦዲት ያልቀረቡ ፋይሎች በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ተደራጅተው መቀመጥ ያለበት ሲሆን፡፡ ያልቀረቡት ሰነዶችም በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ተደርገው በውስጥ ኦዲት ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ውጤቱ ሊገለጽልን ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

ለኦዲት ያልቀረቡት ተፈልገው በድህረ ዕቃ ኦዲተሮች ኦዲት በማስደረግ ሪፖርት እናደርጋለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 1.10) **በዋጋ ስሌት ልዩነት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 29,016.88 መኖሩ**

**ግኝት**

የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 ክፍል ሁለት አንቀፅ 5/ 2ሀ በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ ከሚችሉ ምክንያቶች አንዱ ብዛት/መጠን መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በገባው ዕቃ ብዛት/መጠን ልክና በግብይት ዋጋ መሰረት ለዕቃው በትክክል ቀረጥ እና ታክስ መሰላቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች በትክክለኛ ብዛትን እና መጠን ቀረጥና ታክሳቸው የተሰላ ባለመሆኑ ያልተሰበሰበ ገቢ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,016.88 መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 4 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

በዲክላራሲዮን ላይ የሚታሰበው ቀረጥና ታክስ በአካላዊ ፍተሻ እና በሰነድ ምርመራ ውጤት መሰረት ተገቢው ማስተካከያ የማይደረግ ከሆነ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

የሚመለከተው የስራ ክፍል በሰነድ ምርመራ ውጤት መሰረት መደረግ ያለበትን ማስተካከያ መፈጸሙን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫውን በመጨመር ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

**የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት**

በዋጋ ስሌት ልዩነት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,146.80 በቀሪ ሂሳብ ለአስመጪው በማሳወቅ ይሰበሰባል፡፡ በቀጣይ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር ክትትል ይደረጋል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

**የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የፍተሻው ልዩነት የተፈጠረበት ምክንያት በቴክኒክ ክፍተት መሆኑን፣ በሰዓቱ አሰሰሩ ክሮስ ቼክ ማድረግ ነበረበት በዚህ መሰረት የተፈጠረ ክፍተት ነው፡፡ ግኝቱም አስተማሪ እና ለቀጣይ ስራችን እንደግብአት በመውሰድ ሥራችንን ለመስራት እንድንችል አቅጣጫ የሰጠበት ነው በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 1.11) <u>**በመንገደኛ ጓዝ ዲክሌር ተደርገው ብር 392,972.73 ቀረጥና ታክስ ተወስኖባቸው ክፍያ ያልተፈጸመባቸውና ዕቃዎቹም በጉምሩክ መጋዘን የማይገኙ ንብረቶችን በተመለከተ**</u>

<u>**ግኝት**</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15(1) ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 51(1) ላይ እንደተደነገገው ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነስርአት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት ***የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በአሲኩዳ ምዝገባ መሰረት በመንገደኞች በኩል የ2016 /2017 ሰነዶች የቆይታ ግዜያቸው ከሀምሌ 1/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 ከአንድ ወር እስከ አስራ ሁለት ወራት ያስቆጠሩ በ70 ዲክላራሲዮኖች የተገለጹ የደንበኛ ንብረቶች ያልወጡ/ያልተዘጉ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ንብረቶቹ ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ በሚሞከርበት ወቅት በውርስ መጋዘንም ሆነ በጉምሩክ መጋዘን የማይገኙ እና በወቅቱ መሰብሰብ የነበረበት ቀረጥና ታክስ (Assed but not paid) ብር 392,972.73 ያልተሰበሰበ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF.05.18/12 *ቀን 14/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.5 ላይ ይገኛል)*

<u>**ስጋት**</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ወደ ሀገር የገቡ እቃዎች ተመዝግበው ቀረጥና ታክስ የተከፈላባቸው ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ ገቢ ዕቃው ወጪ የሚደረግ ከሆነ በወቅቱ መሰብሰብ የነበረበት ቀረጥና ታክስ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለብልሹ አስራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ**</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ የሆኑ እቃዎች በአሰስመንት ውጤት መሰረት ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ አስመጪዎቹ እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

- ወደ 168,000.00 ብር አካባቢ ባንክ በሲፒኦ ተንጠልጥሎ የሚገኝ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚለቀቅ መሆኑ፣
- ደንበኞቹ ቀረጥና ታክሱን አሰርተውና በባንክ ክፍያ ፈጽመው የእቃ መውጫ ሳያሰሩ ሲፒኦ በማየት ብቻ እቃው እንዲለቀቅ የተደረገ በመሆኑ የተፈጠረ ችግር መሆኑ፣
- ከዚህ በተጨማሪ አንድ ዲ/ሲዮን በስህተት ሁለት ግዜ ታትሞ የተገኘ በመሆኑና የዕቃው ቀረጥና ታክስ ተወስኖ በዲፖዚት ማስረጃነት እንዲወጣ በመደረጉ የተፈጠረ ችግር ሲሆን በቀጣይ አጣርተን ምላሽ የምንሰጣችሁ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 1.12) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተወስኖባቸው ነገር ግን ቀረጥና ታክሱ ያልተከፈለባቸው (assessed but not paid) ዕቃዎች በድምሩ ብር 27,121,029.36 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 51(1) ላይ እንደተደነገገው ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነስርአት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በየቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ድክሌር ተደርገው ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ቀረጥና ታክሳቸው የተሰላ(assessed) ቢሆንም የቀረጥና ታክስ ክፍያ ሳይፈጸምበት ወይም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ ገቢ ዕቃ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 27,121,029.36 ቀረጥና ታክሱ ሳይሰበሰብ ወይም አስፈላጊው እርምጃ ሳይወሰድ የቆየ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 5 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ዕቃ ወደ ሀገር ሲገባ ቀረጥና ታክሱ ስለመከፈሉ ዕቃው ከመለቀቁ በፊት የማይጣራ ከሆነ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

የገቡት እቃዎች በህግ በተወሰነዉ ግዜ ውስጥ መክፈል ያለባቸውን ክፍያ እንዲፈጽሙ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተቀመጠው ግዜ ወስጥ የጉምረክ ሥነ-ስርዓቱን በማይፈጽሙት ላይ በአዋጅ በተቀመጠው መሰረት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***ቅ/ጽ/ቤቶቹ***

በአጠቃላይ አጣርተን እርምጃ የምንወስድ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### 1.13) <u>በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን ቀረጥና ታክሳቸው ያልተሰላላቸው (Registered but not assessed) ገቢ ዕቃዎች በድምሩ ብር 26,803,896.09 መኖሩ ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አስመጪዎቹ በየቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን ቀረጥና ታክሳቸው በገቢ ዕቃዎች ቡድን ሳይሰላላቸው /Assess ሳይደረግ የቆዩ ቢሆንም ዲክላራንቱ ያቀረበው የቀረጥና ታክስ መጠን በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 26,803,896.09 ትክክለኛ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ /Assess ያልተደረገ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ከአሲኩዳ የመረጃ ዘዴ ከወስድነው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 6 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

በቅ/ጽ/ቤቶቹ ቀረጥና ታክሳቸውን ለመክፈል የተመዘገቡት ገቢ ዕቃዎች በወቅቱ የቀረጥና ታክስ መጠናቸው በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተሰልቶ እንዲከፍሉ ወይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የማይደረግ ከሆነ ገቢው ሳይሰበሰብ ዕቃው ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ገቢ ዕቃዎቹ የጉምሩክ ስነሰርዓቱን በአዋጁ በተቀመጠው መሰረት ያልተፈጸመበት ሁኔታ ሊጣራና ተገቢው እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

**በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት**

የመንግስት መ/ቤት ማለትም የጤና ጥበቃ ሚ/ር የሚያስመጣው መድሀኒት በመሆኑ በደብዳቤ ዋስትና ተለቆ የሚከፈልበት ተከፍሎ ነጻ መሆን የሚገባውም ተረጋግጦ ውስኔ የሚሰጥበት ሲሆን ሌሎች 19 ሰነዶችም ተጣርቶ ያለአግባብ የተመዘገቡትን ዲ/ሲዮን ያለበቂ ምክንያት የመዘገቡ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ላይ እርምጃ ተወስዶ የሚሰረዝ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

ቀረጥና ታክሳቸው ያልተሰላላቸው ተብለው የተጠቀሱት ዲክላራሲዮኖች የታክስ ግምታቸው መሆኑን እና የተቀሩትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተደርገው እንዲሰረዙ በማድረግ በቅርብ ቀን የነዚህን ምላሽ የምናሳውቅ ይሆናል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 1.14) በትክክለኛ የታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ ያልተሰበሰበ ታክስ ብር 797,161.08 መኖሩ

**ግኝት**

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 1 ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ታክስ የሚጣልበት በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሚከፍለውን ቀረጥና ታክስ ጨምሮ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃዎች ዋጋ ስለመሆኑ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 133/1993 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የዕቃው ዋጋ የመድን አረቦን እንዲሁም የማስጫኛ ወጪ (ሲ.አይ.ኤፍ) እና ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ

ቀረጥ የተ.እ.ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ ድምር ይሆናል በሚለው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቅርጫፍ ጽ/ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡት እቃዎች በትክክለኛ የታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሱር ታክስ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 797,161.08 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 7 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ በእቅድ ይሰበሰባል የተባለውን ቀረጥና ታክስ ተግባራዊ እንዳይሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያልተሰበሰበውን ሂሳብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

**በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት**

በኢትዮ ሱዳን ስምምነት መሰረት የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው የሚገቡ እቃዎች ኤክሳይስ ታክስ የማይመለከታችውን ብቻ ለይቶ የasycuda++ ሲስተሙ ከቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ 1% የሚቀንስ በመሆኑና ይህም ተ.እ.ታ እና የሱር ታክስን ስሌት በማሳነስ የተከሰተ ሲሆን ችግሩን ለመፍታት እንዲቻልም ለዋናው መ/ቤትም ያሳወቅን ሲሆን፣ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ጥረት እንደደሚያደርጉ እና በአዋጁና በህግ መሰረት መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ ቅ/ጽ/ቤቱ የሚሰበስብ መሆኑን የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ እና የጉምሩክ ጉዳየች ም/ስራ አስኪያጅ በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

የጉምሩክ ስነ ስርዓት ስራ ሂደት በሰጡት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ መሰረት የሱዳን ስሪት በሚገቡ ዕቃዎች በአሲኩዳ ++ BoX 36 ET-SD በሚሞላበት ወቅት ከ DPV 1% ሲስተሙ በራሱ ግዜ ስለሚቀንሰው በ VAT, Sur taX እና WHT ላይ ልዩነት የሚያመጣ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ሁሉም ስራዎቻችን በአሲኩዳ የመረጃ ስርዓት መሰረት በመሆኑና በማንዋል የሚሰራ ስራ ባለመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት በአሲኩዳ አውቶሜሽን ስርዓቱ በመሆኑ ችግሩም ተቋማዊ መፍትሄ የሚሻ በመሆኑ በቁጥር ቀ65/ጉስ/አ-10/2513 በ23/05/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ለዋናው መ/ቤት ለችግሩ መፍትሄ

የሚሆን አቅጣጫ እንዲሰጥበት የተጠየቀበት በመሆኑ በቀጣይ በዋናው መ/ቤት በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 1.15) በድረህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ወይም በደንብ መተላለፍ ኦዲት ውሳኔ መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ተወስኖባቸው በጊዜ ገደቡ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 1,224,791,068.62 መኖሩ

### ግኝት

በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 (1 እና 2) መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለእዳ በ30 ቀናት ውስጥ እዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት ነገር ግን በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለእዳ ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚችል ይህንን በማይፈጽም ላይ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ያልተሰበሰበ የመንግስት ቀሪ ሂሳብ እና ግብር በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ተመላሽ ለማድረግ ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየቅ/ጽ/ቤቱ በ 2009 በጀት ዓመት የታየው የእዳ መጠን እና በባለፉት አመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ በዋና ኦዲተር መ/ቤት አስተያየት የተሰጠበት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ሳይሰበሰብ የቆየ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,224,791,068.62 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 8 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### ስጋት

ቅ/ጽ/ቤቶቹ  በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድንም ሆነ በደንብ መተላለፍ የስራ ሂደቶች የሚቀርቡለትን የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ውሳኔ እየተከታተለ እንዲሰበሰብ የሚያደርግ ካልሆነና በወቅቱ በማይከፍሉት ላይ ንብረታቸው ተይዞ የቀረጥና ታክስ ዕዳቸውን ለመሸፈን እንዲውል ለንብረት ያዥ ኮሚቴ በወቅቱ ደብዳቤ የማይጽፍ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### ማሻሻያ ሀሳብ

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ከአስመጪዎች ላይ በየስራ ሂደቱ የተወሰነባቸውን የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳቸውን እንዲሁም ሳይከፈል በዘገየበት ወለድ ጭምር መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ በውሳኔው መሰረት

ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ አስመጪዎች ላይ በመመሪያ መሰረት የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ዝርዝሩን ለንብረት ያኘ ኮሚቴ እንዲተላለፍ ማስደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

በዝርዝር በተገለጸው ግኝት መሰረት አብዛኛው የቀረጥና ታክስ ዕዳ እንዲሰበሰብ የተደረገ ሲሆን ቀሪዎቹን ዕዳዎች በቀጣይ ሚሰበስቡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት

በመውጫ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በተደረሰው ውይይት መሠረት አብዛኛዎቹ ባለዕዳዎች ከንግድ ስራ የወጡ እና የአካባቢው ሁኔታ ጋር ተያይዞ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ ሄደው እየሰሩ የሚገኙ በመሆናቸው እነዚህ አስመጪዎች ያለባቸውን እዳ ሳያጠናቅቁ በተለያዩ ጣቢያዎች እንዳይሰሩ ለማድረግ ሲስተሙ የሚይዝበት አሰራር ፕላን ተደርጎ የተገባበት አሰራር ስላለ ወደፊት ሲስተሙ ሊያግዘን ይችላል በማለት ሲያብራሩ፣ ነገር ግን አሁንም ያለባቸውን ዕዳ ተጠናክረን የምንሰበስብ ይሆናል፡፡ እንደተቋም ግን እንደ ክፍተት የምንወስደው ቢሆንም TPRDP (tax payer registration development program) ሊረዳን እንዳልቻለ መግለጽ እንወዳለን፡፡ በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ከኦዲት ስብሰባ መውጫ በሃላ ብር 4,344,949.81 ተከፍሏል በማለት ገቢው የተሰበሰበበት የገቢ ደረሰኝ ልከዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ እዳውን አስመልክቶ የተከፈለ ተብሎ የተላከው የገቢ ደረሰኝ በድምሩ ብር 4,344,949.81 እዳው የተገለጸበት የዲክላራሲዮን ቁጥር ያልተጠቀሰበት በመሆኑ ከተላከው ማስረጃዎች ውስጥ ብር 588,325.17 ብቻ የዲክላራላራሲዮን ቁጥሩ ተጠቅሶ የቀረበልን በመሆኑ ከጠቅላላ የሚሰበሰብ ቀሪ ዕዳ ላይ እንዲቀነስ የተደረገ ሲሆን ቀሪው የገቢ ደረሰኝ የዲክላራሲዮኖቹ ቁጥር ስላልተጠቀሰበትና የቀረበውም ሰነድ በኦዲት ግኝቱ መሰረት ለቀረቡት ዲክላራሲዮኖች ስለመሆኑ ማስረጃዎቹ በግልጽ የሚያሳዩ ባለመሆናቸው ሰነዶቹን አልተቀበልናቸውም፡፡

**በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት**

በአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በመታየት ላይ ያለ እና በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ላይ ያሉትን ክትትል እንደሚደረግና የህግ ውሳኔ የወጣባቸውን ድርጅቶች ንብረታቸውንም ሆነ በባንክ ያለ ገንዘባቸውን እንደሚታገዱ እንዲሁም አንዳንድ አስመጪዎች ደግሞ ድርጅታቸውን የዘጉ መሆናቸውን በመግለፅ ይህን በተመለከተ ለቀጣይ የሚኬድበት ሂደት መኖሩን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት**

በድህረ- እቃ አወጣጥ  ኦዲት ግኝት ተወስኖ ያልተሰበሰበ የቀረጥና ታክስ  መጠን ብር 113,565,532.52 በሚመለከት  በእዳ አሰባሰብ በኩል የተያዘው መረጃ እና በትክክለኛ ቀሪ ሂሳብ በሚል ከተያዘው የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን መካከል ልዩነት ያለው መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ የዚህ መረጃ ክፍተት የኦዲት ሪፖርቱ ወጪ ሲደረግና በአዋጁ መሰረት በ15 ቀናት  ውስጥ ቅሬታ አቅርበው የሚሰረዝላቸው እንዲሁም በጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ በኩል የሚወሰነውን ክትትል በማድረግ ባለመመዝገባቸው የተፈጠረ ክፍተት እንደሆነ ማየት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ብር 98,163,822.80 ሳይሰበሰብ የቀረ ውዝፍ ሂሳብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 60,954,773.67 ለወደብ አገልግሎት መከፈል ያለበት በሚል በኦዲት ተወስኖ ለብዙ አመታት በቅሬታ ሲንከባለል የቆየ በመሆኑ በ44ኛው የሚንስትሮች ስብሰባ ውሳኔ አግኝቶ በምህረት እንዲሰረዝ ውሳኔ ስለተላለፈ ከወደብ ክፍያ ጋር ብቻ የተገናኙ ወጪዎችን በማጣራት ለመሰረዝ እየተሰራ ነው፡፡ ውሳኔ ኮፒ አያይዘን ልከናል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

በሂደት የሚጣሩ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ከየካቲት ወር ጀምሮ መሰብሰብ ያለበትና ከዕዳ ወጪ መሆን ያለበትን በማጣራት ለመሰብሰብ ዕቅድ አውጥተን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በቀጣይ የቀረጥና ታክስ እዳው እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት**

- የተወሰኑ አስመጪዎች በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቱ በቅሬታ ላይ ያሉ መሆናቸው፣

- የተወሰኑ አስመጪዎች ደግሞ አሰፈላጊ መረጃዎችን በቀጣይ በመሰብሰብ እንዲከፍሉ የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት**

ለባንክ የእገድ ደብዳቤ የተጻፈባቸው፣ የቦንድ ዋስትና ያቀረቡ፣ ቅሬታ አቅርበው በመታየት ላይ ያሉ፣ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እየታየ ያሉ፣ በማስታወቂያ እንዲከፍሉ የተነገራቸው መኖሩ እንዲሁም በቀጣይ በሌሎቹም ላይ እንዲከፍሉ ተገቢውን እርምጃ የምንወስድ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በመውጫ ስብሰባ ላይ በተያዘ ቃለ-ጉባኤ መሰረት መመሪያ ቁጥር 94/2006 ከመውጣቱ በፊት የገቡ ዕቃዎች ላይ በሌሎች ወጪዎች ምክንያት የወጣ የቀሪ ቀረጥና ታክስ ውሳኔ ሲሆን በ04/05/2010 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዕዳቸው እንዲሰረዝ ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ውሳኔው የተነሳላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በተጣራው መሰረት ብር 2,470,472.64 ከመመሪያው በኋላ ወደ ሀገር የገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ ብር 2,035,993.22 ዲ.ዮን ቁጥራቸው በግልፅ የማይታወቅ በመሆናቸው የተሰጠው ምክንያት አግባብ ሆኖ ባለመገኘቱ በድምር ብር 4,506,465.86 በኦዲት ግኝቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

## 1.16) በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም በዋስትና የተያዘው ቀረጥና ታክስ ብር 235,177,463.32 ገቢ ያልተደረገ ወይም ዋስትናው ያልታደሰ መሆኑ

**ግኝት**

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 71 እና 73 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ወይም በቦንድ ያስያዘዉ ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ወይም ዋስትናው መታደስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከአዋጁ አንጻር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢዉ ቁጥጥር የሚደረግ

መሆኑንና በአዋጁ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑን ወይም ዋስትናው እንዲታደስ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,177,463.32 ዋስትናው ያልታደረሰ ወይም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ሲሆን በተጨማሪ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ2008 በጀት ዓመት ሰነድ ያልተገኘላቸው የዋስትና ሂሳቦች ብር 32,470,457.32 እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ተገቢ እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ታይቷል፡፡ (ግኝቶቹ በአባሪ 9 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)

**ስጋት**

በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የገቡ እቃዎችን ተገቢውን ክትትል በማድረግ የቆይታ ጊዜያቸው ካለፈባቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ያስያዙትን ዋስትና/ቦንድ ወደ ቀጥታ ገቢ በወቅቱ እንዲለወጥ ወይም ዋስትናው እንዲታደስ ካላደረገ በመንግስት ገቢ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

በጊዜያዊነት ለገቡት እቃዎች በህግ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ሌላ የማራዘሚያ ፈቃድ እስካላገኙ ድረስ በዋስትና/በቦንድ የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የቅ/ጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

**የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት**

ዋስትናውን ከሰጠው ኢንሹራንስ ድርጅት ጋር በመፃፃፍ እንዲሁም ክስ እንዲመሰረት ለአቃቢ ህግ በማስተላለፍ ዋስትናው እንዲከፈል፣ እንዲሰረዝና እንደአስፈላጊነቱ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት**

በጊዚያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ላይ የተያዘው የዋስትና ሂሳብን በሚመለከት ለብዙ ዓመታት ሲንከባለል የነበሩ ሆኖ አብዛኛው ለመንግስት ፕሮጀክቶች የገቡና ከአንዱ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ሲተላለፉ የነበሩ ሲሆን፣ ተከታትሎ ማሳደስና መረጃ የመያዝ ክፍተት የነበረባቸው መሆኑን እንዲሁም ቀላል የማይባል ደግሞ ግዴታቸውን ተወጥተው እያለ

በወቅቱ ቀረበው ዋስትናቸውን ቀሪ ባለማስደረጋቸው መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዝርዝር መረጃውን በማጣራት ላይ ስለሆነ በቀጣይ የምናሳውቅ መሆኑ ይታወቅ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**<u>የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያስተላለፍን ሲሆን ከዋናው መ/ቤትና ብሔራዊ ባንክ ጋር በመነጋገር ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንፈጥራለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**<u>የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ በኦዲት የተረጋገጠ እና መረጃዎች ተጣርተው ከሚመለከተው ድርጅት ወይም ግለሰብ በመሰብሰብ ወደ ገቢ የሚቀየር ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ኮንቴነሮቹ 3 ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሀገር የወጡና ሰነዳቸው ዘግይቶ የመጣ ቢሆንም ከሀገር የወጡ ለመሆኑ ኮፒ ሰነዶቹን ለኦዲተሮች ያቀረቡ መሆኑን ከስራ አመራር ምላሽ ጋር ኮንቴነሮቹ የወጡበትን 02 ገጽ ኮፒ አያይዘናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

የባህር ዳር አንድ (1) ድርጅትና የጎንደር ሶስት (3) ድርጅቶች ኮንቴነሮቹ ከሀገር ስለመውጣታቸው ቀረበ ከተባለው ማስረጃ ውስጥ ተካቶ ባለመቅረቡ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

## 1.17) <u>በቫውቸር ሥርዓት ከቀረጥ ነጻ ገብተው በጊዜ ገደቡ ምርት ላይ ያልዋሉና ምርቱም ለውጭ ገበያ ያልዋለ ጥሬ ዕቃ መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀፅ 10(3 እና 5) መሰረት በቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጪ ገበያ መላክ እንዳለበት ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጥሬ እቃውን ባህሪ መሰረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ነገር ግን የመጠቀሚያ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ

እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50% እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ባስገቧቸው ጥሬ እቃዎች ልክ በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ምርት ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ መሆኑን፣ ይህ ካልሆነ ግን ከቀረጥና ታክስ ነፃ አስገብተው ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ***በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** በኩል በተለያዩ አስመጪዎች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ጥሬ ዕቃዎች በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቢሆንም በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ በመሆኑ በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.12/7 *ቀን 27/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.9 ላይ ይገኛል)*

**<u>ስጋት</u>**

የቀረጥ ነጻ ማበረታቻው ቁጥጥርና ክትትል የማይደረግበት ከሆነ ከተፈለገው ዓለማ ውጪ ሊውል ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ቅ/ጽ/ቤቱ የቫውቸር ተጠቃሚ የሆኑት አስመጪዎች ጥቅም ላይ ባላዋሉት የጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በአዋጁና በመመሪያ መሰረት ክትትል በማድረግ ተገቢውን እርምጃ መወሰድና ማስከፈል አለበት፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

በስራ ላይ ያልዋለ ጥሬ ዕቃን በተመለከተ በአብዛኛው በተቀመጠው የግብአት ጥምርታ መሰረት የተወራረደ ቢሆንም የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ለኢንዲስትሪ ሚ/ር ባቀረቡት ቅሬታ መሰረት እንደገና እንዲታይላቸው የመጣ ሀሳብ ቢኖርም በኛ በኩል መክፈል እንዳለባቸው እናምናለን፡፡ ሆኖም ወጥ የሆነ አሰራር የሌለ በመሆኑ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የተቸገርን መሆኑ ይታወቅ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 1.18) <u>የቀረጥ ሂሳብ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የገቢና ወጪ የቁጥጥር ስርዓት የሌለው እና የማይመዛዘን ስለመሆኑ</u>

### ግኝት

በቅ/ፅ/ቤቱ በተግባር ላይ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎችና ዓይነቶች በአንቀጽ 6 እና 7 በተዘረዘሩት የቁጥጥር ደረጃዎች ዕይታ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቁጥጥር የሚካሄድበትና ማመዛዘኛ የሚሰራለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የቀረጥ ሂሳብ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ/REMOVAL/ ከዋና መ/ቤት ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቶት ወደ ቅ/ፅ/ቤቶች የሚላክ ቢሆንም ***በሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በመቀሌ ቅ/ጽጽቤት*** በሞዴል 19 እና 22 ገቢና ወጪ የማይሆን ከመሆኑም በተጨማሪ የተሰራበትንና ያልተሰራበትን ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ የተዘረጋ የቁጥጥር ስርዓት ባለመኖሩና የደረሰኝ ማመዛዘኛ ለመስራት ባለመቻሉ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.10/13 *ቀን* 22/05/10 *ግኝት ቁጥር* 1.8 *እና* OFAGF-05.13/10 *ቀን 28/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.6 ላይ ይገኛል)*

### ስጋት

የውስጥ ቁጥጥሩ ስርዓት የላላ የሚሆን ከሆነ በገቢ አሰባሰብ ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

### የማሻሻያ ሀሳብ

የስራ አመራሩ በየጊዜው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን በመፈተሽ የቅ/ጽ/ቤቱ ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በገቢ ደረሰኞች ላይም ተገቢው የገቢና ወጪ ቁጥጥር እየተደረገ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መመዛዘን ይኖርበታል፡፡

### የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ

### የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት

የቀረጥና ታክስ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ህትመት ተከናውኖ ከዋናው መ/ቤት ወደ ቅርንጫፍ ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቶት የሚላክ ቢሆንም የተሰራበትንና ያልተሰራበትን ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ የተዘረጋ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩና ማመዛዘኛ አልተሰራለትም ለተባለው በቀጣይ ማስተካከያ የሚሰራለት መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ የቀረጥ ሂሳብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ገቢና ወጪው በአንድ ጊዜ በ2007 ዓ.ም ተሰርቶ በካሸር እጅ የሚገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ማመዛዘኛ አልተሰራም ለተባለው ትክክል መሆኑን እና ወደ ካሸር የገባው ባለማለቁ ከዚያ ወዲህ ከዋና መ/ቤት ያልተላከ ሲሆን በሞዴል 19 እና 22 ገቢና ወጪ ስለመደረጉ ማስረጃ ከስብሰባ በኋላ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

***የኦዲተሩ አስተያየት***

በሞዴል 19 እና 22 ገቢና ወጪ የተደረገበት ማስረጃ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

## 2) ***የሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ***

## 2.1) ***በ2008 በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ያነሰ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 36,838,851.13 መኖሩ***

***ግኝት***

በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ግብር ከፋዮች የሚስታውቁት የሽያጭ ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና የተመረጡት ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2008 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ከ2008 በጀት ዓመት የ 12 ወራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ ጋር ሲነፃፀር በትርፍና ኪሳራ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ያነሰ በመሆኑና ለልዩነቱም አሳማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 36,838,851.13 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 10 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

***ስጋት***

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሚያሳውቁበት ሰዓት ገቢያቸውን በማሳወቂያ ቅጹ ላይ ሙሉ በሙሉ በትክክል እየሞሉና ልየነት ካለም ለልዩነቱ ማብራሪያ እንዲያቀርቡ እየተደረ5ገ የማያሳውቁ ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ግብር ከፋዮች ያመኑበትን ግብር ከፍለው ከሄዱ በኋላ የቀረበውን ማስረጃ ከከፈለው ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ ትክክለኛነቱን ካልተረጋገጠ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ስለሚችል ቅ/ጽ/ቤቶቹ አልተሰበሰበም የተባለውን ግብር ወለድና መቀጫን በመጨመር ሊሰበስቡ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት***

3 ግብርር ከፋዮች እንዲከፍሉ የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸው ሲሆን፣ ሌሎችን በቀጣይ አጣርተን ተገቢውን እርምጃ እንወስዳለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት***

በተገኘው ግኝት ላይ ወለድና ቅጣት በመጨመር በድርጆቶቹ ላይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸው መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

ፈንጡሌ ድርጅትና አባቢያና እስማኤል ድርጅትን በተመለከተ ግኝቱ ትክክል መሆኑን ያረጋገጥን በመሆኑ በቀጣይ ግብሩን እንዲከፍሉ የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸው ሲሆን በቀሪዎቹ ላይ ክትትል በማድረግ ቀጣይ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

የልዩነቱን ምክንያት በማጣራት ውሳኔ የሚያወጡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት***

- ባርነባ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በንግድ ትርፍ ታክስ ላይ ለታየው በልዩነቱ መሠረት ተወስኖ ድርጅቱ በንብረት ሽያጭ ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ንብረት በማፈላለግ ላይ የሚገኝ ድርጅት መሆኑ፣
- አጋር የጥበቃ ድርጅት ኃ/የተ/የግ/ማህ ያልተከፈለ ታክስ ሳይሆን በሽያጭ መመዝገብያ አጠቃቀም ወቅት በፈጠረው ስህተት የተፈጠረ ልዩነት በመሆኑ ተመላሽ እዲደረግለት በተፈቀደለት መሰረት የተስተካከለ ሽያጭ መሆኑ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## <u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

አጋር ጥበቃ በተመለከተ የቀረበው ማስረጃ ተመላሽ የተፈቀደበት ሳይሆን የተጠየቀበት እና በተጨማሪ በገኘው ጥያቄ ተመላሽ የሚደረግበት (Refund book) ሲሆን በማስረጃውም መሰረት ተቀባይነት ያገኘው 250,344.00 ተቀንሶ በመሆኑ በልዩነት ብር 126,934.38 ንግድ ትርፍ ያልተከፈለበት ስለሆነ የተሰጠው ምክንያት አግባብ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም።

***<u>የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በቀጣይ አጣርተው የውሳኔ ማስታወቂያ የሚያወጡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***<u>የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ውሳኔ እንዲወጣ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች ያሉ ሲሆን በቀጣይ በሌሎቹም ላይ አጣርተው ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 2.2) <u>**በ2008 በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ያነሰ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 65,303,657.63 መኖሩ**</u>

## <u>**ግኝት**</u>

በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ግብር ከፋዮች የሚስታውቁት የሽያጭ ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና የተመረጡት ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2008 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ከ2008 በጀት ዓመት የ 12 ወራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ ጋር ሲነፃፀር በትርፍና ኪሳራ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ የበለጠ በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ባለመቅረቡ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 65,303,657.63 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 11 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## <u>**ስጋት**</u>

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሚያሳውቁበት ሰዓት ገቢያቸውን በማሳወቂያ ቅጹ ላይ ሙሉ በሙሉ በትክክል እየሞሉ የማያሳውቁ ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግብር ከፋዮች ያመኑበትን ግብር ከፍለው ከሄዱ በኋላ የቀረበውን ማስረጃ ከከፈለው ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ ትክክለኛነቱን ካልተረጋገጠ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ስለሚችል ቅ/ጽ/ቤቶቹ አልተሰበሰበም የተባለውን ግብር ወለድና መቀጫን በመጨመር ሊሰበስቡ ይገባል፡፡

## <u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ ሥራ አመራር ምላሽ</u>

### *<u>የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት</u>*

- ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አ/ማህበር ለሁለቱ የታክስ ዓይነቶች የተለያየ የሂሳብ ማሳወቂያ ጊዜን የሚጠቀም በመሆኑ ምክንያት በተጨማሪነት ልዩነቱ የተፈጠረ መሆኑ፣
- ዋይ.ኤች.ኤፍ.ኤች ዓመታዊ ግብሩን ሲያስታውቅ በድምር ስህተት ምክንያት በተጨማሪነት በገቢ የያዘ በመሆኑ የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ እንደገና ሂሳቡን አስተካክሎ እንዲያቀርብ የተደረገ ሲሆን ኬ.ኤም.ኤስ ኮንስትራክሽንን በተመለከተ አጣርተው ውሳኔ የሚሰጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ዋይ.ኤች.ኤፍ.ኤች የተስተካከለበት ማስረጃ ቀርቧል ቢባልም ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

### *<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>*

አልታድ ኃ/የተ/የ/ግ/ማ፣ አዲስ ፋና ጠቅላላ ንግድ ድርጅት አ.ማ በታየው በልዩነቱ መሠረት የተገኘው ተዕታ ተወስኖ ውሳኔ ደርሷቸው የነበረ ሲሆን በውሳኔው ላይ ያላቸው ቅሬታ ለቅ/ጽ/ቤታችን ቅሬታ አጣሪ ማቅረባቸውን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *<u>የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት</u>*

የሚጣራው ተጣርቶ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውም የውሳኔ ደብዳቤ የሚወጣላቸው መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>*

በቀጣይ የተሰጠውን አስተያየት በመውሰድ የውሳኔ ማስታወቂያ እንዲያሚያወጡ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *<u>የምስራቅ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት</u>*

የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው ክፍያ ለመፈጸም የክፍያ ስምምነት የገቡ ግብር ከፋዮች መኖራቸውና ሌሎችን ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማስደረግ ተገቢው እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት***

በተገኘው ግኝት ላይ ወለድና ቅጣት በመጨመር በድርጅቱ ላይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የወጣለት መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የምዕራብ አ/አ/ቅ/ጽ/ቤት***

ውሳኔ እንዲወጣ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች ያሉ ሲሆን በቀጣይ በሌሎቹም ላይ አጣርተው ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 2.3) በ2008 የግብር ዘመን በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ካሳወቁት የብር 470,425.56 ልዩነት መኖሩ

### ግኝት

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ እና በ2008 በጀት ዓመት በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የ12 ወራቱ ጠቅላላ ሽያጭ እኩል መሆኑንና ካልሆነም ምክንያቱ መጣራቱን በዚህም መሰረት ግብርና ታክስ በትክክል መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተ.እ.ታ ማስታወቂያ ላይ ከሚታየው ጠቅላላ ሽያጭ በብር 470,425.56 የበለጠ በመሆኑ ከሽያጩ ሊሰበሰብ የሚገባ ተጨማሪ እሴት ታክስ ያለ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.6/6 *ቀን 13/03/2010 ግኝት ቁጥር ሀ/የሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ይገኛል)*

### ስጋት

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ካሳወቁ በኋላ ገቢያቸውን በማሳወቂያ ቅጹ ላይ ሙሉ በሙሉ በትክክል እየሞሉ ያሳውቁ መሆኑን ክትትል እና ቁጥጥር ካልተደረገ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**ማሻሻያ ሀሳብ**

የልዩነቱ ምክንያት ተጣርቶ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ካለ እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አመራር ምላሽ**

ሀዋስ አግሪ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ልዩነት ብር 470,425.56 ሲሆን ድርጅቱም ቤት የሚያከራይ በመሆኑ አስቀድሞ በተቀበለው የኪራያ ገቢ ምክንያት የተፈጠረ ልዩነት መሆኑን በደብዳቤና በሰነድ ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን የተሟላ መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ በቀጣይ ማጣራት በማድረግ የሚወሰን ግብር ካለ ተወስኖ የሚሰበሰብ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ኦዲት አስደራጊዎች እንደገለጹት የቤት ኪራይ ቅድሚያ ክፍያ የሰበሰበው ከሆነ መብለጥ ያለበት በተ.እ.ታ ሪፖርት ላይ የተገለጸው እንጂ የትርፍና ኪሳራው መግለጫ ባለመሆኑና የተሰጠው ምክንያት ትክክል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2.4) **ከ2007 የግብር ዘመን መዞር ያለበት የንግድ ክምችት እቃ/ending inventory ወደ 2008 የግብር ዘመን በሚዞርበት ጊዜ ከፍ እንዲል በመደረጉ ምክንያት ገቢ ያልሆነ ፍሬ ግብር ብር 304,546.8 መኖሩ**

**ግኝት**

አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ ስልት (GAAP) መሰረት ያለፈው ዓመት በመጋዘን የቀረ የሚሸጥ ዕቃ (ending inventory) ሚዛን ለቀጣይ ዓመት የመነሻ ሚዛን ሆኖ በዘመኑ ግዢ ላይ በመደመር በዘመኑ ለሽያጭ የሚቀርብ እቃ(goods available for sale) ሆኖ መያዝ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ግብር ከፋይ ድርጅቶች የሂሳብ መግለጫቸውን እያቀረቡ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ2007 የግብር ዘመን የሂሳብ መግለጫ ላይ በአመቱ መጨረሻ ሳይሸጥ የቀረ ዕቃ(ending inventory) በ2008 የግብር ዘመን ላይ እንደ መነሻ ሚዛን(begging inventory) አድርጎ በተመሳሳይ መጠን ማዞር ሲገባው ከፍ እንዲል በማድረጉ ሳይሰበሰብ የቀረ ንግድ ትርፍ ግብር በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 304,546.8 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 12 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

**ቅ/ጽ/ቤቶች ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን በሚያስታውቁበት ጊዜ በማስታወቂያው እና በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚገልጹትን የሂሳብ እንቅስቃሴ በጥንቃቄ እንዲታይ የማያስደርጉ ከሆነ በወቅቱ መሰብሰብ ያለበት ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡**

**<u>ማሻሻያ ሀሳብ</u>**

**ያልተሰበሰበው ፍሬ ግብር ወለድና መቀጫውን በመጨመር እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡**

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

**ለግብር ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ የተሰጠው ሲሆን በቀጣይ የሚሰበሰብ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡**

***<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

**ሙሉ በሙሉ የቀረበውን አስተያየት በመውሰድ በቀጣይ በሂደት የምንሰራ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡**

## 2.5) <u>ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸው አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ በመደረጋቸው ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 10,265,278.35 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

**በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1) ሀ እስከ ኘ በተገለጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ ያልተደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ከገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች እንዲቀነሱ የተደረገ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 10,265,278.35 መኖሩ ታውቋል፡፡** ***(ግኝቶቹ በአባሪ 13 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***

**<u>ስጋት</u>**

**ግብር ከፋዮች በአዋጁ መሰረት ከገቢ ላይ ሊቀነስ የማይገባቸውን ወጪዎች የሚቀነሱ ከሆነና ቅ/ጽ/ቤቶችም ተገቢውን ክትትል የማይደርጉ ከሆነ መንግስት ሊሰበስብ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡**

## የማሻሻያ ሃሳብ

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ወለድና መቀጫውን በመጨመር ከግብር ከፋዮቹ ሊሰበስቡ ይገባል፡፡ በቀጣይም ይህ አሰራር እንዳይደገም ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### የአዳማ እና የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

ለግብር ከፋዮቹ ውሳኔ የወጣላቸው ሲሆን በቀጣይ የሚሰበሰብ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የሀዋሳ፣ የጅማ፣ የኮምቦልቻ እና የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤቶች

የውሳኔ ማስታወቂያ በማውጣት በቀጣይ ተገቢውን እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

- እንዲከፍሉ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣ በደረሳቸው ውሳኔ መሰረት ቅሬታ ያቀረቡ ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣ ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ የተነገራቸው ግብር ከፋዮች መኖሩን እንዲሁም አምባሰል የንግድ ስራዎች እንደ ወጪ የተያዘው (Social responsibility) ብር 1,433,316.60 ዴክስ ኦዲት የተደረገበት እና በኦዲቱ ግኝት ውስጥም የተካተተ ሲሆን በተጨማሪ ኦዲቱን ያከናወነው ኦዲተር ቀርቦ መግለጫ ይሰጥበታል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡
- ያፒ መርከዚን ድርጅቱ ከተሰማራበት የስራ ዘርፈ ባህሪ ለስራ የሚያመጣቸው ማሽኖች መልሶ ወደ ውጭ በሚልክበት ጊዜ የሚፈጠር እና ፕሪ ፋብሪኬትድ ቤቶች የዲፕርሴሽን ወጪ አያያዝ (othermaterials (20%) በመሆኑ የተፈጠረ ልዩነት እንጂ ያልተከፈለ ታክስ አለመሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ ሲሆን የንብረቱ አይነት ተንቀሳቃይ በመሆኑ እና ከሌሎቹ ህንጻ ተብለው ከሚወሰዱ ንብረቶች በመለየቱ ምክንያት የአወሳሰዱን እና የአሰላሉን መግለጫ ጠይቀን ምላሽ በመጠበቅ ላይ ከመሆኑም በተጨማሪም ንብረቱ ለፕሮጀክት አገልግሎት ተብሎ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ስለሆነ ለፕሮጀክቱ አመቱ አካፍሎ የእርጅና ቅናሽ ማስላት እንደ አንድ አማራጭ በመወሰዱ መሆኑን እና ቅድሚያ የሒሳብ መግለጫው ታይቶ ማጣራት እንዲደረግበት ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ከስምምነት ተደርሷል፡፡

- ሱር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የ/ማ ድርጅቱ ያገለገሉ እቃዎች በሚያስወግድበት ጊዜ እና በዋስትና ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ የእቃዎቹ ዋጋ ካላቸው (book value) በታች በሚሸጥበት ጊዜ የሚፈጠር መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ የገለጹ ሲሆን ማስረጃውን ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ታይቶና ተረጋግጦ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ከስምምነት ተደርሷል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

- አምባሰል የንግድ ስራዎች ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ይቀርባል የተባለው ኦዲት መግለጫ ቀርቦ ሲረጋገጥ በኦዲት ግኝት ውስጥ ተካቷል የተባለው ባለመካተቱ እና የሰራው ኦዲተር ቀርቦ የተቀበለበትን ምክንያት እና ማስረጃ ባለማቅረቡ የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡
- ያፒ መርከዚን በተመለከተ ከስብሰባው በኋላ ይቀርባል የተባለው ስለ ተንቀሳቃይ ቤቶችን መረጃ ማለትም የሂሳብ መግለጫ ቀርቦ ማሳወቂያው ላይ በቅድሚያ ማሳወቃቸው ተረጋግጦ ከግኝት ብር 4,861,052.15 የወጣ ሲሆን ማሽነሪዎቹን በተመለከተ ብር 3,354,039.90 ምንም አይነት ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲሁም ሱር ኮንስትራክሽንን በተመለከተ ከስሰባው በኋላ ይቀርባል የተባለው ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምክንያት የማንቀበለው ይሆናል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ውይይት ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ማስረጃ ባለመቅረቡ በኦዲት ግኝቱ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***

- በላይ ተክሉ እና ልጆቹ ሀ/የተ/የግ/ማህበር በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000034716 የሚታወቀው ያልተሰበሰበ ከተባለው ግብር ብር 69,299.97 ውስጥ ብር 39,190.67 ውሳኔ የወጣለት ሲሆን፣ ለቀሪው ውሳኔ ሊወጣለት ይገባል በሚል መጠየቁ ይታወሳል፡፡ ሆኖም ግን እስከ ሰኔ ወር 2009 አጠቃላይ ኦዲት መሆኑን የሚያሳይ በደብዳቤ ቁጥር ታአ/164/2/10 በቀን ታህሳስ 04/2010 ዓ/ም የወጣ የውሳኔ መሰረት ሲሆን በድጋሚ

በአወሳሰን ቡድን ማስተካከያ ማድረግ አንችልም በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

- የእርጅና ቅናሽ ስሌት የተፈጠረ ስህተትን በተመለከተ ለአራቱም ግብር ከፋዮች የግብር ዕዳ ውሳኔ ማሳወቂያ የወጣ ሲሆን፣ ይሳኮር የግብርና ግብአቶች አስመጪ እና አከፋፋይ በቀጣይ ተጣርቶ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

በላይ ተክሉና ልጆቹ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በታክስ ኦዲት አልተሰበሰበም ተብሎ ውሳኔ ከወጣበት ውስጥ የኦዲተሩ ግኝት ሙሉ በሙሉ ያላካተተና ቀሪ የሚታይ ብር 30,109.30 በመኖሩ ለልዩነቱ ማስረጃ ሊቀርብ አልያም የግብር እዳ ውሳኔ ሊወጣ ይገባል፡፡የኦዲት ግኝቱ ትክክል እስከሆነ ድረስ  እርምጃ አንወስድም ማለት  አግባብ ባለመሆኑ ይህን በሚያደርጉ የሥራ ኃላፊዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## 2.6) ከገቢ ላይ ተቀናሽ የተደረገው ወጪ በድምሩ ብር 13,741,882.62 ተቀባይነት ያላቸው ወጪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ

**ግኝት**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1)ሀ-ኘ በተገጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ከገቢ ላይ አለመቀነሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወጪዎች በትክክል ከገቢ ላይ የሚቀናነሱ ስለመሆኑ አስፈላጊው መረጃ ሳይኖር ከገቢ ላይ እንዲቀናነስ የተደረገ ወጪ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 13,741,882.62 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 14 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

በግብር ከፋዮች የሚቀርቡ ወጪዎች ተቀባይነት ያላቸው ወጪዎች ስለመሆናቸው በአግባቡ የማይጣራ ከሆነ በሚሰበሰበው ገቢ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ግብር ከፋዮቹ ከገቢ ላይ እንዲቀነስ ያደረጉት ወጪ ትክክለኛ ስለመሆኑ በቀጣይ ተጣርቶና አስፈላጊው ማስተካከያ ተሰርቶ ውጤቱ በውስጥ ኦዲት ሊገለጽልን ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### *የጅማ ቅ/ጽ/ቤት*

ከገቢ ላይ ተቀናሽ የተደረገውን ወጪ በተመለከተ በቀጣይ ክትትል በማድረግ ተቀባይነት የሌላቸው ወጪዎች ካሉ ውድቅ በማድረግ የሚሰበሰብ ግብር ካለ የውሳኔ ማስታወቂያ በማውጣት የሚሰበሰቡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት*

በቀጣይ ውሳኔ እንዲወጣ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት*

ግብር ከፋዩ በአካል ቀርበው ያስረዳን ሲሆን ማስረጃውን ለማቅረብ ተስማምተው ከሄዱ በኋላ ተመልሶ ሊመጣ ባለመቻሉ ወደፊት በቀረበው አስተያየት መሰረት ማስተካካያ የምንወስድ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 2.7) ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሽ ግብር ብር 11,990,829.61 መኖሩ ግኝት

በየቅ/ፅ/ቤቶቹ ያሉ ግብር ከፋዮች ሐምሌ 30/2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 መሰረት ከ2006 በጀት ጀምሮ ኩባንያዎች ያገኙትን ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት እና ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እንዲያቀርቡ በሚያዘው መሰረት ማስረጃውን ማቅረብ እንዳለባቸውና ማስረጃውን ያላቀረቡ ኩባንያዎች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖች እንዳከፋፈሉ ተቆጥሮ ግብሩን መክፈል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ መሰረት አየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ግብር ከፋዮች ያገኙትን ትርፍ የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ያሳደጉ ስለመሆኑ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ ባለአክሲዮኖቹ እንደተከፋፈሉ በመቁጠር ቅ/ጽጽቤቶቹ ከግብር ከፋዮቹ መሰብሰብ የሚገባቸውን የትርፍ ክፍፍል ግብር ባለመሰብሰባቸው ከ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ

ብር 11,990,829.61 ያልተሰበሰበ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 15 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ መሰረት ግብር ከፋዮች ያገኙትን ትርፍ አክሲዮኑን ለማሳደጊያ ወይም አባላቶቹ ክፍፍል ስለማድረጋቸው የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ስለማቅረባቸው እየተጣራ የማይስተናገዱ ከሆነ መንግስት ከትርፍ ክፍፍል ገቢ ግብር የሚያገኘውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቶቹ መመሪያው ባስቀመጠው የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር የጊዜ ገደብ መሰረት ግብር ከፋዮች ያልከፈሉትን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ግብር እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት***

ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብርን በተመለከተ ሐረር መድሀኒትና የህክምና መሳሪያዎች እና ሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃ/የተ/የግ/ማ ለካፒታል ማስፋፊያ ያዋሉበትን ማስረጃ እንደሚያቀርቡ እንዲሁም ኢንዱራንስ ኃ/የተ/የግ/ማ ላይ ወለድና ቅጣትን በመጨመር የግብር ውሳኔ እንዳሚወጣ በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ሐረር መድሀኒትና የህክምና መሳሪያዎች እና ሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃ/የተ/የግ/ማ በመመሪያው መሰረት የንግድ ትርፉ ለካፒታል ማሳደጊያነት የዋለ ስለመሆኑ ማስረጃው ከውልና መስረጃ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ የውሳኔ ማስታወቂያ ወቶላቸው የሚፈለግባቸውን የትርፍ ድርሻ ግብር እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መሰረት ኩባንያዎች ብቻ እንጂ የትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር እንዲከፍሉ የተጠቀሰው በሽርክና ማህበር የተደራጁ ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር መክፈል አስገዳጅ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ በግኝቱ ላይ ለተጠቀሱት በተወሰኑ ድርጅቶች ላይ የትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር መወሰን የማይቻል ሲሆን ለሌሎቹ መረጃውን አጣርተን የውሳኔ ማስታወቂያ የሚያወጡ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

የተጠቀሰው ሁኔታ ለማንኛውም ኢንቨስትመንት ላይ ለዋለ የትርፍ ድርሻ ሂሳብ ስለሆነና ሁሉም አክስዮኖችና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን የሚመለከት መመሪያ በመሆኑ የተሰጠው ምክንያት አጥጋቢ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

### *የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት*

የ2008 በጀት አመት የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር ከፋዮች የማስታወቂያ ጊዜ እስከ ሰኔ 30/2009 የበጀት አመት የግብር ከፋዮች መብት ሲሆን፣ ያሳወቁና ያላሳወቁትን በመለየት ተቋሙ መስራት የሚጀምረው በ2010 በጀት አመት ስለሆነ በእቅዳችን 312 ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን መረጃው ተይዞ በኦዲት ከተለዩት 22 ግብር ከፋዮች ውስጥ የ7 ግብር ከፋዮች በበድምሩ 1,349,694.27 የግብር ውሳኔ የወጣላቸው ሲሆን ለቀሪዎቹ በኦዲት የተለዩትን እና በተቋሙ የተለዩትን በያዝነው በጀት አመት ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል በማለት በስራ አመራር ምላሽላይ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተር አስተያየት

ውሳኔ ወቶላቸዋል የተባሉት 7 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ስለመውጣቱ ማስረጃው ከስራ አመራር ምላሹ ጋር ባለመቅረቡ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

### *የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት*

በመውጫ ስብሰባ ላይ ማስረጃዎች መኖራቸውና ከስብሰባ በኋላ እንደሚቀርብ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የቀረቡት ማስረጃዎች የታዩ ሲሆን የተቀሩት በኦዲት ግኝት መሰረት ግብሩ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

### *የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት*

በመውጫ ስብሰባም ሆነ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

## 2.8) <u>በወሩ መከፈል ያለበት የተጣራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 500,215.81 ያልተሰበሰበ መሆኑ</u>

### <u>ግኝት</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ክፍል 7 አንቀጽ 26/1/ለ መሰረት እያንዳንዱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ታክሱን መክፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 21 እና 26 ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው በደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ መቅረቡን፣ ተቀናንሶ መሰላቱን እንዲሁም የተመላሽ ሂሳብ በትክክል ወደ ሚቀጥለው ወር መተላለፉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች የከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል ካሳወቁት ያነሰ በመሆኑ እንዲሁም በገገርው በተያዘው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ ባለመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 500,215.81 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 16 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### <u>ስጋት</u>

በቅ/ጽ/ቤቶቹ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍሉ ድርጅቶች ታክሳቸውን በሚያሳውቁበት ጊዜ በሚያስታውቁት መሰረት እንዲከፍሉ የማይደረግ ከሆነ እና በገገርው ተከናሽ በተደረገው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ መጠን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የቅ/ጽ/ቤቶቹ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች በየወሩ የሚያሳውቁትን የሽያጭ ገቢ በማስታወቂያ ላይ በአግባቡ እንዲገልጹ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ያልተሰበሰበውንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ወለድና መቀጫውን በመጨመር መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡

### <u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>

*<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>*

ያልከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ዕዳ እንዲከፍሉ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ማውጣታቸውን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

***ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማስደረግ በቀጣይ አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡***

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ቅ/ጽ/ቤት***

***በቀሪነት ለሚታየው አልተሰበሰበም ለተባለው ግብር በመውጫ ስብሰባም ሆነ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ምላሽ አልተሰጠም፡፡***

## 2.9) ***በሽያጭ ማጠቃለያ/Zreport/ ላይ በተገለጸው የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰረት ታክሳቸውን ባለማሳወቃቸው ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 4,366,021.82 መኖሩ***

***ግኝት***

***ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የሽያጭ ማጠቃለያ***/Z-Report ***መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን አስታውቀው እየከፈሉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያስታወቁት የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን በሽያጭ ማጠቃለያ***/ Z-Report ***ላይ ካስታወቁት ያነሰ በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ባለመቅረቡና በሽያጭ ማጠቃለያ ላይ በተገለጸው መሰረት እንዲከፍሉ ባለመደረጉ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ*** 4 ***ቅ***/***ጽ***/***ቤቶች በድምሩ ብር*** 4,366,021.82 ***መኖሩ ታውቋል፡፡ (ግኝቶቹ በአባሪ 17 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***

***ስጋት***

***በቅ/ጽ/ቤቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍሉ ድርጅቶች ታክሳቸውን በሚያሳውቁበት ጊዜ በሽያጭ ማጠቃለያ ላይ የሚታየው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠንና በማስታወቂያው ላይ የሚታየው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን እየተነጻጸረና ልዩነቱ እየተጣራ እንዲከፍሉ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊያሳጣው ይችላል፡፡***

***የማሻሻያ ሃሳብ***

***ቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከፋዮች በየወሩ የሚያሳውቁትን የሽያጭ ገቢ ከማጠቃለያ የሽያጭ ሪፖርት ጋር በማነጻጸር ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ያልተሰበሰበውንም የተጨማሪ እሴት ታክስ ወለድና መቀጫውን በመጨመር መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡***

## *<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>*

*<u>የምስራቅ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት</u>*

በቀጣይ የውሳኔ ማስታወቂያ የምንሰጣቸው ነው የሚሆነው በማለት በሰጡ ምላሽ ገልፅዋል፡፡

*<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>*

ማስረጃ ቀርቦ ትክክለኝነቱ እንዲጣራ በመውጫ ስብሰባ ላይ ከስምምነት ተደርሷል፡፡

*<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>*

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የመከላከያ ኮንስትራክሽንን ይቀርባል ከተባለው ማስረጃ ውስጥ የየካቲት 2008 ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

*<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>*

እንዲከፍሉ የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣ ሲሆን በቀጣይ ተከታትለው የሚያስከፍሉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

*<u>የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት</u>*

አራት ግብር ከፋዮች የግብር እዳ ውሳኔ የወጣላቸው መሆኑን፣ እንዲሁም አደምና ቤተሰቦቹ፣ ሂሚትረን ትራንዚት፣ ኤሲ ቢጄ፣ ጂጄ ላቮግላስ በካሽ ሪጅስተር ስህተት የተፈጠረ በመሆኑ ተመላሽ መፈቀዱን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

*<u>የኦዲተር አስተያየት</u>*

በካሽ ሪጅስተሪ ስህተት ተመላሽ በጠየቁት መሰረት ተመላሽ የተጠየቀበት ቅጽም ሆነ በቅ/ጽ/ቤቱ የተፈቀደበት ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

### 2.10) <u>በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ በድምሩ ብር 4,070,094.00 መኖሩ</u>

*<u>ግኝት</u>*

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ መቅረቡን፣ ተቀናንሶ መሰላቱን እንዲሁም የተመላሽ ሂሳብ በትክክል ወደ ሚቀጥለው ወር መተላለፉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ተመላሽ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ወር ሲተላለፉ በአግባቡ የማይተላለፉ በመሆኑ በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብምሩ ብር

4,070,094.00 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 18 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

ተመላሽ ሂሳብ ትክክለኛ የገንዘብ መጠን ይዞ የማይዞር ከሆነ ለቅ/ጽ/ቤቱ ተከፋይ እዳ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ቅ/ጽ/ቤቱ ሊሰበስብ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል

**የማሻሻያ ሃሳብ**

በብልጫ ለተያዘው የተመላሽ ሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግለት እና ያልተሰበሰበውም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት***

ታምሬ እና ቤተሰቦቹ ኃ/የ/የግ/ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000044575 የታህሳስ/2009 የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የወጣለት መሆኑ እና ማስረጃውን ማቅረባቸውን ገልጸው ለቀሪዎቹ ግብር ከፋዮች ሙሉ በሙሉ የቀረበው አስተያየት ወስደን ወደፊት በሂደት የምንሰራ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት***

አልታድ ኃ/የተ/የ/ግ/ማ እና ሄኖክና ቤተሰቡ ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ ግብሩ ተወስኖ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የደረሳቸው ሲሆን ውሳኔው በመቃወም ለቅ/ፅ/ቤታችን ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ጽ/ቤት ቅሬታ አቅርበዋል በማለት በስራ አመራር ምላሽ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***

ለግብር ከፋዮች የግብር እዳ ውሳኔ ያወጣንላቸው መሆኑና በኦዲት ቡድኑ ተመላሽ ተብሎ የተያዘው ከፍ እንዲል በመደረጉ ማስተካከያ ሊሰራለት እንጂ የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ሊወጣለት አይገባም ተብሎ በኦዲት ቡድኑ የተገለጸው ለአሰና ትሬግንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የወጣ የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚጣራ ሲሆን ነገር ግን ለሌሎች ግብር ከፋዮች የወጣው የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ መውጣቱ ትክክል በመሆኑ በቀጣይ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 2.11 በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን፣ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን፣ የኤክሳይስ ታክሳቸውን እና የተርን ኦቨር ታክሳቸውን በአግባቡ የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች መኖራቸው

### ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 66 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ እና ለ ማንኛውም የደረጃ ሀ ግብር ከፋይ ከሆነ የግብር ዘመኑ በተጠናቀቀ በ 4 ወር ጊዜ ውስጥ የደረጃ ለ ግብር ከፋይ ደግሞ የግብር ዘመኑ በተጠናቀቀ በ 2 ወር ጊዜ ውሰጥ ገቢውን ማስታወቅ እንዳለበት፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/94 አንቀጽ 26 ቁጥር 2 መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ ግዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ያለበት ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ያለው ወር መጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት እንደሆነ እንዲሁም በኤክሳይስ ታክስ አዋጅ 307/95 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ ሀ) ቁጥር 2 መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ ግዜ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ያለበት ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ያለው ወር መጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት እንደሆነ እንዲሁም በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/2002 አንቀጽ10/ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና 2/ሀ/ እንዲሁም በቁጥር 3.0/146/05 በቀን 05/ሰኔ/2004 በወጣው ሰርኩላር አንቀጽ2/ንኡስ አንቀጽ2/ መሰረት ንግድ ስራ ፈቃድ አውጥተው ወደ ስራ የተሰማሩ አዳዲስ ግብር ከፋዮች የንግድ ስራ ፈቃድ ካወጡበት ከቀጣዩ ወር ጀምሮ የግብር ግዴታቸውን እየተወጡ ስለመሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ እና የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ግብር ከፋዮች ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠው የመጨረሻ የታክስ ክፍያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ታክሱን መክፈል አለበት ብሎ ይደነግጋል፡፡ በየቅ/ጽ/ቤቱ በእነዚህ አዋጆች መሰረት ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፋቸውን፣ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያስታውቁ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትል እያደረገ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከየቅ/ጽ/ቤቱ ለናሙና ከመረጥናቸው ድርጅቶች ውስጥ የሽያጭ ገቢያቸውን ወይም ግብራቸውን ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች፤

| ቅ/ጽቤት | ቫት ያላሳወቁ ብዛት | ንግድ ትርፍ ያላሳወቁ ብዛት | ኤክሳይስ ታክስ ያላሳወቁ ብዛት | ተርን ኦቨር ታክስ ያላሳወቁ ብዛት | ግብራቸውን ያላሳወቁ ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| በአዳማ | 17 | 11 | 0 | 0 | 28 |
| በሀዋሳ | 1 | 1 | 1 | 0 | 3 |
| በምስራ አ/አ/መ/ግ/ከፋዮች | 0 | 0 | 22 | 0 | 22 |
| በድሬዳዋ | 0 | 23 | 0 | 0 | 23 |
| በጅማ | 1 | 8 | 0 | 0 | 9 |
| በኮምቦልቻ | 3 | 28 | 0 | 2 | 33 |
| በከፍተኛ ግብር ከፋዮች | 5 | 8 | 0 | 0 | 13 |
| በባህርዳር | 2 | 0 | 0 | 1 | 3 |
| በመቀሌ | 4 | 16 | 0 | 0 | 20 |
| በምዕራብ መ/ግ/ከፋዮች | 3 | 0 | 0 | 0 | 3 |
| ድምር | 36 | 95 | 23 | 3 | 157 |

*መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ግኝቶቹ በአባሪ 19 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን በወቅቱ አሳውቀው ግብራቸውን እንዲከፍሉ ክትትል የማይደረግ ከሆነ መንግስት በወቅቱ ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**<u>ማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ገቢያቸውን በወቅቱ እና በአግባቡ በማያሳውቁት ላይ በአዋጁ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡ ግብር ከፋዮቹ የገቢ ማስታወቂያቸውን እንዲያቀረቡ በማድረግ ሰነዱ በውስጥ ኦዲት ተጣርቶ የሚሰበሰብ ገቢ ካለ እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

የግብር ከፋዮቹ አድራሻቸውን ያጠፉና ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000022829 አርባምንጭ ጨርቃጨርቅ በተመለከተ የውሳኔ ማስታወቂያ ማውጣታቸውንና ለቀሪዎቹ ግብር ከፋዮች በቀጣይ እንዲያሳውቁ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የምስራቅ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

ምርት ሳይኖራቸው ላላሳወቁ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች መተማመኛ በማስሞላት መረጃውን እንደሚያያይዙ እንዲሁም ምርት ያላቸው ድርጅቶች ስለማሳወቃቸው ማስረጃ እናቀርባለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

### የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

በግኝቱ ላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ግብር ከፋዮች ንግድ ትርፍ ገቢያቸውን እንዲያሳውቁ የሚደረግ እና መክፈል የሚገባቸውም ግብር ካለ እንዲከፍሉ የሚደረግ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የጅማ ቅ/ጽ/ቤት

ባለማሳወቃቸው የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸው ግብር ከፈዮች ያሉ ሲሆን ውሳኔ ያልወጣላቸውን በቀጣይ አጣርተን ተገቢውን እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት

በ2009 በጀት ዓመት ሆነ በ2008 በጀት ዓመት ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ ያላሳወቁ ስለመሆናቸው በኦዲት የተገኙት ድርጅቶች በመጀመሪያ ድርጅቶቹ በራሳቸው እንዲያሳውቁ ክትትል እንዲደረግ ነገር ግን ቀርበው ማሳወቅ ያልቻሉትን በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ በግምት የሚወሰን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### የከፍተኛ ግብር ከፋች ቅ/ጽ/ቤት

ግብር ከፋዮቹ ግብር እየከፈሉ የሚገኙ ሳይሆን በክትትል ሂደት ሃብት ይዞ በመሸጥ ደረጃ ላይ የሚገኙ ግብር ከፋዮች በመሆናቸውና እያሳወቁ የሚገኙ ባለመሆናቸው በግኝቱ

አስተያየት መሰረት በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት ሂሳባቸው እንዲመረመርና በቅ/ጽ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ቡድን ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ምላሽ የሚሰጥበት መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት***

ለግብር ከፋዮቹ ውሳኔ እንዲወጣላቸው የተደረገ ግብር ከፋይ መኖሩ፣ በቀጣይ ውሳኔ የሚወጣላቸው ግብር ከፋይ መኖሩና እንዲሁም ድርጅታቸው የይዘጋልኝ ጥያቄ አቅርበው በኦዲት እየታየ ሚገኝ ግብር ከፋይ መኖሩን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

ቲ ኢ ኤም ኮንስትራክሽን ውሳኔ ስለመውጣቱ እንዲሁም ትዕዛዙ በቃሉ ህ/ሽ/ማ የይዘጋልኝ ጥያቄ ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ላይ ማስረጃዎች መኖራቸውና ከስብሰባ በኋላ እንደሚቀርብ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የቀረቡት ማስረጃዎች የታዩ ሲሆን የተቀሩት በኦዲት ግኝት መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባም ሆነ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

### 2.12) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ያልተሰበሰበ ቅድመ ግብር እና ከግብር ከፋዩ ተቀናሽ ተደርጎ በአግባቡ ለግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያልተደረገ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 3,699,991.15 መኖሩ

**ግኝት**

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ግብር ከፋይ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው/ድርጅት/የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው/ድርጅት/ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ሠላሣ በመቶ(30%) ቀንሶ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በህግ ግብር ቀንሶ የማስቀረት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች የዕቃ/የአገልግሎት/ ግዥ

ሲፈጽሙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 በመቶ እያስቀሩ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በህግ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ስልጣን የተሰጣቸው ድርጅቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረቡ ድርጅቶች ግዢ ሲፈጽሙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 በመቶ መቀነስ ሲገባቸው 2 በመቶ ብቻ ተቀናሽ ያደረጉ በመሆኑ እና ከግብር ከፋዩ ላይ ተቀናሽ የተደረገው ተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ በተደረገው መጠን ገቢ እንዲሆን ባለመደረጉ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ቅድመ ግብር ከ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,699,991.15 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 20 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የሚደረገው ግብር በአዋጁ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ካልቻለ አንድ አይነት የግብር አሰባሰብ ስርአት እንዳይከተል እና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ግብር ቀንሰው የሚያስቀሩ ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 በመቶ ተቀናሽ ያደረጉ ስለመሆኑ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አሁንም ቢሆን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ባላቀረቡ ግብር ከፋዮች ላይ ያልተቀነሰው ግብር ከድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

- መቱ ዩንቨርስቲ በተመለከተ ፋይሉ በኦዲት ላይ ሲሆን በተገኘው ስህተት ላይ እንዲከፍል የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣለት መሆኑ፣
- የሮሰን ጀነራል ትሬዲንግን በተመለከተ ግብር ከፋዩ የሚገኘው ነቀምት በመሆኑና በወቅቱ ምላሽ እንዲሰጥ ሲፈለግ ሊገኝ ባለመቻሉ በቀጣይ ግብር ከፋዩ ላይ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት***

- ***ዘ ኢምራልድ አዲስ ሆቴል ኃ/የተ/የግ/ማህ እና አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህ የውሳኔ ማስታወቅያ የደረሳቸው ሲሆን ውሳኔው በመቃወም ለቅ/ፅ/ቤታችን የውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ከሚቴ ቅሬታቸውን ያቀረቡ መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ የገለጹ ሲሆን፡፡***
- ***ሂኖክና ቤተሰቡ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህ እና ቃሊቲ ኮንስትራክሽን መለያ ቁጥር ያላቸው መሆኑና በስህተት ማሳወቅያ ቅፅ ላይ ባለሞሞለቱ የተፈጠረ ስህተት መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ ሲሆን፣ በመውጫ ስብሰባ ላይም መለያ ቁጥር የላቸውም የተባሉት ከሲስተም ትክክለኛ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥራቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወጥቶ በማቅረብ ማረጋገጥ የሚገባ በመሆኑ ማስረጃው ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡***

***የኦዲተሩ አስተያየት***

*ሂኖክና ቤተሰቡ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህ እና ቃሊቲ ኮንስትራክሽን ከመውጫ ስብሰባው በኋላ ይቀርባል የተባለው መረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት ግኝቱ ሪፖርት ውስጥ እንደተካተተ ይቀጥላል፡፡*

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ቅ/ጽ/ቤት***

*ለግብር ከፋዮቹ የግብር ዕዳ ውሳኔ የወጣ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡*

## 2.13) ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት የሽያጭ ገቢያቸውን ባለማስታወቃቸው ያልተሰበሰበ ግብር ብር 21,451,462.61 ስለመኖሩ

## ግኝት

ግብር ከፋዮች የ2008 በጀት ዓመት ንግድ ትርፍ መግለጫ ላይ ባሳወቁትና በተካካሰላቸው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) 2% መሰረት መሆን ያለበት የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭን በንግድ ትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ላይ ያሳወቁት ጠቅላላ ሽያጭ ለማመሳከር ኦዲት ሲደረግ፡ በሂሳብ መግለጫው ላይ መታየት ያለበት የዓመቱ ጠቀላላ ሽያጭ ቢያንስ (የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ≥ ቅድመ ግብር X 50) መሆን ሲገባው ግብር ከፋዮቹ ያሳወቁት የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ከዚህ በታች በመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ

ግብር ከ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,451,462.61 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 21 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

***ስጋት***

ቅድሚያ ግብር ማስረጃ መሰረት ግብር ከፋዮች በገቢና ወጪ መግለጫው ላይ የሚያሳውቁት ጠቅላላ ሽያጭ እየተነጻጸረ ትክክለኛነት ተረጋግጦ ግብሩ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስትን ከገቢ ግብር ሊያገኝ የሚገባውን ግብር ሊያጣ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

***የማሻሻያ ሃሳብ***

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ከላይ የተጠቀሰውን ያልተሰበሰበ ግብር ወለድ እና ቅጣት ታክሎበት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

***የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ***

***የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት***

ብር 70,774,800.80 ያልተከፈለ ታክስ ሳይሆን ድርጅቱ በ2007 በጀት አመት ከስኳር ኮርፖሬሽን እና ከኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ድርጅት ጋር በነበረው የስራ ውል መሰረት ክፍያው የተቀበለው ከሂሳብ መዝጊያ በኋላ በ2008 በመሆኑ የቅድሚያ ተከፋይ ሂሳብ ደረሰኝ የተሰጠው ክፍያው በተፈፀመበት ጊዜ በመሆኑ ህጉም የሚፈቅደው የቅደመ ግብር ደረሰኙ በተቆረጠበት ጊዜ የሚያዝ በመሆኑ የተፈጠረ ልዩነት እንጂ የሚከፈል ታክስ አለመሆኑ ድርጅቱ ያቀረበው ማስረጃ አያይዘን አቅርበናል፡፡ በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ ሲሆን፣ ድርጀቱ የተመሰረተው በታህሳስ 2008 ማለትም በመጀመሪያ ከውሃ ስራዎች ድርጅት ጋር አንድ ከመሆናቸው በፊት ከሎጅሰቲክ አገልግሎት እና ከስኳር ኮርፖሬሽን ጋር በነበራቸው ውል ስምምነት መሰረት ገቢው በ2007 ገቢ የተደረገ ሲሆን ቅድመ ግብሩ የተቆረጠው በ2008 ማለትም ድርጅቶቹ ከተቀላቀሉ በኋላ የመጣ ልዩነት መሆኑን ለዚህም ማስረጃ እናቀርባለን በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የኦዲተሩ አስተያየት***

ከስብሰባው በኋላ ይቀርባል የተባለው ማስረጃ ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

***<u>የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በመውጫ ውይይት ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ ድርጅቱ የኮንስትራክሽን ድርጅት በመሆኑ ለግብር ከፋዩ ተፅፎ በክትትል ላይ ያለ መሆኑን እና ውጤቱን የምናሳውቅ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

**2.14) <u>በታክስ ኦዲት ውሳኔ መሰረት የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከግብር ከፋዮቹ ያልተሰበሰበ ግብር እና ታክስ ብር 6,219,889,149.10 መኖሩ</u>**

***<u>ግኝት</u>***

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77/1፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 31፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 10 እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308 አንቀጽ 13 መሰረት በታክስ ኦዲትም ሆነ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት ውዝፍ የግብር ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የግብር ዕዳቸውን በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ውሳኔ ደርሷቸው ያለባቸውን የግብር እና የታክስ ዕዳ እስካሁን ድረስ ባልከፈሉ ግብር ከፋዮች ላይ ንብረት በመያዝ ያለባቸውን የግብር ዕዳ ለመሸፈን እንዲሆን በአዋጁ መሰረት የንብረት መያዝ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በየቅ/ጽ/ቤቶቹ በጊዜ ገደቡ ሳይሰበሰብ የቆየ በ2009 በጀት ዓመት እና በባለፉት ዓመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ውዝፍ የግብር እና ታክስ ዕዳ ከ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 6,219,889,149.10 ሳይሰበሰብ የቆየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 22 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

***<u>ስጋት</u>***

መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ካልተሰበሰበ ከቆይታ ብዛት መሰብሰብ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ከመቻሉም በላይ መንግስት ሊሰበስበው ያቀደውን ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

***<u>ማሻሻያ ሀሳብ</u>***

የቅ/ጽ/ቤቶቹ ዕዳ ክትትል ቡድን ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የውሳኔ ማስታወቂያ ወጥቶላቸው ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ ያለባቸውን ዕዳ ለመሰብሰብ ቀጣይ እርምጃቸውን በመውሰድ ውዝፍ ዕዳውን ሊሰበስቡ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### *የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት*

ከግብር ከፋዮቹ በቀሪነት የሚፈለገው የግብር ዕዳ በቀጣይ የሚሠበሰብ ሲሆን የተደረሠበትን ውጤት ለውስጥ ኦዲት በሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት*

አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚችል ለግብር ከፋዮች በደብዳቤ የተገለጸላቸው ሲሆን አብዛኞቹ ግብር ከፋዮች በክትትል ላይ እንደሚገኙ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የምስራቅ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት*

በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ያሉትን የዕዳ መጠን ለማጣራት ሙከራ አድርገናል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

በግኝቱ ላይ በዝርዝር የተገለጹት ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቱ በዕዳነት መዝግቦ የያዛቸው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ከግብር ከፋዮቹ የሚፈለገው የግብርና ታክስ ዕዳ በአዋጁ መሰረት በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚገባው በመሆኑ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ያሉትን የእዳ መጠን ለማጣራት ሙከራ አድርገናል ብቻ ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

### *የጅማ ቅ/ጽ/ቤት*

በዘንድሮ እና በባለፉት ዓመታት የታክስ ኦዲት ግኝት ውሳኔ መሰረት በትክክል ገንዘቡ እንዳልተሰበሰበ በመግለጽ በብዛት ዕዳው የሚሰበሰበው ከመንግስት ዩኒቨርስቲ በመሆኑ በያዝነው የድርጊት መርሀ ግብር መሰረት ያልተሰበሰበውን ገንዘብ ከሚመለከተው የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅቶች በቀጣይ የምንሰበሰብ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት*

በግብር ከፋዮቹ ላይ አስፈላጊው ክትትል እያደረግን ሲሆን በቀጣይ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልጻለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*

በቀጣይ ክትትል እየተደረገ የሚሰበሰብ እና በተለያየ አቤቱታ ላይ የሚገኝ ያለ ጉዳይ በመስሪያ ቤቱ ኮሚቴ ተቋቁሞለት እየተሰራበት መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ወቅት እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት***

የግብር ዕዳ ውሳኔ ወጥቶላቸው ውሳኔውን ያልወሰዱ በመኖራቸውና ውሳኔ ደርሷቸው ያልከፈሉ ግብር ከፋዮች በመኖራቸው በቀጣይ ክትትል እየተደረገ መሰብሰብ ያለበትን የግብር ዕዳ የሚሰበስቡ መሆኑን በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ውይይት ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ ከስብሰባው በኋላ ማስረጃ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃው ያልቀረበና ከስራ አመራሩ ምላሽ ጋር አጠቃልለው እንደሚልኩ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው ባለመቅረቡ በኦዲት ግኝቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

***የምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***

እግድ ላይ ያሉት፤ስምምነት የገቡ እና ግብር ይግባኝ የሄዱ ተለይተው የሚቀርቡ መሆኑን እና በቀሪዎቹ ላይ በቀጣይ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 2.15) በደንበኞች አ/የስ/ሂ በግብር ከፋይነት ዝርዝራቸው ተይዞ በግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በኩል ግን በግብር ከፋይነት ያልተያዙ ግብር ከፋዮች መኖራቸው

**ግኝት**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ምዕራፍ 1 ክፍል 1 አንቀጽ 4 ማንኛውም በዚህ ህግ የሚሸፈን ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ግብር ከፋዮቹን ለይቶ በመመዝገብ ግብር እንዲከፍሉ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት በተገኘው መረጃ መሰረት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የሚታወቁት ግብር ከፋዮች በግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በኩል ተመዝግበው ከተያዙት ጋር ሲነጻጸር 12 ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ በልዩነት የታዩትን 12 ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት መዝግቦ ያልያዛቸው በመሆኑ ግብር ከፋዮቹ ገቢያቸውን እያሳወቁ የሚከፍሉ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

*(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.15/5 *ቀን 22/05/2010 ግኝት ቁጥር 1.2.7)*

***ስጋት***

*ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ግብር ከፋዮቹን በአግባቡ መዝግቦ የማይዝ፣ ግብር እየከፈሉ ስለመሆናቸው ቁጥጥር እና ክትትል የማይደረግ ከሆነ ፍትሀዊ የንግድ ውድድር እንዳይኖር እና የመንግስት ገቢም በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡*

***የማሻሻያ ሀሳብ***

*በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ የስራ ክፍሎች ስለግብር ከፋዮቻቸው አንድ አይነት መረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ገቢያቸውንም በማያሳውቁ ግብር ከፋዮም ተገቢውን ክትትል በማድረግ ቅ/ጽ/ቤቱ ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡*

***የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አመራሩ ምላሽ***

*በግብር አወሳሰንና አሰባብ በኩል አልተመዘገቡም የተባሉት ግብር ከፋዮችን በተመለከተ በተገኘው ግኝት የኦዲቱ ቡድን ካገኘው የመረጃ ስህተት እንጂ በቅ/ጽ/ቤቱ በግብር ከፋይነት ተመዝግበው በግብር አወሳሰን ዝርዝራቸው ያልተያዘ ግብር ከፋዮች እነደሌሉ በመጥቀስ ይህ ስህተት የተፈጠረው ከደንበኞች አገልግሎት እና ከግብር አወሳሰን ባገኛችሁት የመረጃ ክፍተት መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡*

***የኦዲተሩ አስተያየት***

*በቅ/ጽ/ቤቱ የመረጃ አያያዝ ክፍተት እንዳለ የተገለጸ በመሆኑ በቀጣይ ቅ/ጽ/ቤቱ የግብር ከፋዮችን መረጃ በማጥራት ትክክለኛውን ዳታ መያዝ የሚገባው በመሆኑ በግኝቱ ላይም በአወሳሰን እና አሰባሰብ የስራ ሂደት አልተመዘገቡም የተባሉት ግብር ከፋዮች ተመዝግበው እንዲያዙ አስፈላጊውን ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡*

**2.16) *ኪሳራ በተደጋጋሚ ያሳወቁ ድርጅቶች ስለመኖራቸው***

***ግኝት***

*በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች በተደጋጋሚ ኪሳራ በሚያሳውቁበት ጊዜ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ለናሙና ከመረጥናቸው ግብር ከፋዮች ውስጥ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት* 2 *ግብር ከፋዮች ከ*2004 *ዓ.ም እስከ* 2008 *ዓ.ም እስከ ለ*3 *እና ለ*4 *ዓመታት ኪሳራ ያሳወቁ ቢሆንም ምንም ዓይነት ክትትል እና ማጣራት አለመደረጉን*

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.14/5 *ቀን 07/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.4)*

**<u>ስጋት</u>**

በተደጋጋሚ ኪሳራ በሚያሳውቁ ድርጅቶች ላይ ክትትልና ማጣራት የማይደረግ ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ቅ/ጽ/ቤቱ ኪሳራ በተደጋጋሚ ባሳዩት ድርጅቶች ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ ካለ መሰብሰብ ይኖርበታል ፡፡ ለወደፊቱም ኪሳራ በተደጋጋሚ የሚያሳዩ ድርጅቶችን ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

ኪሳራ የሚያሳውቁ ድርጅቶችን በተመለከተ በስጋት ስራ አመራር ተመርጠው የተለዩ ባለመሆኑ ሳይታዩ የቆዩ ሲሆን በግኝቱ መሰረት እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ድርጅቶቹ የይርጋ ጊዜያቸው እየመጣ ስለሆነ በቀጣይ በታክስ ኦዲት እንዲታዩ የሚደረግ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 2.17) <u>የጥገና እና የማሻሻያ ወጪ አቀናነስ ስሌቱ በህግ በተደነገገው መሰረት የተሰላ ባለመሆኑ ያልተሰበሰበ ፍሬ ግብር ብር 283,524.75 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 608/2001 አንቀጽ 3 መሰረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ለንግድ ስራው ቋሚ ንብረት የተደረገ የጥገናና የማሻሻያ ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡ ወጪው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው የዕቃ ሃያ ከመቶ በላይ ከሆነ ሙሉ በሙሉ በዕቃው የዘመኑ ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተደምሮ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሰረት ይታሰባል ብሎ ይደነግጋል፡፡ በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች የሚያስይዙት የጥገናና የማሻሻያ ወጪ በአዋጁ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ለጥገናና ለማሻሻያ ወጪ የሆነው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው የዕቃ ዋጋ ሃያ

ከመቶ በላይ መሆኑ እየታወቀ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሰረት ካፒታላይዝ በማደረግ የእርጅና ቅናሹ መሰላት ሲገበው ወጪውን ሙሉ በሙሉ በወጪ በመያዙ ያልተሰበሰበ ፍሬ ግብር በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 283,524.75 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 23 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን አስታውቀው ከሄዱ ቡኃላ በማስታወቂያው እና በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚገልጹትን የጥገናና የማሻሻያ ወጪ ከቋሚ ዕቃው የመዝገብ ዋጋ ከ20 በመቶ የሚበልጥ ስለመሆኑ የማይጣራ ከሆነ በወቅቱ መሰብሰብ ያለበት ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ድርጅቶች ለጥገናና ማሻሻያ ያወጡት ወጪዎች ከእቃው የመዝገብ ቀሪ ዋጋ ከ20 በመቶ በላይ ከሆነ ወጪውን ካፒታላይዝ በማድረግ በእርጅና ቅናሽ ስሌት መሰረት እንዲያዝ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ያልተሰበሰበው ፍሬ ግብር ወለድና መቀጫውን በመጨመር ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

በግኝቱ መሰረት ለግብር ከፋዮቹ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተደውሎ የተነገራቸው በመሆኑ ማስረጃው ሲቀርብልን አጣርተን ውጤቱን የምናሳውቅ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የምዕራብ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***

የእርጅና ቅናሽ ማስረጃ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የሚቀርብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ይቀርባል የተባለው ማስረጃ ባለመቅረቡ ግኝቱ ይቀጥላል፡፡

## 2.18) <u>በገቡት የክፍያ ስምምነት መሰረት ውል ገብተው በውሉ መሰረት ክፍያ መፈጸም ያልቻሉና ውላቸውን ያቋረጡ በመኖራቸው ያልተሰበሰበ የግብር ዕዳ ብር 242,399.34 መኖሩ</u>

### <u>ግኝቱ</u>

*በመመሪያ ቁጥር* 55/2003 *ምእራፍ* 3 *አንቀፅ* 13 *እንደተገለፀው በክፍያ ግዜ ስምምነት በሚገባቸው የግብር እና ታክስ እዳዎች ቢያንስ ሀያምስት በመቶ*(25) *በቅድሚያ ክፍያ ተፈፅሞ ቀሪው እዳ ክፍያ እንዲፈፀም ስምምነት ለሚገባቸው ወራቶች እኩል ተካፍሎ ክፍያ እንዲፈፀም ብሎ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ አንቀፅ* 11፣ 12 *እና* 13 *እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በ አንቀፅ* 17 *እንደተጠቀሰው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት በየወሩ እዳውን የማይከፍል ወይም መክፍል ያቋረጡ ግብር ከፋይ ያለተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የክፍያ ጊዜ ስምምንት ተቋርጦ ቀጣይ የግብርና ታክስ አሰባሰብ ስነስርዓት ይተገበራል ይላል፡፡ በመሆኑም **በጅማ ቅ/ፅ/ቤት** ውል የገቡ ግብር ከፋዮችን በውሉ መሰረት ክትትል እየተደረገ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-* 3 *ግብር ከፋዮች በገቡት የክፍያ ስምምነት መሰረት ዕዳቸውን ያልከፈሉ መሆኑ እየታወቀ በመመሪያ መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰዳባቸው በመሆኑ ብር* 242,399.34 *አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.14/5 *ቀን 07/06/2010 ግኝት ቁጥር 1.11)*

### <u>ስጋት</u>

*የታክስ ኦዲት ውሳኔ ተሰጥቶበት እንዲሁም በውላቸው መሰረት ይሰበሰባል የተባለው ግብር የስራ ክፍሉ ተገቢውን ክትትል እያደረገ ግብሩን የማይሰበስብ ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡*

### <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ቅ/ጽ/ቤቱ *በውሉ መሰረት የግብር ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑት ላይ ውሉን በመሰረዝ ወደ ቀጣይ የግብር መሰብሰብ ስርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ የሚፈለግባቸውን ግብር እና ታክስ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡*

### <u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>

*ጉርጉርቶ እና እሰማኤል ኢብራሂም በተመለከተ የግብር እዳውን* 25 *በመቶ ከፍለው ውል የገቡ ቢሆንም በውሉ መሰረት ክፍያውን መፈጸም ስላልቻሉ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የተጻፈባቸው ሲሆን፣ ደጓጃ ንግድ ስራን በተመለከተ የመጨረሻ ዙር ክፍያና አስተዳደራዊ*

*መቀጫ ሲቀረው ያቋረጠ ቢሆንም ከፍያውን እንዲፈጸም የማስጠነቀቂያ ደብዳቤ የተጻፈለት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡*

## 2.19) *<u>የዜድ ሪፖርት ማስረጃ ከግብር ማሳወቂያው ጋር ተያይዞ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ</u>*

***<u>ግኝት</u>***

*የሽያጭ መመዝገቢያ የሚጠቀም ማንኛውም ንግድ ድርጅት ዓመታዊ እና ወርሃዊ ግብር በሚከፍልበት ጊዜ በሽያጭ ማጠቃለያ/ዜድ ሪፖርት ላይ ባሳየው ሽያጭ መጠን መሰረት ዓመታዊ ንግድ ትርፍም ሆነ ወርሃዊ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲያሳውቁ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በተገኘ ወርሃዊ ማጠቃለያ ዜድ ሪፖርት* (summery report) *መሰረት ስለመሆኑ ከሰነዱ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ በ* 2 *ቅ/ጽጽቤቶች በድምሩ* 12 *ግብር ከፋዮች በማስረጃው መሰረት አሳውቀው ስለመከፈላቸው ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (ግኝቶቹ በአባሪ 24 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

***<u>ስጋት</u>***

*ወርሃዊ ግብር የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች በዜድ ሪፖርት መሰረት ግብራቸውን አሳውቀው ክፍያ የማይፈጽሙ ከሆነ የሚሰበሰበው ወርሃዊ ግብር ትክክለኛነት ማረጋገጥ አዳጋች ሊያደርገው ይችላል፡፡*

***<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>***

*ግብር ከፋዮች ወርሃዊ ግብራቸውን የሚያሳውቁበት ሰዓት በዜድ ሪፖርት መሰረት አሳውቀው ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚመለከታቸው የስራ ክፍል ሰራተኞች ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡*

***<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>***

***<u>የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

*ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ አ.ማ እንዲያቀርብ የተነገራችው ሲሆን አዲስ አበባ ጭምር ቅርንጫፍ ያላችው ስለሆነ እና የሁለት ዓመት ስለተጠየቁ በተጨማሪም የአንዳንዶቹ ማሽኖች ማስታወሻ የተቀየረ በመሆኑ ዜድ ሪፖርት አሁን ለማውጣት የማይቻል ሲሆን የቀሪ ማሽኖች እንዲያቀርቡ የሚደረግ ይሆናል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡*

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ላይ ማስረጃዎች መኖራቸውና ከስብሰባ በኋላ እንደሚቀርብ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ዝርዝራአው ለተጠቀሱት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም በኦዲት ግኝት መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.20) **በመንግስት መ/ቤቶች ተቆርጦ ለቀረው ተጨማሪ እሴት ታክስ ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ግብር ብር 16,917.53 መኖሩ ግኝት**

ግብር ከፋዮች በየወሩ በሚያቀርቡት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ ተቀናሽ የሚደረግላቸው በመንግስት መ/ቤቶች ተቆርጦ ቀሪ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ (Government Voucher) ማስረጃ በትክክል እየቀረበ መቀናነሱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ከግብር ከፋዮች በመንግስት መ/ቤቶች ተቆርጦ የተቀነሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ትክክለኛ ስለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ **በምዕራብ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት** ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ ላይ በድምሩ ብር 16,917.53 ተቀናሽ የተደረገው ሂሳብ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8 ቀን 13/07/2010 ግኝት ቁጥር 1.11)*

**ስጋት**

በግብር ከፋይ ማሳወቂያ ላይ ተቀናሽ የሚደረጉ ሂሳቦች በማስረጃ መሰረት የማይቀናነሱ ከሆነ መንግስት ሊሰበስብ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቱ ማስረጃዎች በትክክል መሟላታቸውን እያረጋገጠ ተቀናሽ በማድረግ ታክሱ በትክክል እንዲሰበሰብ ሊያደርግ ይገባል፡፡ አስፈላጊው ማስረጃም ሊቀርብ ካልቻለ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ወለድና መቀጫውን በመጨመር ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የምዕራብ አ/አ/ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

**2.21) <u>የግብር ዕዳ ውሳኔ ባለመስማማት ለቅ/ጽ/ቤቱ አቤቱታ አቅርበው ቅሬታቸው ውሳኔ ሳያገኝ የቆየ ብር 1,619,812,240.90 መኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 105 መሰረት አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት በሚለው መሰረት በወቅቱ ውሳኔ መሰጠቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ግብር ከፋዮቹ በግብር ዕዳ ውሳኔው ባለመስማማት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ቅሬታቸው በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሳይታይ የቆየ የግብር ዕዳ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,619,812,240.9 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 25 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታቸው በወቅቱ ታይቶ እልባት የማይሰጥ ከሆነ መሰብሰብ የሚገባው የመንግስት ግብር በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እንዲታይ የቀረቡ ቅሬታዎች አፋጣን ምላሽ እንዲሰጣቸው ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል ተደርጎበት በውሳኔው መሰረት መሰብሰብ ያለበት ግብር ካለ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>***

አቤቱታ ላይ ከነበሩት 10 ድርጅቶች 7ቱ ድርጅቶች ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ 3 ድርጅቶች አሁንም አቤቱታ ላይ መሆናቸው እንገልፃለን በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ

ሲሆን በመውጫ ስብሰባ ላይ ውሳኔ አግኝተዋል ለተባለው 7 ድርጅቶች ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በተገለጸው መሰረት ለ10 ሩም ድርጅቶች በቀጣይ አቤቱታ ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን በማለት ገልጸዋል፡፡

***የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት***

- ቅርጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ ከጀመረ ጀምሮ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማስታወቂያዎችን በትኩረት ይዞ የሚከታተል ሲሆን፣ የተለዩ ቅሬታዎች የበላይ አካል ውሳኔ የሚፈልጉ እንደ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከታክስ ነጻ እንደሚደረጉ በቃል የገለጸ መሆኑና በጽሁፍ እስኪገልጹ ድረስ የታክስ ህግ ማስከበር ስራ ተፈጻሚነት እንዲዘገይ በቁጥር 6.1.0/1772/61/ ቀን 16/ነሀሴ/2005 ዋናው መ/ቤት የጻፈና ሂደቱ የቆመ መሆኑን፤
- አምስት ቅሬታዎች የገቢያ ማዕከላት ሲሆኑ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራር ግንዛቤ ሳይያዝበት የቆየና አሰራሩ ግልጽና ወጥ ባለመሆኑ አጠቃላይ ጥናት ተደርጎ ውጤቱ እስኪገለጽ ተወስነው የተጠየቀው ታክስ አፈጻጸም እንዲቆም በቁጥር 6.1.0/635/09 ቀን 30/ሰኔ/2009 አቅጣጫ የተሰጠ በመሆኑ ሂደቱ ያቆመ መሆኑን፡፡
- አራት ቅሬታዎች ታክስ በመሰወርና በማጭበርበር ወንጀል ተጠርጥረው በምርምራና በክስ ሂደት ላይ ያሉ በመሆናቸው የመከራከር አቅምን ከማስከበር አንጻር ውሳኔ እስኪያገኙ የሚጠበቅ መሆኑን፤
- አንድ ቅሬታ የታክስ ውሳኔ በባንክ ሂሳብ መሰረት የተወሰነ በመሆኑ አፈጻጸሙ እንዲቆይ በዋናው መ/ቤት የተገለጸ ቢሆንም አሁን የአፈጻጸም መመሪያ ስለተላለፈ በመታየት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2.22) <u>በንግድ ሥራ ግብር ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በ Z ሪፖርት ላይ ከታየው ሽያጭ ጋር ልዩነት በመኖሩ ያልተሰበሰበ ግብር ብር 2,650,787.58 ስለመኖሩ</u>

### <u>ግኝት</u>

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት በንግድ ሥራ ግብር ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ በአመታዊ ማጠቃለያ (Z-Report) ላይ በታየው ሽያጭ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ***በምዕራብ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት*** ግብር ከሚከፍሉ ድርጅቶች ውስጥ፤

- አደምና ቤተሰቦቹ ኃ/የተ/የግ/ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0002587188 በ2008 በጀት ዓመት ዜድ ሪፖርት ላይ የሚታየው ጠቅላላ ሽያጭ ብር 2,311,561.34 ሆኖ ሳለ በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ ብር 2,274,014.49 በመሆኑ በልዩነት ብር 37,546.86 ምክንያት ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 11,264.05 የሚታይ መሆኑ፣
- ሂሚትረን ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር/0074204276/ በዜድ ሪፖርት መሰረት በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ ማሳወቅ የነበረበት ጠቅላላ ሽያጭ ብር 10,178,843.83 ሆኖ ሳለ ያሳወቀው ጠቅላላ ሽያጭ ብር 9,073,440.23 በመሆኑ እንዲሁም ድርጅቱ ባቀረበው የውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ሪፖርት ላይ ያልተገለጸ የተሸጡ እቃዎች ዋጋ (CGS) ብር 7,968,063.62 በመቀነሱ ንግድ ትርፍ ሊከፈልበት የሚገባ የተጣራ አመታዊ ገቢ ብር 8,798,411.76 ሆኖ ሳለ ኪሳራ ብር 250,028.45 የታየ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 2,639,523.53 የሚታይ ከመሆኑም በላይ ድርጅቱ ያለ አግባብ የተካካሰለት ሂሳብ በቀጣይ ግብር እንዳይሰበሰብበት የሚያደርግ ሲሆን በአጠቃላይ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 2,650,787.58 መኖሩ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.20/8 *ቀን 13/07/2010 ግኝት ቁጥር 1.4 ላይ ይመልከቱ )*

## ስጋት

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሚያሳውቁበት ሰዓት ገቢያቸውን በማሳወቂያ ቅጹ ላይ ሙሉ በሙሉ በትክክል እየሞሉ የማያሳውቁ ከሆነና ካቀረቡት የኦዲት ሪፖርት ጋር የማይመሳከር ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሃሳብ

ግብር ከፋዮች ያመኑበትን ግብር ከፍለው እንዲሄዱ ከተደረገ በኋላ የማስረጃውን እና የሂሳቡን ትክክለኛነት በሚመለከተው የስራ ክፍል በማረጋገጥ መሰብሰብ ያለበትን ግብር ክትትል በማድረግ ወለድና መቀጫውን በመጨመር እንዲሰበሰብ ሊደረግ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ

- ሂሚትረን ትራንዚት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ልዩነቱ የመጣው ድርጅቱ ትራንዚተር በመሆኑ ስለ አስመጪዎች የጉምሩክ እና የወደብ ላይ ወጪዎችን ስለሚከፍልላቸው የከፈለውን ወጪ

ከአስመጪዎች ላይ ሲቀበል በገቢ ደረሰኝ በመሰብሰቡ እንደ ገቢ ሊታይ ችሏል፡፡ በመሆኑም በጠቅላላ ኦዲት ጊዜ በትክክል ከኮሚሽን ያገኘውን ገቢ ማሳወቁን የምናጣራ ይሆናል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል

- አደምና ቤተሰቦቹ በመውጫ ስብሰባም ሆነ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

**<u>የኦዲት አስተያየት</u>**

ትራንዚተሩ የአስመጪውን የወደብ ላይ ወጪዎችን የከፈለ ስለመሆኑና ሂሳቡም በወጪ ስለመያዙ የሚያስረዳ መረጃ በለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ባለመቻሉ ከላይ በተባለው መሰረት የማጣራት ስራው ተሰርቶ ምላሹ ሊገለጽልን ይገባል፡፡

## 2.23) <u>በታክስ ኦዲት ውሳኔ መሰረት የደመወዝ ወጪያቸውን በዓመታዊ የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ ያልገለጹ በመሆኑና ወጪው ከፍ እንዲል በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 5,776,344.36 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በገቢ ግብር አዋጅ 286/ አንቀጽ 20 ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ሥራው ገቢ ለማግኘት፣ ለንግድ ሥራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ በሚለው መሰረት ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር ላይ የሚያሳውቁት የደመወዝ ወጪ በየወሩ ለሰራተኞች ለሚከፍሉት የደመወዝ ግብር ላይ ባሳወቁት የዓመቱ የደመወዝ ዝርዝር መሰረት መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ***በምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት*** ግብር የሚከፍለው ካጂማ ኮርፖሬሽን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000056605 ግብር ከፋዩ የ2008 በጀት ዓመት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ባለማሳወቁና ባለመክፈሉ በቅ/ጽ/ቤቱ ታክስ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ በተገኘ የኦዲት ውጤት መሰረት የበጀት ዓመቱ የደመወዝ ወጪ ብር 41,376,327.00 መሆን ሲገባው ድርጅቱ በዓመታዊ ንግድ ትርፍ ግብር ላይ እንደ ወጪ የተያዘለት ደመወዝ ብር 60,630,808.19 በመሆኑና በልዩነቱ ብር 19,254,481.20 በታክስ ኦዲተሩ ማስተካከያ ያልተሰራለት በመሆኑ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 5,776,344.36 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8 ቀን 13/07/2010 ግኝት ቁጥር 1.13 ላይ ይመልከቱ)*

**<u>ስጋት</u>**

ግብር ከፋዮች በየወሩ የደመወዝ ግብር ለመክፈል የሚያሳውቀው ደመወዝ መሰረት ዓመታዊ ግብሩ ላይ የደመወዝ ወጪን የማያሳውቅ ከሆነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚገባውን ግብር ሊያጣ የሚችክ ከመሆኑም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

የስራ ክፍሉ ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ግብር ሊሰበስብ የሚገባ ሲሆን ድርጅቱ ያላሳወቀውን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር በማሳወቅ እንዲከፍል ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

ካጅማ ኮርፖሬሽን ልዩነቱ የመጣው በታክስ ኦዲቱ የስራ ግብር ውሳኔ ላይ የታየው የደመወዝ ክፍያ መጠን የተወሰደው በፌደራል መንግስት መስተዳደር ላይ ለተከፈሉ ክፍያዎች ስለሆነ በሂሳብ መግለጫ ላይ ያሳየው የደመወዝ ወጪ ግን ስራውን በሰሩበት ክልል የከፈሉትን ደመወዝ ወጪን ጨምረው በመያዙ ልዩነት ሊመጣ የሚችል በመሆኑ በቀጣይ ማስረጃው ክልል ላይ የተከፈለው ታይቶ የሚወሰን ይሆናል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

**2.24) ያልተሰበሰበ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ብር 18,650.10 መኖሩ**

**ግኝት**

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ክፍል ሁለት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በሚገልጸው አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው እያንዳንዱ ክፍያ ላይ ግብርን መቀነስ፣ የተቀነሰውን ግብር በየወሩ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት በሚለው መሰረት በቅ/ጽ/ቤቱ ከመቀጠር የሚገኝ ግብር የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች በትክክል ግብራቸውን የሚያሳውቁና የሚከፍሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ***በምዕራብ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት*** ግብር የሚከፍለው የተባበሩት እንጅነሪግ ኃ/የተ/የግ/ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000009817 የሆነ ድርጅት አሳውቆ በከፈለው የሶስት ወር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ማስረጃ መሰረት መከፈል የነበረበት የሥራ ግብር ብር 616,371.67 ሆኖ ሳለ ተከፍሎ የተገኘ ግን ብር 597,719.57 በመሆኑ በልዩነቱ ብር 18,650.10 ያልተሰበሰበ የስራ ገቢ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8 ቀን 13/07/2010 ግኝት ቁጥር 1.14 ይመልከቱ)

**ስጋት**

ከመቀጠር የሚገኝ የገቢ ግብር ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ በስሌቱ መሰረት የማይሰበሰብ ከሆን የመንግስት ከመቀጠር ከሚያገኘውን ገቢ ግብር ሊያሳጣው ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

የስራ ክፍሉ ከመቀጠር የሚገኘውን የገቢ ግብር ትክክለኛነት በማረጋገጥ ሊሰበስብ የሚገባ ሲሆን ያልተሰበሰበውም ግብር ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

በመውጫ ስብሰባም ሆነ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ምላሽ አልተሰጠም፡፡

## II. የወጪ ሂሳብን በተመለከተ

### 1) ከቤት አበል እና ከሙያ አበል ያልተቀነሰ የስራ ግብር ብር 1,287,630.52 መኖሩ ግኝት

በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ….ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 እንዲሁም ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 11 በተገለጸው ሰንጠረዥ ሀ መሰረት ግብር የሚከፈልባቸው መሆኑን መስከረም 19/2008 በደብዳቤ ቁጥር 3.5.0/165/09 በገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሰረት የቅ/ጽ/ቤቱ ሰራተኞች በሚከፈላቸው አበልና ጥቅማ ጥቅም ተገቢውን የሥራ ግብር የከፈሉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ16 ቅ/ጽ/ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት እና ባለፉት የኦዲት አመት እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ በድምሩ ብር 1,287,630.52 ከቤት እና ከሙያ አበል ያልተቀነሰ የስራ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 26 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት ከተፈቀደለት ከግብር ነፃ መብት ውጪ ማንኛውም ዓይነት ጥቅማጥቅም ከደመወዝ ገቢ ጋር ተዳምሮ ግብር ሊከፈልበት የሚገባ መሆኑን ክትትል ማድረግና አሁንም ያልተሰበሰበውን ግብሩን በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***ሁሉም የቅ/ጽ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ***

- የአቃቢ ከገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/764 በቀን 20/10/2009 በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ግብር እንዳይከፈል በተደረገ ገቢ ላይ ወደ ኋላ ግብር እንዲከፈልበት ማድረግ በዜጎች ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር መሆኑን በመግለጽ ከመጋቢት 1/2007 እስከ ታህሳስ 30/2009 ድረስ ያለውን ሰርተው ወደ ዋናው መ/ቤት ያስተላለፉ መሆናቸውን
- ለወንጀል ምርመራ ባለሙያዎች ወደ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የተዛወሩ በመሆናቸው በኮሚሽኑ በኩል ከታህሳስ 2010 ጀምሮ ከደመወዛቸው እየቀነሰ ወደ መ/ቤታች ገቢ እንዲያደርጉ በደብዳቤ የተገለጸላቸው መሆኑን
- የIT ባለሙያዎችና ሎሎች ስራ መደባቸው ከወንጀል ምርመራ ወደ ሌላ መደብ ቀይረው በመ/ቤታችን ካሉ ሰራተኞች ከታህሳስ 2010 ጀምሮ ከደመወዛቸው መቁረጥ የጀመሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2) <u>ከግዢ (ከተከፋይ) ላይ ተቀናሽ የተደረገው የተ.እ.ታ ተከፋይ እና ቅድመ ግብር ብር 106,122.36 ስለመከፈሉ ደረሰኝ ያልቀረበና ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979 አንቀጽ 96 ላይ ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር ተቀንሶ በሚያዝበት ጊዜ፣ ግብሩን ቀንሶ የሚይዘው ሰው/ድርጅት ክፍያውን ለሚቀበለው ሰው ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት በሚለውና እንዲሁም በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር

27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ እንደሚገባ በሚያዘው መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በግዢ ምክንያት ከተፈጸመው ክፍያ ላይ ለቅድመ ግብር እና ለተ.እ.ታ ቀንሶ ወደ መንግስት ካዝና ፈሰስ ስለመደረጉ ማረጋገጥ ያልተቻለ እና ተቀናሽ ያልተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ በ4 ቅ/ጽ/በቶች በድምሩ ብር 106,122.36 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 27 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

በቅ/ጽ/ቤቱ ግዢ ሲፈጸም ከሚከፈለው ክፍያ ላይ ለሚቀነሰው ቅድመ ግብር እና የተ.እ.ታ ተከፋይ ደረሰኝ የማይቆረጥለት ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ቅ/ጽ/ቤቱ ለግዢ ከሚከፍለው ክፍያ ላይ ቀንሶ ለሚያስቀረው ተከፋይ ሂሳብ ተገቢውን ደረሰኝ ቆርጦ መስጠት ይኖርበታል፡፡ የቅ/ጽ/ቤቱ የውስጥ ኦዲትም በግኝቱ ለተጠቀሰው ተቀናሽ ሂሳብ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን እና ለመንግስት ፈሰስ የተደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ በሪፖርት ሊያሳውቀን ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶች የስራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>አዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በስህተት በወጪ ያልተመዘገበና ገንዘቡ ተቀንሶ ስለመቅረቱ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት፣ ገንዘቡም ፈሰስ ያልተደረገ እና እንደ ወጪም ያልተመዘገበ በመሆኑ ፈሰስ ከተደረገው ሂሳብ ጋር አብሮ የተያዘ ስለሆነ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመፃፃፍ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***<u>ጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

የቅድመ ታክስ እና የቫት ተቀናሽ ሂሳቦቹ ደረሰኝ የተቆረጠላቸው ቢሆንም በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ ለሚመለከተው የግብር ታክስ ባለመከፈሉ ወደፊት እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

***<u>ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ከድርጅቱ ተቀናሽ መደረግ የነበረበትን ብር 8,034.84 በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ ገቢ እንዲያደርጉ የተገለጸላቸው ሲሆን ገቢ ለማድረጋቸው ተከታትለን የምናሳውቅ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***ጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

ከቅ/ጽ/ቤቱ ተሸከርካሪዎች በሞኤንኮና በሪያስ ኢንጂነሪንግ ጥገና ሲደረጉ ክፍያዉን በተመለከተ ጠቅላላው ክፍያ በየካምፓኒዉ የባንክ አካዉንት ፊሰስ የተደረገ ቢሆንም የቅደመ ግብር 2% እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ 15% ያልተቀናሰ ሲሆን ከካምፓኒዎቹ ጋር በስልክ በተነጋገርነዉ መሠረት ደረሰኝ አምጥተዉ ተመላሽ እንደሚያደረጉልን የተገለፀልን ስለሆነ በቀጣይ ሂሰቡን ሰብስበን ማስረጃ የምናቀርብ ይሆናል በማለት፡፡

## 3) ***ከግዥ መመሪያ ውጭ የተፈጸመ የብር 2,152,264.93 ግዥ የሚታይ መሆኑ ግኝት***

በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 55 እንደተገለጸው የመንግሰት መ/ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ግዥው በሚኒስተሩ በሚወጣው የግዥ መመሪያ ከሚወስነው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም የዕቃ ግዥ የገንዘብ መጠኑ ከቀን 12/4/2008 ዓ/ም ተፈፃሚ የሚሆነው መመሪያው ለማሻሻል በወጣ ሰርኩላር መሰረት እስከ ብር 200,000.00 መሆኑንና የገንዘብ መጠኑ ከብር 200,000.00 በላይ ደግሞ የዕቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ የሚፈጸም መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ግዥዎች የሚፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በዋጋ ማቅረቢ በማወዳደር እንዲሁም በግልጽ ጨረታ መከናወን የነበረበት ግዥ ከመመሪያና ደንብ ውጭ የተፈጸመ ግዥ በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,152,264.93 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 28 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

***ስጋት***

የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ እንዲባክን ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

***የማሻሻያ ሀሳብ***

ቅ/ጽ/ቤቶች የግዥ ክፍያ ከመፈጸማቸው በፊት ግዥዎች በመመሪያው መሰረት የተከናወኑ ግዥዎች መሆናቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡ የሰራ ኃላፊዎች የግዥ ስርዓቱ ተከትሎ ግዥና የግዥ ክፍያ በማይፈጽም ሰራተኛ አስፈላጊ ቁጥጥር እና ክትትል ሊያደረርጉ ይገባል፡፡

***የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ***

***የባህር ዳር***

- ለደብረ ማርቆስ ማዕከል ቢሮ ኪራይ ለአምባሰል ንግድ ስራዎች ድርጅት የተከፈለው ታክስ ማዕከሉ ደ/ማ ላይ ለቢሮ እና አገልግሎት አሰጣጥ ያለበት ቦታ ለግብር ከፋዮች ማዕከላዊነት ያለው በመሆኑና ግንባታውም ተጠናቆ የተገኘ ከመሆኑም ባሻገር ድርጅቱ የልማት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ያለአግባብ የሆነ ክፍያ ሊጠይቅ እንደማይችል ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመነሻ የጨረታ ዋጋ የተገኘ መሆኑ እንዲሁም ድርጅት በካሬ ሜትር ከሌሎች እንጻር የተሸለው ዋጋ ያለው በመሆኑ መሆኑን፡፡
- ለድብ አንበሳ ሆቴልና ለሰመር ላንድ ሆቴል የተከፈለው ፕሮፎርማ ባይሰበሰብም ከተለያዩ ስራ ክፍሎች ኮሚቴ በማቋቋም ዋጋ ጥናት እንዲያደርጉ ተደርጎ ከተደረገው ጥናት በዋጋውም ሆነ ጥራትም የተሻለ ብሎ ኮሚቴው ያመነበትን እንዲሁም ለመድረኩ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለማመላለስ ያመች ዘንድ ያላቸው ቀረቤታ እና ታዳሚዎቹ ግብር ከፋዮች እንደመሆናቸው መጠን ሰፊና ምቹ የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም አዳራሽ ያላቸው መሆኑን ግንዛቤ ተወሰዶበትና የበላይ አመራሩም አምኖበት ሊፈጸም መቻሉን
- የትራንስፖርት አገልግሎት ግዥውን በተመለከተ የኮንትሮባንድ እቃዎችና የተገዙ እቃዎችን ለማጓጓዝ የተሰጠ አገልግሎት ሲሆን ዋጋ በየቦታው ከተገኙ መኪና አሽከርካሪዎች ጋር በመከራከርና በመስማማት የሚጫን ሲሆን ፕሮፎርማ ሰብስቦ፣ ከፍቶ አወዳድሮ እና አሸናፊውን ለይቶና ገልጾ ለመፈጸም አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***<u>የጋፋፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በአዋጅና መመሪያው መሰረት ያልተገዛ መሆኑን ያመንበት ሲሆን በወቅቱ የነበሩ አመራር ሲሰጡ እና ሲሰሩ የቆዩ አካላት በአሁኑ ሰዓት ተገኝተው መልስ ሊሰጡ ይገባ እንደነበር ገልጸዋል፡

***<u>የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ግልጽ ጨረታን ግዢን በተመከተ

ጨረታ  ሁለት ጊዜ ያወጣንበት መንገድ እንዳለ በዚህ መሰረት ከአካባቢው አስቸጋሪነት አንጻር በቂ አቅራቢ ባለመኖሩ እና ግዥው አስቸኳይ በመሆኑ ግዥውን ልንፈጽም ችለናል በማለት ገልጸዋል፡፡

የዋጋ ማወዳደሪያ ግዢን በተመለከተ

- ግዥው የአሳይታ ጉ/መቆ/ጣቢያ በ2008 በጀት ዓመት በዋጋ ማወዳደሪያ /POFORMA/ የግንባታ ጥገና እንዲካሄድ የተሰጠው ስራ ላይ አሸናፊው ድርጅት በተጨማሪነት የተሰጠው ስራዎች ሲሆኑ ስራዎች ስለመከናወናቸው ከጣቢያው ሃላፊዎች ጋር በጋራ ተረጋግጦና ሪፖርት ቀርቦ ክፍያው የተፈጸመበት መሆኑን፡-
- ለግንባታ አገልግሎት ግዥ በተመለከተ በ2009 በጀት ዓመት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር ተያይዞ ኬላዎች በ24 ሰዓታት ውስጥ እንዲቋቋሙ ትእዛዝ ስለተሰጠንና ለሰራተኞችና ለፌደራል ፖሊሶች ጊዜያዊ መጠለያና መስሪያ ቦታ ማዘጋጀት ስለነበረብን ለባቲ እና ጭፍራ ኬላዎች በተለያዩ ደረሰኞች ቆርቆሮ፣ሚስማር፣ጀሶ፣ቀለምና የተለያዩ ግዥዎች ሲሆኑ ግዥው የተፈጸመው በእቅድ ተይዞ የቢሮ እና የሰራተኞች የጋራ መኖሪያ ቤት የግንባታ እድሳትና ጥገና እንዲደረግ ነሀሴ 2008 ዓ.ም የግንባታ እቃ ለማቅረብ ተወዳድሮ ካሸነፈው አቅራቢ ድርጅት ሲሆን በአስቸኳይ PROFORMA በመበተን ግዥ ለመፈጸም ጊዜ ስላልነበረን በወቅቱ ለቢሮና ሰራተኞች መኖሪያ ቤት ጥገና ሥራ ማቴሪያል እንዲያቀርብ በበፊቱ ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥውን የፈጸሙ መሆኑን
- ቅ/ጽ/ቤታችን ለሰመራ ጉ/መቅ/ጣቢያ ሰራተኞች ሰርቪስ አገልግሎት እንድንሰጥ የተመደበው ተሽከርካሪ በድንገተኛ ብልሽት አዳማ ሞይንኮ ለጥገና በመግባቱ በውል ስምምነት በቀን ብር 1000.00 ለሰራተኞቹ የሰርቪስ አገልግሎት እንዲሰጥ የተከፈለ መሆኑን
- ለግንባታ ጥገና አገልግሎት የሚውል ግዥው ተፈፅሞ የተወራረደበት ምክንያት የባህር ዛፍ እንጨት እና የብሎኬት ግዥ የተፈፀመበት ሲሆን የባህር ዛፍ እንጨት ለባቲ ኬላ እና የጭፍራ ኬላ የፍተሻ አገልግሎት እንዲሰጥ፤ የብሎኬቱ ግዥ ደግሞ በመውጫ በር በኩል ለካፌና ለቢሮ አገ/የሚሰጥ ግንባታ እንዲሁም ለጀኔሬተር ኦፕሬተሮችና ለጥበቃ ሰራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን በወቅቱ ብቁ አቅራቢ ተወዳዳሪ ባለመኖሩ እና ስራው አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን የብሎኬት ግዥው ግን በፊት በፕሮፎርማ ተወዳድሮ ካሸነፈው ድርጅት የተገዛ መሆኑን፡-
- የፎቶ ኮፒ ቀለም ግዥ የተባለው ብራዘር ፕሪንተር ቀለም ግዥ ተብሎ እንድስተካከልልን እየጠየቅን በመንግስት ግዥና ንብረት ማሰወገድ አገልግሎት በኩል ለ3 ዓመት ኮንትራት

ውል ገብተው ለመ/ቤቱ የእቃ አቅርቦት እንዲያቀርብ ከብርጅቴክ ኃ/የተ.የግል ድርጅት የተገዛ መሆኑን፡-

- የፎቶ ኮፒ ቀለም ግዥ በአዋሽ ጉ/መቅ/ጣቢያና ለሚሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ከአልታ ኮምፒውተር ግዥው የተፈፀመ ሲሆን ከሰነዱ ጋር በአባሪነት እንደተያያዘው በሰአቱ ማሽኖች የተገዙት ከዚሁ ድርጅት በመሆኑ ለስራው ማስጀመሪያነት ከአልታ ኮምፒውተር አቅራቢ ድርጅት ግዥውን የተፈፀመበት መሆኑን፡-
- የግንባታ እቃ የሚለው አላቂ የቢሮ እቃዎች ተብሎ እንዲስተካከለልን እየጠየቅን ግዥዎቹ በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ በኩል አሸናፊ ድርጅቶች ለሶስት ዓመት ግዥ እንድንፈጽም በተሰጠ ትእዛዝ መሰረት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተር አስተያየት

- ጨረታ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ወቷል ቢባልም የብሔራዊ የጨረታ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፡፡
- ለጽዳት አገልግሎት ለተሰጠው ምላሽ የተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ያልተያያዘና አሸናፊ ተብሎ የቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ቀን የሌለው፣ በጨረታ መክፈቻ ተገኝቷል ተባሎ በቃለ ጉባኤ የተዘረዘሩ ተወዳደሪዎች ፊርማ ያልካተተ በመሆኑ፤
- ለቢሮ ሰራተኞች ጥገና ማቴሪያል እንዲያቀርብ በበፊቱ ዝቅተኛ ዋጋ ካሸነፈው ድርጅት ግዥውን የተፈጸመ መሆኑን ቢጠቅሱም ማረጋገጫ ሰነድ ያልቀረበ በመሆኑ፡-
- ለግንባታ ጥገና አገልግሎት የሚውል የብሎኬት ግዥው በፕሮፎርማ ተወዳድሮ ካሸነፈው ድርጅት በተጨማሪነት በበፊቱ ባሸነፈበት ዋጋ እንዲያቀርብ የተደረገ መሆኑን ማስረጃ ተያይዟል የተባለው የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፡-
- ብራዘር ፕሪንተር የፕሪንተር ቀለም TONNER TK3320 በሚል ሞዴል በአሸናፊው ድርጅት ዝርዝር ውስጥ የሌለ መሆኑን፡-
- የሻርፕ ፎቶ ኮፒ ቀለም ግዥ በማዕቀፍ ግዥ የተካተተ መሆኑን የሚያገጋግጥ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ
- የአላቂ የቢሮ እቃዎች በሰነዱ ላይ እንደተገለፁት የግዥ ማዕቀፍ ዉስጥ በሞዴላቸው እና ዋጋቸው የማይቀራረብ በመሆናቸው ያልተካተቱ እና ሊድ ፕሮጀክተር ኢፕሰን የጥቅምት ወር 2008 በጀት ዓመት በመሆኑ የተሰጡት ምላሾች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

## የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት

ግዢው ሊፈፀም የቻለው በኮንትሮባንድ መከላከል ዙሪያ የጥምር ኮሚቴ ስብሰባ ለማካሄድ ለአዳራሽ ኪራይና ለመስተንግዶ አገልግሎት ሲሆን፣ እኛ ባለንበት ከተማ ይህንን አሟልተው መጫረት የሚችሉ የሆቴል አገልግሎቶች ስለማይገኙ ከአንድ ድርጅት ውል በመዋዋል የቀጥታ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን ለወደፊቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተር አስተያየት

በሞያሌ ከተማ በተመሳሳይ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች የሚገኙ በመሆኑ ምላሹ አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## 4) የተሰራበት ቦታና ጊዜ ሳይጠቀስ፣ የውሎ አበል ፎርም ሳይሞላ የተከፈለው የምሳ አበል ብር 30,809.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለአለመቻሉ፣

## ግኝት

ሰኔ/2004 በወጣው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ወሎ አበል የአከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 9(1 እና 2) ላይ እንደተመለከተው ሰራተኛ ከመደበኛ ቦታው ወደ ሌላ ስፍራ ለስራ ከመላኩ በፊት የውሎ አበል መጠየቂያ፣መፍቀጃና መክፈያ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሰራተኞች ወይም የስራ ኃላፊዎች እንዲሞላ እንዲሁም ሲመለስ የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የስራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ በመሙላት ያከናወነውን ስራ በተመለከተ መግለጫ ይሰጣል በሚለው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሰራተኞቹ የት ቦታ ለስራ እንደተሰማሩ እና ለምን ያህል ቀን በስራ እንደቆዩ የሚገልጽ መረጃ ሳይኖር እና የውሎ አበል ፎርም ሳይሞላ ***በዋና መ/ቤት*** የተከፈለ የምሳ አበል ብር 30,809.00 በመኖሩ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.1/25 ቀን 01/05/2010 ግኝት ቁጥር 1.1 ይመልከቱ)*

## ስጋት

ከመመሪያ ውጭ የውሎ አበል ክፍያ የሚከፈል ከሆነ መንግስት ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርገው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ የውሎ አበል በሚከፍልበት ወቅት መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት አስፈላጊዎች ቅጾች እየተሞሉና እና የማስረጃውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ መወራረድ

ይገባል ፡፡አሁንም ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለው ሂሳብ በተመለከተ በውስጥ ኦዲት ሊጣራና ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ካለ ለመንግስት ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

**<u>ዋና መ/ቤት</u>**

ሐምሌ/2008 ሊወገዱ እና ሊጠገኙ የሚገባቸው ተሽከርካሪ ለመለየት በየቅርንጫፉ እና በየመጋዘኑ እየዞሩ ስራ ለሰሩ መካኒኮች እና ግንቦት/2009 የሰርቪስ አሰጣጥ ለማጥናት ለሰሩ የኮሚቴ አባላት የተከፈለ መሆኑን እና የት ቦታ እና ለምን ያህል የሚለውን በተዘጋጀው የማስፈፀሚያ መርሀ ግብር መሰረት ለ31 ቅ/ጽ/ቤት መሆኑን በሚገልጸው መሰረት አዲስ አበባ ለሚገኙ ቅርንጫፍ እና መጋዘን ለሰሩ መካኒኮችና የኮሚቴ አባላት የተከፈለ የምሳ አበል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

የማስፈጸሚያ መርሀ ግብሩ (TOR) የሚያሳየው ሊሰራ የታቀደውን ስራ እንጂ የተሰራ ስራ የማያሳይ በመሆኑና የተሰራበትን ቦታና ጊዜና ማን እንደሰራው እንዲሁም የውሎ አበል ፎርሙ ሳይሞላ የተከፈለ የውሎ አበል በመሆኑ የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

### 5) <u>በጨረታ ግምገማ ቴክኒክ መመዘኛ መሰፈርት መሰረት ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው መገዛት ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው በመገዛቱ በብልጫ የተከፈለ ብር 1,435,878.00 ስለመኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

የፌደራል መንግሰት ግዥና የንብረት አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀጽ 43/8/ሀ መሰረት በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው በጨረታ ግምገማ ቴክኒክ መመዘኛ ማሟላቱን የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች መሆኑን ያስቀምጣል ቅ/መ/ቤቶች በዚህ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ቫትን ጨምሮ ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ባቀረበበት ዋጋ መገዛት ሲገባቸው ቫትን ጨምሮ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት በመግዛታቸው በብልጫ ወጪ የሆነ በድምሩ ብር 1,435,878.00 ግዥው መከናወኑ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 29 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

በጨረታ አወዳድሮ ግዥዎች ሲፈጸሙ ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች የማይገዛ ከሆነ መ/ቤቱ ላላስፈላጊ ወጪ ከመዳረጉም በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

መ/ቤቱ የጨረታ የግምገማ ቴክኒክ መመዘኛዎች በአግባቡ በመገምገም ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ግዥ መፈጸሙን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ**

***የዋና መ/ቤት***

ግዥው በጨረታ ሲወጣ በአንድነት የደህንነት መፈተሻ መሳሪያ በሚል የወጣ በመሆኑ እና በቴክኒክ ግምገማው መሰረት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት ያቀረበው ማስረጃ ያልተሟላ በመሆኑ እንዲሁም የስልጠና እና ዝርጋታው ተያያዥነት ግምት ውስጥ በማስገባት ምክንያቱም ቴክኒክ የገመገመው አካል ማሽኖቹን የመግጠም እና ባለሞያዎችን የማሰልጠን ስራውንም ዕቃዎችን የሚያቀርበው ድርጅት በኩል እንዲፈጸም የሚል በመካተቱ አሸናፊነት ለአንድ ድርጅት መስጠቱ ለክትትልና ለስልጠና ዝግጅት አመቺ መሆኑን በማየት የተሰጠ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

የደህንነት መሳሪያዎቹ በጨረታ ጋዜጣው በአንድነት ተብሎ ያልወጣ እና አራት የተለያዩ የፍተሻ መሳሪያዎች ከመሆኑም በተጨማሪ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛ መሰፈርት ገምጋሚው ኤጀንሲ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት Walk through metal detector እና under veheicle inspection mirror ብቻ መወዳደር እንደማይችል የገለጸ ቢሆንም በX-Ray inspection system እና Handle held metal detector የፍተሻ መሳሪያዎች ላይ መወዳደር እንደማይችል ባለመገለጹ አነስተኛ ዋጋ ካቀረበው መግዛት ሲገባው ባለመገዛቱና በምላሻቸው እንደገለጹት ለክትትልና ለስልጠና አመቺነቱ ከታመነበት የተመረጠው ድርጅት በቀረበው አነስተኛ ዋጋ እንዲያቀርብ ድርድር መደረግ የነበረበትና ይከው ሁኔታ ተገልጾ በስራ አመራሩ እንዲወሰን ማድረግ ሲገባ ዝቅተኛ ያቀረበው ድርጅት መስፈርቱን አላሟላም ተብሎ ለውሳኔ መቅረቡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

- የቲሸርት ግዥ የተፈጸመው ከአካባቢው ሁኔታ አንጻር የቲሸርቶቹ ናሙና በሰራተኞቹ ተወካይ የተመረጠ በጥራት ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በማኔጅመንቱ ውሳኔ መሰረት የተፈጸመ ግዥ መሆኑን፣
- የቁም ፍሪጅ ግዥን በተመለከተ ለአዋሽ እና ለሚሌ ሰራተኞች ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት እቃውን እንዲያቀርብ ብናሳውቅም በሰጠው የሶስት ቀን ገደብ መሰረት አልወሰዳችሁም በማለት ሰቶክ ላይ የለኝም በማለት ማስረጃ ሰለሰጠን ከቦታው ርቀት አንፃር ባለመድረሳችን ከሁለተኛው አሸናፊ ድርጅት በመሄድ ግዥው ፈጽመናል በማለት ገልጸዋል፡፡

<u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

የቲሸርቱ የግዥ ግዥው ከመፈጸሙ በፊት መስፈርት በማዉጣት ማወዳደር ሲገባው ከዉድድር በኋላ ተጨባጭ ማስረጃ የሌለው በመሆኑ እና በፕሮፎርማው በተሰጠው የስቶክ ቀነ ገደብ መሰረት መገዛት ስለነበረበት ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

## 6) <u>የወጪ ማረጋገጫ ሰነድ፣ እቅድ እና የግዥ ትእዛዝ ሳይኖር የተወራረደ/ወጪ ሆኖ የተከፈለ/ ሂሳብ ብር 3,958,311.60 መኖሩ</u>

<u>**ግኝት**</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገባ ጥንቃቄዎች በሚለው አንቀጽ 9 ስር በተዘረዘረው መሰረት እቃው ወይም አገልግሎቱ እንዲገዛ ትእዛዝ መሰጠቱ፣ እቃው ወይም አገልግሎቱ ተፈላጊውን ባህርያት ያሟላ ስለመሆኑ፣ እቃው ወይም አገልግሎቱ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን መግባቱን፣ የእቃውን ወይም የአገልግሎቱ ትክክለኛነት በሚመለከታቸው ባለሞያዎች የጽሑፍ ማረጋገጫ መሰጠቱ፣ በስምምነት መሰረት ቅድሚያ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ በውሉ ላይ በተጠቀሰው መሰረት መሆኑን፣ ለተገዛ እቃ ወይም አገልግሎት በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጅናል ደረሰኝ መሆኑን እና የእቃው ልዩ ባህሪ ምክንያት ወደ መጋዘን ማስገባት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እቃው መገዛቱ አግባብ ባለው ሰራተኛ ተረጋግጦ ክፍያ ሊፈጸም እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ መሰረት እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ግምገማ ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች ስለመሳተፋቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ስለመኖሩ፣ ወጪው በመመሪያ መሰረት ስለመሆኑ፣ እቃው በገቢ ደረሰኝ ስለመግባቱ ሳይረጋገጥ፣ የቋሚ ዕቃ ግዥ በዕቅድ

ሳይያዝ፣ የግዥ መጠየቂያ ወይም የግዢ ትዕዛዝ እና የወጪ ማስረጃ ሳይኖር በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,958,311.60 ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 30 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## ስጋት

አግልግሎት ላልተሰጠባቸው ወጪዎች ክፍያ ሊፈጸም ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ያደርጋል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

መ/ቤቱ የሚከፍለው የወጪ ክፍያዎች ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ማረጋገጫ ሰነድ መቅረቡ በሚመለከተው አካል መረጋገጥ አለበት፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ

### *የዋና መ/ቤት*

- በቢሾፈቱ እንሰሣት ህክምና ግብርና ኮሌጅ ከጥር14/05/2009-20/05/2009 በተደርገው ግምገማ ላይ 281 የተሳተፉ ሰራተኞች ክፍያው ሊፈጸም የቻለው ከአገልግለቱ አቅራቢ እና ከጠቅላላ አገልግሎት የቀረበውን ማረጋገጫ ተቀብለን መሆኑን እና በማንኛውም ስልጠና ወቅት ተሳታፊዎች የሚቆጣጠሩ ሰዎች ተመድበው የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ ሲደረግ የነበረ እና ማስረጃው ስለሚኖር በአስቸኳይ ተፈልጎ ለኦዲት የሚቀርብ መሆኑን
- የኤዲቶሪያል አባልነት ክፍያ የሚከፈልበት መመሪያ ባለመገኘቱ ለተወሰኑ ወራት ሳይከፈል የቆየ ቢሆንም ከበላይ አመራር በተሰጠ አቅጣጫ ቅሬታ እስካቀረቡበት ድረስ እንዲከፈል ተደርጓል፡፡ ነገር ግን  ለወደፊቱ መመሪያው ካልተገኘ ወደ አመራር ቀርቦ ውሳኔ እንዲያገኝ የሚደረግ ይሆናል በማለት በስራ አመራር ሪፖርት እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ለስልጠና የተከፈለውን በተመለከተ ማስረጃ ተፈልጎ ይቀርባል ቢባልም ከኦዲት መውጫ ስብሰባ ቡኋላም አለመቅሩቡ የኢዲቶርያል አበል ክፍያም ያለመመሪያ መከፈሉ አግባብ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምክንያት አጥጋቢ ሆኑ አላገኘነውም፡፡

### *የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት*

- የዕቅድና የተሃድሶ አመታዊ የስራ እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ተሳታፊዎች አቴንዳስ ከውሎ አበል ጋር ክፍያ ሲፈጸም የታሰረ በመሆኑ በወቅቱ ከመስተንግዶ ክፍያ ጋር ያልታሰረ በመሆኑ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን፡-
- የግዥ መጠየቂያ የቲሸርት ህትመት በእቅድ የተያዘ በመሆኑ ከአመታዊ የግዥ ላይ በእቅድ ተይዞ ለሰራተኞች ደንብ ልብስ የተገዛ ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ አልተያዘለት መሆኑን እና፣
- የመኪና ጥገናው ከአዋሽ የመኪና ጥገና እንዲደረግለት ለቅ/ጽ/ቤቱ ደብዳቤ በጠየቀው መሰረት መሆኑን
- የጀነሬተር ነዳጅ ግዥ በተመለከተ በሚመለከተው የስራ ክፍል እየተረጋገጠ በግዥ መጠየቂያ ፎርም ግዥው የሚፈጸም መሆኑን እና በቀጣይ አሰራሩን በማስተካከል በገቢና ወጪ እንዲሰራለት የምናደርግ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

<u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

የዕቅድና የተሃድሶ አመታዊ የስራ እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ላይ የተሳታፊዎች አቴንዳስና አስፈላጊ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ይቀርባል ቢባልም ባለመቅረቡ፣

የቲሸርት ህትመት በእቅድ የተያዘ ነው ተብሎ የተገለጽው በእቅድ ስለመያዙ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>***የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

በወቅቱ የተገዛው ዕቃ በእቅድ ያልተያዘ ሲሆን ዕቃው ለስራው አስፈላጊ በመሆኑ እንዲገዛ በተደረገው መሰረት ግዥውን ፈፅመናል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 7) <u>ባልተፈቀደ የውጪ ምንዛሬ ተመን መሰረት የተከፈለ የደመወዝ ልዩነት ብር 3,438,587.44 የአገልግሎት ክፍያ በሚል ተመዝግቦ መገኘቱ ፡- (ዶላር 280,412.50)</u>

<u>**ግኝት**</u>

የመ/ቤቱ የባንክ አገልግሎት ክፍያ ወጪ የተመዘገበው ሂሳብ መጠን ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ **በዋና መ/ቤት** ለጅቡቲ ቅ/ፅ/ቤት ሰራተኞች በ2009 በጀት ዓመት የደመወዝ ክፍያ በወቅቱ በነበረው የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት መላክ ሲገባው ወይም በብር በ8.00 ተሰልቶ ይከፈል የሚል ማስረጃ ሳይኖር ደመወዛቸው በብር 8 (ስምንት) እየተሰላ የሚላክ በመሆኑና በወቅታዊ የዉጭ ምንዛሬ ተመን ስሌት መስረት 149,410.93

የአሜሪካን ዶላር መከፈል ሲገባው በ8.00 ብር የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት ብር 429,823.43 በመከፈሉ በልዩነቱ 280,412.50 የአሜሪካ ዶላር በብልጫ የተመዘገበው ሂሳብ ከወቅቱ የምንዛሪ መጠን ለታየው ልዩነት የባንክ አገልግሎት ክፍያ በሚል በመያዙ የአመቱን የደመወዝ ሂሳብ እንዲያንስና የባንክ አገልግሎት ክፍያ በብልጫ የተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* **OFAGF-05.1/25 ቀን 1/05/10 ግኝት ቁጥር 1.5** *ይመልከቱ)*

## ስጋት

የውጪ ምንዛሬ ዶላር የተላከው የደመወዝ ክፍያ የባንክ አገልግሎት ክፍያ በሚል ትክክለኛ ሂሳብ መደብ ካለመመዝገቡም በተጨማሪ በወቅቱ የውጪ ምንዛሬ ተመን መሰረት እየተካፈለ የማይላክ በመሆኑ መ/ቤቱ ያልተፈቀደ ወጪ እንዲዳረግ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

የሚመለከተው የስራ ክፍል በተገቢው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገብ ሊያደርግ የሚገባ ከመሆኑም በተጨማሪ የተከፈለው ክፍያ የውጪ ምንዛሬ ተመን የተፈቀደበት ማስረጃ በማቅረብ በትክክለኛው ተመን መሰረት ሊልክ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ

ባልተፈቀደ የውጪ ምንዛሬ ተመን መሰረት ለጅቡቲ ሠራተኞች የሚከፈለውን በተመለከተ የአገልግሎት ክፍያ በሚል በሂሳብ መደብ በ6256 መመዝገቡ ትክክል ሲሆን፣ የምንዛሬ መጠኑ ከወቅቱ የምንዛሬ መጠን ጋር መስተካከል ባለመቻሉ በአፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር የፈጠረ በመሆኑ ስሌቱን በተመለከተ ማስተካከያ የሚሰራ መሆኑን በስራ አመራር እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ወጪው የደመወዝ ፤የቤት አበል እና የኑሮ መደጎሚያ ሆኖ ሳለ በባንክ አገልግሎት ሂሳብ መደብ 6256 መመዝገቡ ትክክል ባለመሆኑ ምላሹን ያልተቀበልነው ሲሆን፣ በ8 ብር የውጪ ምንዛሬ ተመን መስራቱም አግባብ ባለመሆኑ በአስቸኳይ ከሚመለከተው ክፍል ተጠይቆ መስተካከል ይገባዋል፡፡

## 8) <u>የግንባታ ስራ ቅድመ ክፍያ በትክክል ባለመመዝገቡ ብር 60,741.25 ባልተለመደ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን እንዲታይ ስለመደረጉ</u>

**ግኝት**

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14/8 መሰረት የመደበኛና የካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸሙ ለኮንስትራክሽን ወጪዎች የክፍያ ምስክር ወረቀት መቅረቡንና በትክክል መሰላቱን መረጋገጥ እዳለበት በሚያዘው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ **ዋና መ/ቤት** በቀን 28/2/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 28140 ለሚሌ ቅ/ጽ/ቤት የቢሮና መንገድ ስራ ግንባታ ቅድመ ክፍያ የተከፈለ ብር 1,336,307.63 ሆኖ ሳለ በክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ በስህተት በብር 1,397,048.88 በመወራረዱ ምክንያት በልዩነት ብር 60,741.25 ተሰብሳቢ ሂሳብ ባልተለመደ ሂሳብ ሚዛን እንዲታይ ተደርጓል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* **OFAGF-05.1/25 ቀን 01/05/10 ግኝት ቁጥር 1.6 ላይ** *ይመልከቱ)*

**ስጋት**

ለቅድመ ክፍያ ሂሳቦች በክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ በትክክለኛው እየተመዘገበ የክፍያ ሂሳቡ የማይቀናነስ ከሆነ ሂሳቡን ተቀባይነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

መ/ቤቱ የሚዘጋጀው የክፍያ ምስክር ወረቀት የቅድመ ክፍያ ሂሳብ መሰረት ተቀናሽ እንዲደረግ የሚመለከተው ክፍል ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡አሁንም ለሂሳቡ ማስተካከያ ምዝገባ ሊከናወንለት ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

በሚቀጥለው የክፍያ ምስክር ወረቀት እንዲስተካከል እናደርጋለን በማለት በስራ አመራር ምላሽ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 9) <u>ከመመሪያው ውጪ የተከፈለ የዉሎ አበል ብር 313,962.59 መኖሩ</u>

**ግኝት**

ሰኔ ወር 2004 ዓ/ም በወጣው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ወሎ አበል የአከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 8 (1ሀ-ሐ) ላይ እንደተመለከተነው ማንኛዉም የመንግስት ሠራተኛ ለስራ ጉዳይ ከመደበኛ የስራ ቦታ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለሚያደርገዉ እንቀስቃሴ ከጠዋቱ አንድ ስዓት

በፊት የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለቁርስ፤ ሄዶ ዕለቱን ከስድስት ሰዓት ተኩል በኋላ የሚመለስ ከሆነ ለምሳ እንዲሁም ሄዶ ከምሽቱ ሁለተ ስዓት በኋላ የሚመለስ ከሆነ የእራት እንድሚታሰበልት መመሪያዉ ያዛል፤ በዚህ መሰረት መ/ቤቱ የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት፤ ሲደረግ ያለአግባብ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለቀጠራቸው ባለሙያዎች እና ከሚሰሩበት መ/ቤት ሠራተኛ መሆናቸውንና የወር ደመወዝ መጠን የሚገልፅ ደብዳቤ ሳይኖር እንዲሁም ሠራተኞቹ ለስራ የተጓዙት ሞጆ ሆኖ ሳለ የአበል ክፍያው አዳማ እንደሄዱ ተደርጎ በመከፈሉ የውሎ አበል መመሪያ ያልተከተለ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 313,962.59 ያለ አግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 31 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## <u>ስጋት</u>

የመንግስት ህግ እና መመሪያ ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ላልተገባ እና ያለአግባብ  ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡አሰራሩ ልብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

## <u>የማሻሻያ  ሀሳብ</u>

በጥቅማጥቅም መመሪያ መሰረት ለተፈቀደላቸው የስራ መደቦች ብቻ መከፈል አለበት፡፡ በብልጫ እና ባልተፈቀዱ የስራ መደቦች የተከፈሉ ጥቅማጥቅሞች ብር13,900 ከሰራተኞቹ ተመላሽ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## <u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>

### <u>*አዲስ አበባ ሬርፖርት*</u>

በሲቪል ሰርቪስ መመሪያው ላይ በግልጽ ሞጆ በሚል የውሎ አበል ታሪፍ ስላልተቀመጠ በአቅራቢያው ባለው ከተማ ክፍያ ልንፈጽም የቻሉ መሆኑን እና በእላፊ የተከፈለው የውሎ አበል ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### <u>*ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት*</u>

ከዋናው መ/ቤት አዲስ ቅጥር ፈፅመው ወደ ቅ/ጽ/ቤታችን ከመጡ በኋላ ቅ/ጽ/ቤት ላይ የማስተዋወቂያ ስልጠና  ለመስጠት እና ወደ የጣቢያው እስኪመደቡ ድረስ የተከፈለ የውሎ አበል መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### <u>*ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት*</u>

ለወደፊቱ ምንም አስቸጋሪ ቢሆንም ከሚነሱበት አካባቢ የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸውንና የደሞዛቸውን መጠን የሚገልፅ ደብዳቤ ይዘው እንዲመጡና የዉሎ አበል መክፈያ ፎርማት እንዲሞሉ የሚደረግ መሆኑ እና የዉሎ አበል መክፈያ ፎርማት አለመጠቀማችን እንደክፍተት ተቀብለነው በቀጣይ በመመሪያው መሰረት የውሎ አበል ጥያቄን የምናስተናግድ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 10) <u>***መመሪያን መሰረት ያላደረገ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር ብር 318,346.42 መኖሩ***</u>

### <u>ግኝት</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የትርፍ ስዓት ክፍያና የማካካሻ እረፍት አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 104/2007 አንቀፅ 16 ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ በተገለፀው መሰረት የትርፍ ስዓት ስራ የማይከናወንባቸው የስራ መደቦች ወይም የስራ ዝርዝር በተላከው ደብዳቤ መሰረት ተግባራዊ እዲደረግ ያዛል፡፡ በተጨማሪ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ/ም በወጣ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፤ስለክፍያው መጠን እና የማካከሻ ዕረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ አንቀፅ 10.2 አንድን ሰራተኛ በወር ዉስጥ እጅግ ቢበዛ ከ60 ሰዓት በላይ ትርፍ ሰዓት ማሰራት እንደማይቻል በሚደነግገው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የተሰራ ስራ ሳይገለጽ፣ በሚመለከተው የስራ ክፍል ሳይፈቀድና ሳይጸድቅ በመደበኛ የሰራ ሰዓት ሊሰሩ የሚችሉና የትርፍ ሰዓት ላልተፈቀደ የሥራ መደቦች የተከፈለ ትርፍ ስዓት ***በጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 318,346.42 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.22/4 ቀን 06/07/10 ግኝት ቁጥር 2.8 ላይ ይመልከቱ)*

### <u>ስጋት</u>

የትርፍ ስአት ክፍያዎች መመሪያውን ተከትሎ የማይፈጸሙ ከሆኑ የመንግስት ገንዘብ የትርፍ ሰዓት ስራ ምክንያት በማድረግ ላልተገባ ክፍያና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላ፡፡

### <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፤ስለክፍያው መጠን እና የማካከሻ ዕረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡ በተጨማሪ ከመመሪያ ከሚፈቅደው የሰራ መደብ እና በወር ከተፈቀደው የትርፍ ሰዓት በላይ የተከፈለ

ሂሳብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ በቀሩት ወራትም ተመሳሳይ ስህተት ተፈጽሞ ሊሆን ስለሚችል በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

- ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ህግና መመሪያውን ተከትሎ ስራው ተሰርቷል ባንልም በቅርንጫፉ ትርፍ ሰዓት ስራዎች ሲሰሩ የተቋሙ የትርፍ ሰዓት አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 104/2007 መሰረት አድርገን እየሰራን ሲሆን፣ የትርፍ ሰዓት የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ፣ለ፣ሐ፣መ) በተቀመጠው መሰረት በድንገት የሚከሰቱ ልዩ ሁኔታዎችን በሁሉም ስራ ክፍሎች ተረባርቦ ስራውን ማቀላጠፍ ስለሚያስፈልግ ከትርፍ ሰዓት ውጪ ሌላ አማራጪ እንደሌለም በተቋም ደረጃ የሚታወቅ መሆኑን፤
- ለቅርንጫፉ የተሰጠውን አላማ ለማሳካት በመደበኛ የሰራ ሰዓት ሊጠናቀቅ የማይችል ስራ ስለሚገጥመን እና ባለው የሰው ሃይል ለማሰራት በክፍሉ ያሉ ሰራተኞች ለመደቡ ከተፈቀደው መደብ ልክ የተሟሉ ባለመሆኑ ስራዎችን ለመስራት አስቸኳይና የተገደበ ጊዜ ስለሚሰጥና በወቅቱም በእኛ ቅርንጫፍ ሁኔታ የ24 ሠዓት የማያቋርጥ አገልግሎት ከኮንትሮባንድ ቁጥጥሩ ጋር ቀጥተኛ የሆነ መረጃ ስለሚሰጡና ስለሚቀበሉ ቀጥታ ከትራዚት ስራው ጋር በመቀናጀት ኮንትሮባንድ በስውር ወደ ሃገር ውስጥ እንዳይገባና እንዳይወጣ የመከታተልና የማረጋገጥ ስራ እሁድና ቅዳሜ እንዲሁም በበዓላት ቀን ማሰራት አስፈልጓል ለምሳሌ ትራንዚቱ ባለበት ሰዓት ሁሉ ትራንዚት ስራ የሚያከናውኑ ስራ ክፍሎች የሚኖሩ በመሆኑን በተቋም ደረጃ የሚታወቅና የትርፍ ሰዓት ክፍያው ከህግና መመሪያ ውጪ የተሰራ አለመሆኑን
- በመመሪያ 104/2007 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ፣ለ፣ሐ፣መ) መሰረት በትርፍ ሰዓት እንዲሰራ ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ ጀነሬተር ኦፕሬተር አንድ ሰራተኛ ብቻ ስላለ እና ጀነሬተሩ ለ24 ሠዓት አገልግሎቱ ዝግጁ ስለሆነ ፤ በከፍተኛ ሁኔታ መጠበቅ ያለባቸው የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች በግቢው ውስጥ ስላሉ ፤ የመረጃ ቴክኖሎጅ ድጋፍ ሠጪ ስራ የኤሌክትርሻን ስራ የስምሪት ስራ የ24 ሰዓት ትራንዚት አገልግሎት ሲሰጥ ባለው የሰው ሃይል መሸፈን ባለመቻሉ በየቀኑ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ስላለው የስራ ክፍሎችም ክፍት ሆነው የ24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት ስላለባቸው

- በተጨማሪም በትርፍ ሰዓት ስራው ላይ ምን እንደተሰራ በቅፁ ላይ አልተለጸም ለሚለው ስራ ክፍሎች እሁድና ቅዳሜ እንዲሁም የበዓላት ቀን መደበኛ የሆነውን ስራ በቀጣይነት የሚሰራ ስለሆነ የስራ ክፍሉ ሲገለፅ ምን እንደሚሰራ ስለሚታዎቅና ምክንያቱ በቅፁ ላይ ስለተቀመጠ አሻሚ ስላልሆነ ትኩረት ሰጥተን አለመሙላታችን
- በመመሪያ ቁጥር 104/207 አንቀፅ 15 መረት የትርፍ ሠኣት ስራ ገደብን መሰረት አድርገን በወሩ ወስጥ አንድ ሰራተኛ በቀን በተሰጠው ገደብ ልክ ሰርቶ አጠቃላይ ሲደመር ከ60 ሊበልጥ የሚችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

የትርፍ ሰዓት ክፍያ የተከፈለው የሰው ሃብት ስራ አመራር፣ መረጃ ቴክኖሎጂ፣ ህግ ማስከበር፣ ዲቾቶ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ፣ የሪከርድ ስራ አመራር፣ የሪከርድ ስራ አመራር ድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት፣ንብረት አስተዳደር፣ የትራንስፖርት ፀሃፊ፣ ን/አስ/ጠ/አገልግሎት፣ ጠ/አገልግሎት የተከፈለ በመሆኑ በመደበኛ ሰዓት ሊከናወኑ የሚችሉ እና የተሰራው ስራ ሳይኖር እና በሚመከተው የሰራ ክፍሎች በመመሪያ መሰረት ሳይታቀዱና ሳይፈቀዱ የተከፈሉ በመሆናቸው የተሰጠው ምላሽ አልተቀበልነዉም፡፡ በተጨማሪም ስራው በግድ በሌሎች ክፍሎችም ተደርቦ መሰራት አለበት ከተባለ ከባለስልጣኑ መ/ቤት ጋር በመነጋገር በልዩ ሁኔታ ማስፈቀድ ሲገባ የተለያየ ምክንያት በመስጠት ለሁሉም ሰራተኛ በሚመስል መልኩ የትርፍ ስዓት ክፍያ መፈጸም ተገቢ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምክንያት አጥጋቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## 11) <u>በቅ/ፅ/ቤቱ በጀት መገዛት የሌለበት እንዲሁም ለቅ/ጽ/ቤቱ የሚሰጠው ጥቅም ወይም አገልግሎት ግምት ውስጥ ሳይገባ በብር 116,043.96 የተፈጸመ ግዥ ስለመኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በቅ/ጽ/ቤቱ የአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥዎች በጀት ተይዞለት እና ለመ/ቤቱ አላማ የሚውል መሆኑን ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገበት በከፍተኛ ደረጃ ውጤት ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በመደበኛ የወጪ በጀት ተይዞለት መገዛት ሲኖርበት ያለ በጀት የተገዛ እና ለመንግስት ስራ ተገቢ መሆኑን የተፈቀደበት ሰነድ ሳይኖር በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ በብር 116,043.96 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 32 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## ስጋት

ግዥ በሚፈፀምበት ወቅት ለቅ/ጽ/ቤቱ የሚሰጠው ጥቅም ታሳቢ ተደርጎ የማይገዛ ከሆነ የመንግሰትን ሀብት ለማጭበርበር እና ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡አሰራሩም ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

ለቅ/ጽ/ቤቱ የሚያስገኘው ጥቅም እና ተገቢነት በማረጋገጥ እንዲሁም የተያዘ በጀት መኖሩን በሚመለከተው ሀላፊ ሲረጋገጥ ግዥው መፈጽም አለበት፡፡ ያለአግባብ በቅ/ጽ/ቤቱ ሂሳብ የተገዛ ሸቀጥም ሆነ ንብረት ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶች ስራ አመራር ምላሽ

### *የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት*

- ለሥራ አስኪያጅ የተገዛ ሞባይል ምክንያቱ ከቦታው ርቀት ከመሆኑ አንጻር መረጃ ለመላላክ እና አብዛኛውን ኢንተርኔት አክሰስ ስለሌለ የአሲኩዳና የቪዲዲ የመሳሰሉትን መረጃዎችን ለመለዋወጥ ይረዳ ዘንድ የተሻለ ሞባይል የተፈጸመ ግዥ መሆኑን፡፡
- የካውያ ግዥን በተመለከተ መ/ቤቱ ካለበት በረሃማነት የተነሳ እንግዶች ለስራ ጉዳይ በሚመጡበት ጊዜ ለማረፊያ /ገስት ሀውስ/ አገልግሎት የሚውሉ አንሶላዎች ለመተኮስ የምንጠቀምበት ስለሆነ ግዥው ሊፈጸም ችሏል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

ለሥራ አስኪያጆች ተገዛ የተባለውን በተመለከተ ቀደም ሲል ሁለት ሞባይሎች ለኃላፊዎች የተገዙ ቢሆንም በዝዉዉር የለቀቁ አመራሮች ንብረት እንዲመልሱ በማድረግ መጠቀም ሲቻል ተመላሽ እንዲያደርጉ ባለመደረጉና የወጪ ቅነሳ ግምት ዉስጥ ያላስገባ በአዲስ መልክ መገዛቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ምላሹ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

### *የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት*

ለቅ/ጽ/ቤቱ መዝናኛ ክበብ የተገዛ ሸቀጥ ሲሆን በወቅቱ ስራውን ሲመሩ የነበሩ አመራሮች መልስ ሊሰጡበት ይገባልበማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

በወቅቱ ስራውን ሲመሩ የነበሩ አመራሮች መልስ ሊሰጡበት ይገባል ተብሎ የተሰጠ ምላሽ አግባብ ባመሆኑ የጽ/ቤቱ ሰነድ ለኦዲት አቅርቦ በቀረበው አስተያየት ትክክለኛነት በማረጋገጥ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

12) **የብር 352,002.47 የያዘ የወጪ ሂሳብ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ስለመሆኑ**

**ግኝት**

በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል የተመዘገቡት ሂሳቦች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በተሞከረበት ወቅት ለኦዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት የወጪ ሂሳብ ማስረጃዎች መካከል **በጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት** በስድስት (6) የወጪ ማስመስከሪያ በድምር ብር 352,002.47 የሚያሳይ ማስረጃዎች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.22/4 ቀን 06/07/10 ግኝት ቁጥር 2.10 ላይ ይመልከቱ)*

**ስጋት**

ለኦዲት የተጠየቁ ሰነዶች ለኦዲት የማይቀርቡ ከሆኑ በሂሳብ ምዝገባ የተመዘገቡና ሪፖርት የተደረጉ የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ለኦዲት ያልቀረቡት ማስረጃዎች ተፈልገው ትክክለኛነታቸው በውስጥ ኦዲት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራሩ ምላሽ**

የውስጥ ኦዲት በሚሰሩበት ሰዓት ሰነዶቹ ከመበታተናቸው የተነሳ በቀላሉ ማግኘት ስላልቻልን በመሆኑ መረጃውን ፈልገን የምናቀርብ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

13) **ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 2,206.60 ስለመኖሩ**

**ግኝት**

የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባወጣው ከመደበኛ የስራ ጊዜያቸው ውጭ በዘላቂነት አገልግሎት መስጠት በሚያስገድዱ የሾፌር መደቦች ላይ ለሚሰሩ ሾፌሮች አበል አከፋፈል በተመለከተ በቁጥር ፐ/ስ/ስ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ13/46/1010 በቀን 19/05/2008 ዓ.ም በተሻሻለው መመሪያ እና ከጥር1/2008 ጀምሮ ቀደም ሲል በቀን 19/05/2007 በሲ.ሰሚ30/ጠ13/49/1056 በተላለፈው መመሪያ ላይ የተገለጹ ሌሎች ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚሁ መሰረት

አበሉ በቁርጥ እንዲከፈልና አበሉ ግን ግብር የሚከፈልበት ሆኖ በተሻሻለው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ሰራተኞችና ሀላፊዎችን ከመደበኛ ስራቸው ውጪ ለሚያገለግሉ ሹፌሮች በቁርጥ አበል መክፈል ሲገባው፤ በትርፍ ሰዓት ክፍያ በመክፈሉ ***በምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 2,206.60 መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ ታይቷል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.1/20 ቀን 10/02/10 ግኝት ቁጥር 3.3 ላይ ይመልከቱ)*

**ስጋት**

ተሻሽሎ በቀረበው መመሪያ መሰረት በቁርጥ አበል ክፍያው የማይፈጸም ከሆነ መንግስት ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርገው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

የሚመለከተው ስራ ክፍል ሃላፊ ለከፍተኛ አመራሮች፣ ስራ ሃላፊዎችና ለሰራተኞች በመደበኛነት የሰርቪስ አገልግሎት ለሚሰጡ ሹፌሮች ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ መሰረት ክፍያ መፈጸሙን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ያለአግባብ የጠከፈለው አበልም ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

የትርፍ ሰዓት ክፍያው የተፈጸመው በተቋሙ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ19/1 እና አንቀጽ 20/2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 104/2007 መሰረት በመሆኑ ከመመሪያ ውጪ ተከፈለ የተባለውን አስተያየት አንቀበለውም፡ ወደፊትም የተለወጠ መመሪያ ከዋናው መ/ቤታችን እስካልመጣልን ድረስ የምንሰራው በዚሁ መመሪያ መሰረት ሲሆን የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስተር አወጣ የተባለውን መመሪያ በዋናው መ/ቤታችን በኩል ካልመጣልን መመሪያውን ቀይረን ሚኒስቴር የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አወጣው በተባለው መመሪያ ለመስራት ስልጣን የለንም፡ እየሰራንበት ያለውን መመሪያ እንዲቀየር ማድረግ ከተቻለ መመሪያውን ላወጣው አካል አቅርቦ ማስቀየር እንጂ በተሰጠን ስልጣን በወጣ መመሪያ መሰረት ስራ ከመመሪያ ውጪ እንደተሰራ ተደረጎ መቅረቡና የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲመለስ አስተያየት መቅረቡ ከህግ አንጻር ተቀባይነት አለው ብለን አናምንም በማለት ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

ስራው በሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የወጣ አገር አቀፍ መመሪያን አንቀበልም ማለቱ ለህግ ተገዢ አለመሆን በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይሁን እንጂ ቅ/ጽ/ቤቱ እንደገለጸው የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ ሾፌሮች በተመለከተ በወጣው መመሪያ መሰረት እንዲሰራ የባለስልጣኑ መ/ቤት ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤ/ቶች ሊያሳውቅ ይገባል ፡፡

## 14) <u>ያለአግባብ ላልተሰራበት እና በዝውውርና ከስራ ለተሰናበቱ የተከፈለ ደመወዝ ብር 46,370.41 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በቅ/ጽ/ቤቱ አማካኝነት የሚፈጸሙ የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ10 ን.አ 5 በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ምክንያት ከስራ የተለዩት ሠራተኞችን ከደመወዝ መክፍያ ዝርዝር ውስጥ ስለመውጣታቸው እየተረጋገጠ ክፍያ መፈጸሙን እንዲሁም አንቀጽ12/ ሀ-ሐ/ መሰረት የመ/ቤቱ የስራ ክፍሎች የክፍሉ ሰራተኞች በስራ ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ወር በገባ በ20ኛው ቀን ውስጥ የስራ ክፍሎቹ ማሳወቃቸውን እና ሳይረጋገጥ ክፍያ የማይፈጸም መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ሃያ አምስት (25) ቀናት ሰርተው ሳለ የሙሉ ወር (30) ቀናት ደመወዝ የተከፈለ በመሆኑ፣ ስራ ለለቀቁ ሰራተኛ ላልሰሩበት የተከፈላቸው በመሆኑ፣ በዝዉዉር ለለቀቁ የጽ/ቤቱ ሰራተኞች ያለ አግባብ የተከፈለ በመሆኑ፣ እንዲሁም መከፈል ከሚገባው የተጣራ ደመወዝ ክፍያ በላይ የተከፈለ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምር ብር 46,370.41 አላግባብ የተከፈለ የደመወዝ ክፍያ መኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 33 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያላግባብ ክፍያ ሲፈጽሙ መንግስትን ላልተገባ ወጪ ከመዳረጉም በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ሊያደርገው ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

በየቅ/ጽ/ቤቶቹ የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሰራተኞቹ ላልሰሩበት ቀናት ክፍያ እንዳይፈጸም ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች አስቀድሞ ለፋይናንስ ክፍል መረጃው

እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

አንዱ ሰራተኛ ከሀገር ወጥቷል/አሜሪካ ገብቷል/ ማግኘት የሚቻል ባይሆንም ጥረት ይደረጋል፤ ሌላው ከአኒሳ መሀመድ ግን መሰብሰብ የሚገባው ገንዘብ የሚሰበሰብ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የጅማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ያለ አግባብ የተከፈለው የደሞዝ ክፍያ ተመላሽ እነዲሆን ይደረጋል፡፡ ለወደፊቱም ከሰው ሀብት ወይም ከየስራ ክፍሉ ማረጋገጫ ሳይሰጥበት የደሞዝ ክፍያ እነዳይፈፀም ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***<u>የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- በስራ ገበታው ላይ ላልተገኘ ሰራተኛ የተፈጸመው የደመወዝ በስራ ስህተት የተፈፀመ በመሆኑ ገንዘቡን ተመላሽ እንደሚያስደርጉ፣
- የትርፍ ሰዓት ክፍያን ቀደም ሲል ጀምሮ የትርፍ ሰዓቱ ለብቻው ከተሰላ በኃላ ታክሱ ተቀናንሶ በተጣራው ደመዎዝ ላይ ተደምሮ ነበር የሚሰራው በዚህም መሰረት በታክስ አቀናነሱ ላይ ልዮነት በመፈጠሩ ሲሆን በቀጣይ ከሰራተኞቹ የሚሰበሰብ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ሰራተኞች ከቅርንጫፍ በዝውውር ወደ ሌላ ቅርንጫፍ ሲሄዱ የተከፈለ ሲሆን መከፈል ያለበት እኛ ቅርንጫፍ በስራ ላይ እስከ ቆዩበት መሆን እንዳለበት አይተን አላግባብ የተከፈለ መሆኑን ተረድተናል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 15) <u>የተፈቀደበት መመሪያ ሳይኖር እና ያለአግባብ የተከፈለ የወሮታ ዉሎ አበል ብር 29,384.00 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

የህገ ወጥ አቃዎች መረጃ አሰጣጥ፤አያያዝ፤አመዘጋገብ፤እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 78/2004 አንቀጽ 18 እስከ 24 ንኡስ አንቀጽ ሐ መሰረት ዕቃዉ የተያዘዉ በህግ አካል ከሆነ በተጠቀሰው ንኡስ አንቀጽ ባለው የስሌት ተመን መሰረት

**የወሮታ ክፍያ ለተቋሙ እንደሚከፈል እንዲሁም አንቀፅ** 16(1) **ለባለስልጣኑ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ያለ ምንም ጥቆማ ሕገ ወጥ ዕቃ ከተያዘና ለባለስልጣኑ ገቢ ከተደረገ ጠቋሚው፣ ያዡ፣ ትብብርና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ በዚህ መመሪያ መሰረት የወሮታ ክፍያ እንደሚከፈላቸው በሚያዘው መሰረት ቅ/ጽ/ቤቱ የወሮታ ክፍያው በማስረጃዎች በመመስረት እና በትክክለኛው የሰሌት መጠን እየከፈለ መሆኑን ለማረጋገረጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የወሮታ አበል ክፍያ የሚፈፀምበት ህገ ወጥ እቃዎች ይዘው ለሚመጡ የፌዴራል እና ክልል ፖሊስ አባላት የፌደራል ፖሊስ በፌዴራል ፖለስ ጽ/ቤት የክልል ፖሊስ በክልል ፖሊስ ጽ/ቤት የዉሎ አበል መከፈል ሲገባቸው፣** ***በሚሌ ቅ/ጽ/ቤት የዉሎ አበል እንዲከፍል የተፈቀደበት መመሪያ ሳይኖር ብር*** 9,072.00 ***እና ከሚመለከተው አካል የገበያ ጥናት ዋጋ በቀረበ ማስረጃ መሰረት በማድረግ መከፈል የነበረበት የወሮታ ክፍያ በብልጫ የተከፈለ ብር*** 20,312.00 ***በመኖሩ በድምር ብር*** 29,384.00 ***የተከፈለ የወሮታ ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡*** (***ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር*** OFAGF-05.21/3 ***ቀን*** 06/07/10 ***ግኝት ቁጥር*** 2.6 ***እና*** 2.7 ***ላይ ይመልከቱ***)

**<u>ስጋት</u>**

**ወሮታ ለሚከፈልበት የህገ ወጥ እቃዎች ላመጡ የዉሎ አበል እንዲከፍል የተፈቀደበት መመሪያ ሳይኖር እና በትክክል ተሰልቶ የማይከፈል ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊከፈል የሚችል ከመሆኑም ባሻገር ለብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡**

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

**ቅ/ጽ/ቤቱ የሚፈጽማቸው የዉሎ አበል ክፍያዎች የተፈቀዱ እና ህግን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው በሚመለክተው የስራ ክፍል ማረጋገጥ ይኖረበታል፡፡ አሁንም ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡**

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

- **በፌ/ፖ/ስም ዝርዝር ጋር በጥምረት ሥራወን በተለያዩ ግዜያት ኮንትሮባንድን ለመያዝ ወይም አጅበው ሲመጡ የውሎ አበል ተሰርቶ መ/ቤታችን ሰራተኞች በድምሩ ብር** 5,833.00 **ክፍያ የተፈጸመው ለመ/ቤታችን ሰራተኞች መሆኑን እና ለፖሊሶች አበል የተከፈለው ብር** 5,668.00 **ብቻ መሆኑ፣**

- ከመድሃኒት የዋጋ ጥናት ጋር በተያያዘ ጠቋሚው ቅሬታ አቅርቦ መስሪያ ቤቱ በሰየመው ኮሚቴ አማካኝነት በአካባቢው ባሉት መድሃኒት ቤቶት ጥናት ተደርጎ በቀረበው ጥናት መሰረት ስሌቱ የተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

- የተዘረዘሩ ሰራተኞች የጽ/ቤቱ ሰራኞች መሆናቸውንና የስራ መደባቸው የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡
- በመድሐኒት ምግብ ቁጥጥር ኤጀንሲ በቀረበ የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት የወሮታ ክፍያ መከፈል ሲገባው በአካባቢው ባሉት መድሀኒት ቤቶች ዋጋ የጠከፈለ ነው የተባለው በመመሪያው መሰረት ባለመሆኑ ምላሽ አልተቀበልነዉም፡፡

**16) <u>ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የስልክ እና የመዘዋወሪያ አበል ብር 41,100.00 መኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የልዩ ልዩ አበሎችና የስራ ወጪ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 109/2007 አ/ም በተፈቀደው ጥቅማጥቅም መሰረት የተፈቀደላቸው የስራ መደቦች ብቻ የሚከፈል መሆኑን እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመርያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት ከተፈቀደለት የገንዘብ ጣሪያ ሳይልፍ ከተከፈተለት የገንዘብ ማስተላለፊያ የባንክ ሂሳብ በቼክ ወይም በገንዘብ ማዘዋወሪያ ትዕዛዝ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ክፍያ እንደሚፈጽም በሚያዘው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ያልተፈቀዳላቸው የሰራ መደቦች እና ለተፈቀደላቸው የስራ መደቦች በብልጫ ከደመወዛቸው ጋር በመደመር የተሰጠ እና ከተፈቀደለት የስልክ አጠቃቀም ተመን በላይ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 41,100.00 ከመመሪያ ውጪ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 34 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

የመንግስት ህግ እና መመሪያ ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ላልተገባ እና ያለአግባብ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡ አሰራሩ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

በጥቅማጥቅም መመሪያ መሰረት ለተፈቀደላቸው የስራ መደቦች ብቻ መከፈል አለበት፡፡በብልጫ እና ባልተፈቀዱ የስራ መደቦች የተከፈሉ ጥቅማጥቅሞች ከሰራተኞቹ ተመላሽ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ

### *የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት*

- ለተለያዩ ቡድን አስተባባሪዎች የስልክ አበል የተከፈለው ለስራው አስፈላጊነቱ በማኔጅመንት ታይቶና ታምኖበት የተከፈለ ሲሆን ለዚህም ማኔጅመንት አባላቱ በመውጫ ፕሮግራማችሁ ላይ ካቀረበው ውጪ ሌላ ማስረጃ የለም፡፡
- አንድ ሰራተኛ በደረጃ እድገት ምክንያት በቀረበ ቅሬታ ሲታይ ቆይቶ በመፅደቁ ወደ ኋላ እድገቱ መሰጠት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ስለተሰጠ እንጅ በወቅቱ የመዘዋወሪያ እና የስልክ አበሉ ከተፈቀደበት መደብ ላይ እየሰሩ በመሆኑ የተከፈለ ሲሆን፣ ለዚህም የቅሬታው ውሳኔ እና ቅሬታው ታይቶ እስከሚያልቅ በወቅቱ ስራ መደቡ ላይ ለመቆየታቸው የተሟሉ ማስረጃዎች አሉ ለእናንተም በወቅቱ ቀርበዋል፡፡

## የኦዲተሩ አስተያየት

በመመሪያው ከተፈቀደው ጥቅማጥቅም ዉጭ ምንም ዓይነት የህግ መሰረት ሳይኖረው የበጀት መዝግያ በመሆኑ ብቻ በገንዘብ የተከፈለ የሞባይል ሂሳብ መሆኑን አግባብነት የለዉም፡፡ በደረጃ እድገት ምክንያት ቅሬታ ላይ የነበረ ተብሎ የተመለሰ ከፒሲኤ ወደ ሀብት አስተዳደር ቡድን አስተባሪ በማደጉ በቅሬታ ምክንያት ሳይከፈለው የቆየ ለስራ መደቡ የተፈቀደ ደመወዝ የተከፈለ በመሆኑና ያደገበት የስራ ቦታ የሞባይል ጥቅማጥቅ የሌለው በመሆኑ ያለአግባብ የተከፈለ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

### *የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት*

በብልጫ የተጠቀሙት የስልክ ወጪ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች የመስመር ስልክ አገልግሎት በመ/ጣቢያ ካሉት ጋር ለስራ ግንኙነት የስልክ ምልክት (miss call) ሲያደርጉ ደውለን የምናገኝበት በመሆኑ የተተመነው ዋጋ ለስራ ከምናደርገው ግንኙነት አንጻር አነስተኛ በመሆኑ ልዩነት ሊታይ ችሏል፡፡ ቢሆንም ከተተመነው ወጪ በብልጫ የተጠቀሙትን ተመላሽ እንዲያደርጉ ደብዳቤ እየጻፉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

ከዋና መ/ቤት በመጣ መመሪያ መሠረት የተከፈላቸው በመሆኑ የእርምት ውሳኔ በድብዳቤ ጠይቀን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን በማለት ገልጸዋል፡፡

## 17) ከዋናው መ/ቤት ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት ስራ ለመጡ ሰራተኞች ከውሎ አበል መመሪያ ውጭ ብር 64,600.00 የተከፈለ መሆኑ

***ግኝት***

የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመርያ ሰኔ/2004ዓ.ም በወጣው በክፍል 2 አንቀፅ 5/1/ሀ-ሰ/ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልላዊ ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንዳንዱ ቀን በመመርያው ክፍል 2 አንቀፅ5/1/ሀ-ሰ/ ባለው ሁኔታ መከፈል እንዳለበት መመርያው ይደነግጋል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት የውሎ አበል ክፍያ እየተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ለኢንቨስቲጌሽን ኦዲት ስራ ብዛታቸው 7 የሆኑ ሰራተኞች ለ10 የስራ ቀናት በጋምቤላ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንዲሰሩ ከባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት የተላኩ ቢሆንም የዋናው መ/ቤት የግዢ ቡድን አስተባባሪ ከደንብና መመሪያ ውጭ የአልጋና የምግብ ክፍያ ሆቴል ተይዞ እንዲፈጸምላቸው ተብሎ ፋክስ በተደረገ ደብዳቤ መሰረት ሆቴሎችን አወዳድረው ***በጅማ ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 64,600.00 ተገቢ ያልሆነ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.14/5 ቀን 7/06/10 ግኝት ቁጥር 2.1 ላይ ይመልከቱ)*

***ስጋት***

ቅ/ጽ/ቤቱ ከዋና መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ለስራ የተላኩ ሰራተኞች ከዋና መ/ቤት በስራ ለሚቆዩበት ቀናት የውሎ አበል እንዲከፈል መደረግ ነሲገባው አልጋና ምግብ በሆቴል ተይዞ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ተገቢ ባልሆነ መልኩ ሊባክን ይችላል፡፡ የዚህ አይነት አሰራርም በኃላፊነት ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

***የማሻሻያ ሀሳብ***

በውሎ አበል መመሪያ መሰረት እና ሰራተኞቹ ከተላኩበት ከዋና መ/ቤት የውሎ አበል የተከፈላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጫ መኖሩ ሊረጋገጥ የሚገባ ሲሆን ወጪ የሆነው ሂሳብ

ተጣርቶ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከመንግስት ደንብ ውጪ የሆቴል መስተንግዶ እንዲደረግ ባዘዙት የስራ ኃላፊ ላይም አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

ቅ/ጽ/ቤቱ ክፍያውን ለሆቴሉ ሲፈጽም በአገልግሎት ግዢ ሲሆን ትዕዛዙም የተላለፈው ከዋና መ/ቤት ስለሆነ በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት ሆቴሎችን አወዳድረን በኮሚቴ በመስራት ጨረታውን ላሸነፈና አገልግሎቱን ለሰጠው ሆቴል ክፍያውን የፈጸምን ቢሆንም በኦዲት ግኝቱ ክፍያው መፈጸም የነበረበት በውሎ አበል የክፍያ መመሪያ ብቻ መሆን ይኖርበታል በሚለው አካሄድ የጋራ መስማማት ላይ ስላልደረሰን በልዩነት እንዲያዝልን ሲሉ በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከዋና መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የተላኩት ሰራተኞች ለመስክ ስራ እስከሆነ ድረስ ቅ/ጽ/ቤቱም ሆነ ዋና መ/ቤቱ ወጪያቸውን መሸፈን ያለባቸው በውሎ አበል መመሪያ መሰረት ሲሆን፣ ቅ/ጽ/ቤቱ ከዋና መ/ቤት የግዢ ቡድን አስተባባሪ ወደ ጋምቤላ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ለተላኩት ሠራተኞች ሆቴል እንዲያዝላቸው፣ የሆቴል አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን አወዳድሮ ላሸነፈውና አገልሎቱን ለሰጠው ድርጅት የአኮሞዴሽን ወጪውን እንዲሸፈን ብሎ ባስተላለፈው ደብዳቤ መሰረት የሰራተኞቹ ወጪ እንዲሸፈን መደረጉ ከውሎ አበል መመሪያ አንጻር ተገቢ ባለመሆኑና ቅ/ጽ/ቤቱም መመሪያን የሚቃረን ትዕዛዝ የማስተናገድ ግዴታ የሌለበት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

## 18) **መመሪያ ከሚፈቅደው ውጪ የተፈጸመ የጥቆማ አበል ክፍያ ብር 18,786,184.38 መኖሩ**

**ግኝት**

የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 78/2004 ክፍል አምስት አንቀፅ 29 ን.አ 1 እና 2 መሰረት ህገ ወጥ ዕቃ ተይዞ ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ግዜ ጀምሮ በ 6 ወር ጊዜ ዉስጥ የክፍያ ጥያቄ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል ብሎ ይደነግጋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በመመሪያ መሠረት የጥቆማና የወሮታ ክፍያዎችን እየፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ *በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት* በ2005 በጀት ዓመት በጥቆማ ለተያዘ እቃ በ2009 በጀት ዓመት በባንክ

ክፍያ ማሳወቂያ መሰረት የይርጋ ገደቡ ካለፈ ከሶስት ዓመታት በላይ መሆኑ እየታወቀ ያለአግባብ ብር 18,786,184.38 የጥቆማና የወሮታ ክፍያዎችን የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.19/8 ቀን 21/05/10 ግኝት ቁጥር 2.1 ላይ ይመልከቱ)*

**ስጋት**

*መንግስት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች በአግባቡ በስራ ላይ ተግባራዊ አለማድረግ ተገቢ ካለመሆኑ የተነሳ ለብልሹ አሰራር በር ከፋች ሊሆን ይችላል፡፡*

**ማሻሻያ ሀሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቱ የወሮታ ክፍያን በተመለከተ የክፍያ ጥያቄዎችን ማስተናገድ የሚኖርበት ዕቃው ተይዞ ቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ክፍያ የሚፈጸምለት አካል አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

ክፍያውን የፈፀምነው የይከፈለን ደብዳቤ በየጊዜው በሚቀርብልን ወቅት ለዋናው መስሪያ ቤት በቅ/ጽ/ቤት የህግ ማስከበር ከዋ/መ/ቤት የህግ ማስከበር ዳይሬክቶሪት ክፍያውን በተመለከተ በማሳወቃቸው ወደ ኋላ በመሄድ ክፍያው እንዲፈፀም በተነገራቸው መሰረት ክፍያውን ፈፅመናል በማለት ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

በመመሪያው መሰረት የክፍያ ጥያቄ በወቅቱ ያልቀረበና ክፍያው ከመመሪያው አንጻር የጊዜ ገደቡ ሊራዘም ከሚገባው አንጻርም ያለፈ በመሆኑ እንዲሁም ከዋና/ቤት የህግ ማስከበር ዳይሬክቶሬት የክፍያውን ትዕዛዝ ያስተላለፈበት ደብዳቤ ባለመቅረቡ ምላሹ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

### III) የበጀት ሂሳብን በተመለከተ

#### 1) የተጠቃለለው ስራ ላይ ያልዋለ የካፒታል በጀት

**ግኝት**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2009 በጀት አመት የተመደበለትን የካፒታል በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ መ/ቤቱ የካፒታል በጀት ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ከ10% በላይ ልዩነት ያልተጠቀመበትን በጀት የሚያሳዩ በ3 የሂሳብ መደቦች ጠቅላላ ድምር ብር 80,251,132.95 ያልተጠቀመበት በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡

**ስጋት**

መ/ቤቱ የተመደበለትን በጀት በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ ካላዋለ አላስፈላጊ በጀት በመያዝ መንግስት ያስቀመጠውን ግብ እንዳያሳካ ሊያደርግ ከመቻሉም በላይ መንግስት ለሌላ ሥራ ሊያውለው ይችል የነበረውን ገንዘብ አላግባብ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

**የማሻሻያ ሃሣብ**

ባለስልጣን መ/ቤቱ በበቂ ጥናት የተመሰረተ አስተማማኝ የበጀት እቅድ በመያዝ በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ የሚያውለውን በጀት ክትትል ሊያውል ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ያልተጠቀምንባቸው የሂሳብ መደቦች በቀረበው እና በሪፖርቱ የተወሰኑ ልዩነት ያለ ሲሆን ይህንንም ያልተጠቀምንበት ምክንያት በበጀት የተፈጸሙ  ቅድመ ክፍያዎች ወደ ወጪ ባለመቀየራቸው የተፈጠረ ነው፡፡

#### 2) የተጠቃለለ የገቢ በጀት አፈጻጸም

**ግኝት**

በ2009 በጀት ዓመት የገቢ ሂሳብ ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው ብር 185,949,250,000.00 ሲሆን፣ የተሰበሰበው ደግሞ ብር 160,077,590,000.00 በመሆኑ እቅዱ ከክንውኑ ጋር ሲነጻጸርክንውኑ በብር 25,871,660,000.00(13%) አንሶ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ  የሂሳብ መደብ በመቶኛ ከ10% በላይ ከዕቅድ በታች ክንውን በ75 የገቢ ሂሳብ መደብ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ውስጥ ብር 26,430,907,214.20 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ታውቋል፡፡

**ስጋት**

በዕቅድና ክትትል ክፍል በኩል በታቀደው መሰረት በቅርጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል መሰብሰብ ያለበት ገቢ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስት ሊሰበስብ ባቀደው መሰረት ሳይሰበስብ ሊቀር ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ባለስልጣን መ/ቤቱ የገቢ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ሊሰበሰቡ የሚገባቸውን ገቢዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና ክትትል በማድረግ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ሊሰብስብ ይገባል፡፡

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

በካፒታል ዕቃዎች ሽያጭ ላይ በተገኘ ትርፍ ላይ የነበረው አፈጻጸም እንቅስቃሴው የታለመለትን ያክል አለመሆን፤

- በአገር ውስጥ የሚመረቱና የሚሰጡ አግልግሎቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ከክፍያ ጋር የሚያሳውቅት ምጣኔ ዝቅተኛ መሆን ፣
- የታክስ ህግ ማስከበር ስራዎች ክፍተት መኖር ፣
- በመንግስት በ2008 መጨረሻ ላይ የተደረገው የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የተደረገው ማሻሻያ በመስግስት ገቢ ላይ የራሱን ቅናሽ የሚያስከትል የነበረ በመሆኑ የዚህ ውጤት እንደሆነ ይገመታል፡፡ እንዲሁም በገቢ ሰብሳቢ አካላት የሚደረገው ክትትል ክፍተት የነበረበት ነበር፡፡
- እንዲሁም በገቢ አስገቢው ባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል ያለው የክትትል ክፍተት መኖር
- በኤክሳይስ ታክስ ይሰበሰብባቸዋል የተባሉት ምርቶች እንደታሰበው ያለመመረታቸው እና ግብር ከፋዮችን የሚጠበቅባቸውን የታክሰ መጠን ባለማሳወቃቸው ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት ነው፡፡በተጨማሪም በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የሚጣለውና የሚሰበሰበው ከውጪ በሚገቡ እቃዎች የታሰበውን ያክል ወደ ሀገር አለመግባታቸው እና የታክስና የጉምሩክ ቅሬታና አቤቱታ አፈታት አዝጋሚ መሆን ሊሰበሰብ ያልቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 3) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች በዕቅድ መሰረት ከየአርእስቱ ከ10% በላይ ያልተሰበሰበ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ብር 6,818,756,763.22 የሀገር ውስጥ ገቢ ብር 21,553,114,560.29 መኖሩ</u>

### <u>ግኝት</u>

በ2009 በጀት ዓመት በቅ/ጽ/ቤቶች በየአንዳንዱ የገቢ ሂሳብ መደብ በዕቅድ በተያዘው መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በጉምሩክ ስነ-ስርዓት የስራ ሂደት እና በገቢ አወ/አሰ/ክት/የስራ ሂደት በኩል ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው ብር ውስጥ ከእያንዳንዱ አርእስት ከ10% በላይ ያልተሰበሰበው ሲታይ የጉምሩክ ገቢ በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 6,818,756,763.22 እንዲሁም የሀገር ውስጥ ገቢ በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,553,114,560.29 ከታቀደው የገቢ ዕቅድ አንሶ ተገኝቷል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 35 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### <u>ስጋት</u>

በዕቅድና ክትትል ክፍል በኩል በታቀደው መሰረት የተሰበሰበው ገቢ የማይታይ ከሆነ ቅ/ጽ/ቤቱ ባቀደው መሰረት ሳይሰበስብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ እቅዱን ተዓማኒነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ እርምጃ</u>

ቅ/መ/ቤቱ የገቢ ዕቅድ ጥናት ላይ የተመሰረተ እና ተግባር ላይ ሊውል የሚችል ሊሆን የሚገባ ከመሆኑም በተጨማሪ የቅ/ጽ/ቤቱን የገቢ አሰባሰብ ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

### <u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>

### <u>*የባህርዳርና የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤቶች*</u>

የገቢ ዕቅድ የሚታቀደው የባለፈውን አፈጻጸም በየገቢ ሂሳብ መደብ ያለውን መሠረት በማድረግ በዚህ ላይ በኢኮኖሚ ታሳቢ በፐርሰንት በማሳደግ የሚታቀድ ሲሆን በታቀዱት የገቢ አርስቶች በታች እና በላይ የሚሆንበት አጋጣሚዎች ከንግዱ ባህሪም ጭምር ለምሳሌ በባለፈው ዓመት በአንድ ዘርፍ አትራፊ የነበረው ድርጅት ኪሳራ ቢያስመዘግብ ድርጅቱን ቢዘጋ፣ የንግድ እንቅስቃሴው ቢቀንስ በሚኖሩት ክስተቶች ሲሆን ለወደፊትም በየገቢ ሂሳብ መደብ ዕቅድ ለማሳካት የማይታሰብ መሆኑ ግንዛቤ እንዲወሰድልን ሆኖ ቅ/ጽ/ቤቱ ካሉት ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ያለበትን ገቢ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ሙሉ አቅሙን

ተጠቅመን በተቻለ መጠን በጥቅል የገቢ ዕቅዱን ለማሳካት ጥረት የተደረገ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

እቅድ የሚዘጋጀው በዋናው መ/ቤት ስለሆነ በጣቢያው ዲክሌር የሚያደርጉ እቃዎች በብዛት የቤት መገልገያ እቃዎች በመሆኑ፤ተቋሙ አገልግሎት ሰጪ ስለሆነ ሁሉም የመጣ ተገልጋይ ተገቢ የሆነ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ እና እኛም አሳክተናል አላሳካንም የምንለው የተሰጠን ጥቅል እቅድ ስለሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ቀጣይ በተሰጠን ግብአት መሰረት አድርገን እና የጣቢያው የስራ እንቅስቃሴ መሰረት አድርገን በማቀድ እንሰራለን በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በዕቅድ መሰረት ከየሂሳቡ መደብ ከ10% በላይ ያልተሰበሰበ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ምክንያቱን ለይተን ለወደፊቱ በዕቅድ መሠረት ለመሰብሰብ ጥረት እናደርጋለን በማለት ገልጸዋል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

**የጉምሩክ ገቢን በተመለከተ**

የገቢ እቃዎች በቅርጫፍ ጽ/ቤት መቀነስ ሊታይ የቻለው የምንዛሬ እጥረት በመኖሩ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ያፒ መርከዚ ለፕሮጀክት የሚሆኑ እቃዎች በብዛት በማስገባቱ እና በ2009 በጀት ፕሮጀክቱ በመጀመሪያ ዙር በማጠናቀቁ ምክንያት እቃዎች በብዛት ያላስገባ ሲሆን በተጨማሪም የአምራች ድርጅቶች የሚያስመጧቸው እቃዎች በመቀነሱ የታየ ሲሆን እንደ አጠቃላይ ግን ቅ/ጽ/ቤቱ ዕቅዱ ለማሳካት ሰፊ ጥረት የተደረገ ቢሆንም አብዛኞቹ አርዕስቶች እቃዎቹ ካለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በጊዜያዊነት በቀረጥ ነጻ የገቡ መሆኑና የእቅዱን አለመሳካት ያመጣው ተጽእኖ መሆኑን፤

**የሀገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ**

ከዋና መ/ቤት ዕቅዱ ሲላክ በጣም የተለጠጠ ዕቅድ የተላከ በመሆኑ በገቢ ሂሳብ መደብ የመጣው ዕቅድ የግድ መደልደል ያለበት ስለሆነ እንዳጠቃላይ እቅዱን ለማሳካት ያልተቻለ ስለሆነ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- የኮንቴነር ክምችት በወደቡ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ዕቃዎቻቸውን ቀርበው እንዲያወጡ በተደጋጋሚ ቅስቀሳ የተሰራ ቢሆንም የተለያየ ምክንያት በማቅረብ አስመጪዎች በወቅቱ ቀርበው የሚፈለግባቸውን ቀረጥና ታክስ ከፍለው እቃዎችን ባለማውጣታቸው፣
- ውዝፍ ስራዎች በጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት በእቅድና ግምገማ በመመራት በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ አሟጦ ወደ ገቢ መቀየር ላይ ክፍተት በመታየቱ፣
- ከቀሪ ሂሳብና ከሚወገዱ እቃዎች ሊሰበሰብ የታቀደ ገቢ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ወደ ገቢ መቀየር ላይ በሚፈለገው ልክ አለመሰራቱ፣
- ኮንቴነሮች ደረቅ ወደብ ስለመድረሳቸው የሚመለከተው መ/ቤት በወቅቱ መረጃውን ከማሳወቅ አንጻር ክፍተት መኖሩ፣
- የባንክ ሰነዶችን በወቅቱ የማይደርሱ በመሆናቸው እና የሰነድ እርማት መከልከሉ ዲ/ዮን ሞልቶ ማውጣት አለመቻል ምክንያት መሆን፣
- በውጭ ምንዛሬ አሰጣጥ እጥረት ጋር በተያያዘ ገቢ እቃዎች መጠን መቀነስ (እስከ ሶስተኛ ሩብ ዓመት) ሲሆን፡

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ችግሮችን ከወዲሁ እንዲቀረፉ በማድረግ የቀጣይ በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ አፈፃፀም እንዲሳካ ያለሰለሰ ጥረት ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

አጠቃላይ እቅዱን መሰረት አድርገን በየኮዱ እንሸነሽናለን በዚህ መሰረት ሙሉ በሙሉ ያልተሰበሰበ ገቢ አለ ቅ/ጽ/ቤቱ የሚወስደው ክፍተት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ከዋናው መ/ቤት ሲመጣ የተጋነነ እቅድ በመሆኑ ክፍተቱ ሊጎላ ችሎል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች</u>***

የደመወዝ ገቢ ግብር ከአዲስ የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ጋር የተያያዘ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር በገንዘብ ምንዛሬ ችግር ጋር በተያያዘ እንዲሁም የቴሌ የተ.እ.ታ በአገሪቱ ላይ በተከሰተው ችግር ምክንያት የኢንተርኔት አክሰስ መዘጋቱ እንዲሁም በመንግስት መ/ቤቱ የሚከፈለው ተ.እ.ታ ዊዝሆልዲንግ በበጀት አለመለቀቅ ችግር ዋነኛው ገቢ በዕቅዱ መሰረት አለመሰብሰቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 4) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች በእቅድ ሳይያዝ የተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 59,142,330.60 መኖሩ</u>

### <u>ግኝት</u>

በ2009 በጀት ዓመት በየቅ/ጽ/ቤቱ የተሰበሰበው ገቢ በጥናት የተመሰረተ ዕቅድ ተይዞለት የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በጉምሩክ ገቢ እና በሀገር ውስጥ ገቢ በኩል ይሰበሰባል ተብሎ ዕቅድ ሳይያዝ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 59,142,330.60 የተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 36 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

### <u>ስጋት</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ ሊሰበስቡ ያቀዱትን ማንኛውም ገቢ በዕቅድ አካተው ካልያዙ የሚሰበሰበው ገቢ በብቃት ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ሰዓት የሚሰበስበውን ገቢ በየሂሳብ መደቡ ትክክለኛ ጥናት በማድረግ ሊይዙ እና ሊሰበስቡ ይገባል፡፡

### <u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>

***<u>የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በዕቅድ ሊያዙ የማይችሉ አጋጣሚዎች ያሉ መሆኑና ሳይጠበቁ የሚገኙ ገቢዎች ለምሳሌ በቅ/ጽ/ቤታቸው ከሼር ሽያጭ በእቅድ ያልተያዘለት ያልተጠበቀ ገቢ ያጋጠመ መሆኑን ሊሰበስቡ የቻሉት እንዳጋጠማቸው እና ይህን በመሳሰለ ሁኔታ እቅድ ሳይያዝ ሊቀር ይችላል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ኮድ 1331 ላይ የተያዘው ቀድሞ በቅ/ፅ/ቤቱ የማይስተናገድ ዕቃ ሲሆን፣ በዕቅድ አልተያዘም ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ካለው የረዥም ጊዜ ልምድ ይህ ዕቃ ከአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ውጪ በሌሎች ቅ/ፅ/ቤቶች የመስተናገድ ዕድሉ በጣም አነስተኛና የማይጠበቅ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም እንደዚህ አይነት ዕቃዎች ዕቅድ ሳይያዝላቸው አልፎ አልፎ በቅ/ፅ/ቤታችን ተመዝግበው ሊስተናገዱ የሚችሉበት አጋጣሚ /የገንዘቡም መጠን አንፃር/ ሊያጋጥም ስለሚችል በዚህ አግባብ እንደ ችግር ባይታይ በማለት ገልጸዋል፡፡

## 5) **<u>በቅ/ጽ/ቤቶች ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 210,605,755.19 ስለመኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 02/1 ቅ/ጽ/ቤቶች ለበጀት ዓመቱ ከዋናው መ/ቤቱ የተደለደለላቸውን የመደበኛ ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ በመቆጣጠር ስራ ላይ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2009 በጀት ዓመት ለወጪ ሂሳብ ከተደለደለው በጀት ውስጥ በእያንዳንዱ አርእስት ከ10% በላይ ልዩነት ያላቸው በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 210,823,100.54 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 37 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

የመንግስት መ/ቤቶች በበቂ ጥናትና ዕቅድ ላይ ያልተመሠረተ እና ጥቅም ላይ ከሚያውሉት በጀት በላይ በስማቸው የሚያዝ ከሆነ መንግሥት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ሥራዎች ሊያውል የሚችለው ገንዘብ በተገቢው ቦታና ጊዜ ጥቅም ላይ ሳይውል ሊቀር ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

ለወደፊቱ የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ በበቂ እቅድና ጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

*<u>የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>*

ኮደ 6416 በባህሪው የበጀት ድልድል ስለሌለ የኮንትሮባንድ እቃ በተያዘበት ወቅት የወሮታ አበል በመመሪያው 78/2004 ዓ/ም መሰረት ተሰልቶ ለዋናው መ/ቤት በጀትና እቅድ አፈጻጸም ተልኮ ከዛም ወደ ገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ተልኮ የበጀት ዝዉዉር ተደርጎ ሲፈቀድ በመሆኑ ሰኔ አጋማሽ አካባቢ ወደ 8,148,094 የበጀት ዝዉዉር በማድረግና ቀሪዎቹ ቀናትም የበጀት መዝግያና አጣዳፊ ቀናት ስለነበሩ ብር 4,023,373.32 ስራ ላይ ሳይዉል የቀረ መሆኑን እና ሌሎችም አብዛኛው የበጀት ዝውውሮች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በመደረጉ ሳንጠቀምበት የቀረ ነው በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት***

**አብዛኛውን ጊዜ በጀት ቶሎ የማይለቀቅልን በመሆኑ ወደ  መጨረሻ አካባቢ የሚለቀቀውን በጀት አስፈላጊውን የግዢ ሂደት በመከተል ግዥ በመፈፀም አሟጠን እንዳንጠቀምበት የቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን ከመሃል ሀገር በርቀት ላይ መገኘቱ እንደምክንያት ሊጠቀስ የሚችል ሲሆን ለወደፊቱ በተቻለ መጠን የሚበጀትልንን በወቅቱ ለመጠቀም ጥረት እናደርጋለን በማለት ገልጸዋል፡፡**

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

**ከተፈቀደው ስራ ላይ ያልዋለ በጀት በባንክ አካውንታችን ገቢ ተደርጎልን የነበረ ሲሆን ሳንጠቀምበት በመትረፉ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፈሰስ ተደርጓል ቀሪው በጀቱ ይፈቀድ አንጂ ገንዘቡ አልመጣልንም/በአንዳንድ የወጪ ሂሳብ መደቦች ላይ የተጠቀሰው በጀት ተጠቃሎ ያልተላከ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን**

<u>ተርፎ ፈሰስ የተደረገበት ምክንያት</u>

- የያዥና ጠቋሚ በጀት /6416/ ከመነሻው በጀት አልተያዘለትም ክፍያ ሲመጣ ሊከፈል የሚችል የተወሰነ በጀት በመላኩ እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ድረስ የቀረቡ ክፍዎችን ሙሉ በሙሉ አስተናግደን የተረፈ በጀት በመኖሩ፣
- ልንገዛቸው የነበሩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒዩተሮች እና ፎቶ ኮፒ ማሽኖች በዋናው መ/ቤት በኩል ድጋፍ በመደረጉ ለነዚህ የወጪ ሂሳብ መደቦች በተመደበው በጀት እንዳንድ የሚያስፈልጉንን ተጨማሪ ዕቃዎች ገዝተን የተወሰነ ገንዘብ በመትረፉ፣
- በ6213 ሂሳብ መደብ አብዛኛው የህትመት ውጤቶች ከዋና መ/ቤት ስለተላከልን በበጀት ዓመቱ ብዙ የህትመት ስራ ባለመኖሩ፣
- የካቲት ወር 2009 ዓ.ም የመደበኛ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ ብር 92,000.00 እንድንከፍል ተጠይቀን ክፍያው እጅግ በጣም የተጋነነ ሆኖ ስላገኘነው ቅሬታ አቅርበን ሂሳቡ እንደገና እየተመረመረ ያለበት ሁኔታ በመኖሩ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ክፍያ ባለመፈጸማችን የተመደበው በጀት ተመላሽ በመደረጉ፣
- የቀን ሰራተኞች እንደስራችን ባህሪ ሲፈለጉ የሚቀጠሩበት ሳይፈለጉ ደግሞ የሚሰናበቱበት ሁኔታ በመኖሩ በቀጣይ የሚኖረውን ስራ መገመት ባለመቻሉ ሲሆን ከተፈቀደልን በጀት ውስጥ ብር 76,710.00 አልተላከልንም፣

- በሂሳብ መደብ 5059 በልዩነት የተገለጸው ከወጪ ቀሪ ብር 21,866.30 ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር ተያይዞ የወልዲያ ኬላ አገልግሎት የሚሰጥ የውሃ መስመር ለማስገባት በአካባቢው የውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 80,049.00 እንድንከፍል ተጠይቀን በጀቱ የተፈቀደና ወደ አካውንታችን ገቢ ከተደረገልን በኋላ በኬላው አካባቢ ሌሎች ውሃ የሚያስገቡ አካላት በመኖራቸው ወጪው በጋራ ተሸሽሎ ብር 60798.00 እንድንከፍል በመደረጉ፣
- በሂሳብ መደብ 6257 ለአዲሱ ቢሮና ለመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ ለመብራት ትራንስፎርመር ማስገቢያያ እንድንከፍል የጠየቅነው በጀት ተልኮልን ክፍያውን ሙሉ በሙሉ የፈጸምን ሲሆን ከዚህ ውጪ ከዋነው መ/ቤት በስህተት የተላከ ብር 172,011.00 በመኖሩ፣
- ሌሎች የወጪ ሂሳብ መደቦች ከተፈቀደው በጀት በትርፍ ወይም ከወጪ ቀሪ የሚያሳየው የተፈቀደልንን በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በአግባቡ እና በቁጠባ በመጠቀማችን እንደሆነ ይታወቅ በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የዋና መ/ቤት</u>***

በቀጣይ በባለስልጣኑ መ/ቤቱ ያልተሰራበት በጀት እንዳይከሰት እና በተደለደለው መሰረት ወጪ መደረጉን ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***<u>የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- 6116 በጠየቅነው መሰረት የተጨማሪ በጀት ተከትሎ የተከሰተ መሆኑን እና የሰኔ ወር 2009 በትርፍ ሰዓት ክፍያ ወደ ሀምሌ ወር 2009 በመሄዱ፣
- 6219,6232,6243,6253,6255,6257 እና 6259 በዚህ የሂሳብ አርዕስቶች የተደለደለው በጀት ስራ ላይ ይውላል በሚል ቀደም ብሎ ወደ ባንክ ሂሳብ ቁጥራችን ገቢ በመደረጉ አዘዋውረን ለመጠቀም ባለመቻሉ ያቀረብነው የበጀት ዝውውር ባለመፈቀዱ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች</u>***

- የትርፍ ሰዓት ክፍያ እና የጡረታ መዋጮ ክፍያን ከቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በጀት እንዲፈቀድልን ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳይቀርብ ሰኔ 22 እና 30/2009 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጨማሪ በጀትነት የመጣ በመሆኑ

- የቅ/ጽ/ቤቱ ኦዲተሮች እና ሌሎች ባለሙያዎች ለመስክ ስራ በሚጠበቀው ደረጃ ባለመውጣታቸዉ
- ቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በ2009 በጀት ዓመት አዲስ በወጡት የፌደራል የገቢ ግብርና የታክስ አስተዳደር አዋጆች ዙሪያ ስልጠና ለግብር ከፋዮች ለመስጠት 1.2 ሚሊዮን ብር ተፈቅዶለት ስልጠናው የተዘጋጀዉ በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብሩ ተራፊ ሊሆን በመቻሉ
- የመብራትና የዉሃ ፍጆታ እንደ አጠቃቀማችን የሚመጡና አጠቃቀሙም ከስራው ባህሪ አንፃር ወጥነት የማይኖረዉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር በመሆኑ
- የጥቆማ በጀት ሂሳብ በወቅቱ የጥቆማው ክፍያ አጠራጣሪ በመሆኑ እና ሰነዱ እንዲጣራና በዋናዉ መ/ቤት ደረጃ ጊዜ በመውሰዱ የተነሳ ያልተጠቀሙበት በጀት ሊኖር እንደቻለ ገልጸዋል፡፡

***<u>የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- በኮንትራት የተቀጠሩ ሰራተኞች ክፍያ ያልተጠቀምን ሲሆን ዋናው መ/ቤት ተጠይቆ የተከፈለው ከቋሚ ሰራተኞች ደመወዝ መሆኑን ስናጣራ ደርሰንበታል በመሆኑም በቀጣይ ይህ ትክክል ያለመሆኑን በመረዳታቸው ማስተካከያ የሚደርጉ መሆኑን፣
- 6116 የተያዘው በጀት አልቆ ተጨማሪ የተፈቀደ ሲሆን ነገር ግን በሰኔ ወር የተሰሩ ትርፍ ሰአት ክፍያዎች በሃምሌ ወር የተከፈለ በመሆኑ፣
- 6243 ለጥገና ወጪ በበጀት አመቱ በጀት የተያዘ ቢሆንም በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙትን ኮምቲውተሮች እና ፕሪንተሮችን ጥገና በቅ/ጽ/ቤቱ የአይቲ ባለሙያዎች ጥገና በመደረጉ ምክንያት ወጪ በመቀነሱ የ2009 በጀት አመት ለጥገና ከተያዘው በጀት የተወሰነ በጀት ሳንጠቀምበት የቀረን በመሆኑ፣
- 6259 የማእከላዊ ግምጃ ቤት እና የቅ/ጽ/ቤቱ የውሃ ኪራይ በ 2009 በጀት አመት የሚከፈልበት ደረሰኝ ባለቤቶቹ ባለመስጠታቸው ያልተከፈለ ስለሆነ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ለኮንትራት ሠራተኞች ክፍያ የተያዘውን በተመለከተ የኮንትራት ሠራተኞች ስላልተቀጠሩና የተመደበውን በጀት ስላልተጠቀምንበት የተፈጠረ ችግር ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

## 6) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 9,623,230.80 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

**የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 30 መሰረት እንዲሁም አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 የበጀት ዝውውር ወይም የተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈጸም እንደማይቻል በሚያዘው መሰረት ከበጀት በላይ ሳይፈቀድ ወጪ አለመደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ ጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ከተደለደለው በጀት በላይ በድምሩ ብር 9,623,230.80 ወጪ መደረጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.22/4 ቀን 06/07/10 ግኝት ቁጥር 5.2 ላይ ይመልከቱ)***

**<u>ስጋት</u>**

በጀት የማጽደቅም ሆነ የማዘዋወር ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ከማድረጉም በተጨማሪ በህግ ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

ቅ/መ/ቤቶች በዋናው መ/ቤት ተዘጋጅቶ በተላከው የበጀት ድልድል መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ወይም የበጀት ዝውውርም ዋና መ/ቤቱን በመጠየቅ ስራውን ሊያከናውን ይገባል፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በወቅቱ ስራውን ሲመሩ የነበሩ አመራሮች መልስ ሊሰጡበት ይገባል በማለት በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

የጽ/ቤቱ የስራ አመራር ለኦዲት ባቀረበው ሰነድ መሰረት የኦዲት ግኝት ላይ ተገቢ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

**8) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች ዕቅድ ክፍል ክንውን ተብሎ የተያዘው በሂሳብ ሪፖርት መግለጫ ከተመለከተው ገቢ በብር 3,241,735.89 አንሶ መገኘቱ</u>**

በ2009 በጀት የተሰበሰበው ገቢ በገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ቡድን የሂሳብ ሪፖርት በቀረበው መሰረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ***በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት*** በገቢ ሂሳብ ሪፖርት የተያዘው በእቅድ ክፍል ከተያዘው በብር 3,241,735.89 አንሶ የተገኘ መሆኑ በኦዲት ወቅት

ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF 05.1/8 ቀን 10/02/10 ቁጥር 5.2 ላይ ይመልከቱ)*

**ስጋት**

የገቢ ሂሳብ ሪፖርትና የገቢ ክንውን የተለያየ መረጃ የሚያሳይ ከሆነ በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ ገቢ እንደ ገቢ የሚታይ በመሆኑ ለሶስተኛ ወገን የተዛባ የመረጃ እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመት የተሰበሰበ ገቢ መሰረት የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ሊታይ የሚገባ በመሆኑ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት በመስጠት በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበውን ገቢ ሪፖርት ላይ እንዲታይ ሊያደርግ ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ**

ሐምሌ ወር ተሰብስበው በሰኔ ወር ላይ ሪፖርት በመደረጉ እና የዕቅድ አፈጻጸምና ክትትል ቡድን በኩል ባለመያዙ የታየ ልዩነት መሆንን ገልጸዋል፡፡

**የኦዲቱ አስተያየት**

በሰኔ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የሐምሌ ወር መካተቱ የበጀት ዓመቱን ገቢ በብልጫ እንዲታይ እና የተዛባ የሂሳብ ሪፖርት እንዲኖር የሚያደርገው በመሆኑ ለወደፊቱ ልዩነት መፈጠር የለበትም የተባለው ትክክል ሆኖ ሪፖርቱ ግን ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ሊያሳይ ይገባል፡፡

## IV) ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ

### 1) በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወራረደ) ብር 52,074,280.63 መኖሩ

**ግኝት**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ከ 1999 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ

ከ 10 ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 52,074,280.63 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 38 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## ስጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሃሳብ

በሪፖርት የሚታየው ያልተወራረደ ሂሳብ ክትትል ተደርጎበት መወራረድ ያለበት ሲሆን መወራረድ የማይችለውም በፋይናንስ ደንብ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### *የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት*

ሂሳቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ (1989 ዓ.ም-1996 ዓ.ም) ባሉት ጊዜያት የተሰራ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ ያልተገኘለትና በየአመቱ ከ2005 ጀምሮ በግኝት እየተያዘ የሚገኝ ሲሆን በበላይ አካል እንዲሰረዝልን በተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበን ምለሽ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### *የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት*

- በ 4203 ብር 489,268.68 የተያዘ ተሰብሳቢ በ 2009 ዓመት ለተለያዩ ሠራተኞች አበል ለመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የተላከ ሥራ ማስኪያጃና ሌሎች የተለያየ ክፍያዎች በሰራተኛ ስም ወጪ ሆኖ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሳይወራረድ የቀረና ለ2010 በጀት ዓመት የዞሩ ሒሳቦች ሲሆኑ እነዚሁ ሒሳቦች ከሐምሌ 2009 ጀምሮ እየተወራረዱ ያሉ ሒሳቦች መሆኑ፣
- በ 4211 ብር 51,694.70 የተያዘ ተሰብሳቢን በተመለከተ የግዥ ሠራተኛ የተለያዩ ዕቃዎችን ለመግዛት ወጪ ያደረጉት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ሳይወራረዱ ወደ 2010 በጀት ዓመት የዞረ ሒሳብ ሲሆን ከሐምሌ 1/2009 ጀምሮ ሒሳቦቹ የተወራረዱ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

<u>***የኦዲተሩ አስተያየት***</u>

በ4211 የተመዘገበውን ተሰብሳቢ አስመልክቶ ከሀምሌ 1/2009 ጀምሮ መወራረዱን የገለጹ ቢሆንም በድጋሚ በተደረገው ማጣራት ሂሳቡ ያልተወራረደ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ የማንቀበለው ይሆናል፡፡

<u>***የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን በቀጣይ ክትትል በማድረግ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ተመላሽ እንዲያደርጉ ክትትል የሚያደረጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

<u>***የምስራቅ አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት***</u>

ተሰብሳቢን በተመለከተ ባለሙያ ሰብስበን እየሰራን ሲሆን በባንክና በ IFMIS መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥራት ሞክረን ከገንዘብ ሚኒስተርም ባለሙያ ተመድቦ በሂደት ላይ ነው በማለት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

<u>***የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

- በሂሳብ መደብ 4203 የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ለቅ/ፅ/ቤቱ ሠራተኞች አበል የተከፈለና ሳያወራርዱ በሞትና በተለያዩ ምክንያት ከተቋሙ የተለዩ ሰራተኞች በመሆናቸው ሳይወራረድ ለረዥም ጊዜያት የቆየ በመሆኑ ከመዝገብ ለማሰረዝ (write off) ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በወጪ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 4201 ላይ የሚታየው ከሲስተም ጋር ተያይዞ የተፈጠረ የአመዘጋገብ ችግር በመሆኑ በቀጣይ የማስተካከያ ስራ የሚሰራለት መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

<u>***የአ/አ/ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት***</u>

በአቶ ዘመድኩን ገ/መድህን የጎደለውና በልደታ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሌሉበት የፍርድ ውሳኔ ያገኘ በቅ/ጽ/ቤቱ ለህግ ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት በፍ/ብሄር እንዲጠየቁ በደብዳቤ ቁጥር 07-2.6-289/10 በቀን 18/03/2010 ዓ.ም የተላለፈ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

<u>***የኦዲተሩ አስተያየት***</u>

ለግዢ ሰራተኞች በቅድሚያ የተከፈለውን እና ሌሎች ተሰብሳቢዎች በተመለከተ የስራ አመራሩ ምላሽ ያልተሰጠ በመሆኑ በቀጣይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

ሀብት አስተዳደር በኩል የሚታየው ለረጅም ጊዜ የቆዩ ሂሳቦች እንዲወራረድ በየጊዜው ጥረቶች ተደርገው በርካታ ሰነዶች የተወራረዱ መሆኑ እና በአሁን ወቅት ውሳኔ ለማሰጠት መረጃ የማሰባሰብ ስራ በመሰራት ላይ እንገኛለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት***

- በሂሳብ መደብ 4273 ላይ ከተመዘገበው በግብር እዳ የተያዘ ተሽከርካሪ ከተያዘበት ወደ ፌደራል ፖሊስ ካምፕ ለማጓጓዣ በተሰብሳቢ ወጪ ሆኖ የተከፈለ ሲሆን በቀጣይ ተሽከርካሪው ሲሸጥ የሚሰበሰብ በመሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ በ4274 ላይ በተሰብሳቢ ተመዝግቦ ከሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ በተለያዩ ቀናት ስራ ታዘው ከውሎ አበል ቅድሚያ ወስደው ሂሳቡን ሳያወራረዱ ቦታ የቀየሩ በመሆኑ፣ የፌደራል ፖሊስን ወንጀል መከላከል ዘርፍ ጎንደር ዲቪዥን በተደጋጋሚ በደብዳቤ ቢጠየቅም አድረሻቸውን አናውቅም በማለታቸው እስከ አሁን ድረስ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይወራረድ የቆየ ሲሆን፣ አሁን ሰዓት የበላይ አመራሩ ለፌደራል ፖሊስ ከሚከፍለው የያዥ የወረታ አበል ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲደረግ አቅጣጫ ያስቀመጠ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ የሚደረግ መሆኑን እና በህግ-ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ ተይዞ በቁጥጥር ስር የዋለን ቡና ወደ ሚመለከተው አካል ወስዶ ለመሸጥ ለመጓጓዣ ለአጀቢ አበል እንዲሁም ለሌሎች ወጪዎች ተከፍሎ በተሰብሳቢ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን፣ ቡናው ሲሸጥ ከቡናው ሽያጭ ላይ ተቀንሶ ከገቢ የሚደረግ መሆኑን ፣
- የሀገር ውስጥ የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር የሒሳብ መግለጫ ላይ የሚታየውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አለአግባብ ቀንሶ የሚገኘውን በተመለከተ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከከምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በመሆን ባለስልጣን መ/ቤቱ ገንዘቡ እንዲዛወር ፈቃድ ሳይሰጠው የደሴ ንግድ ባንክ ቅርጫፍ ከአካውንታችን በመቀነሱ ምክንያት በተሰብሳቢ የተያዘ መሆኑና ቅ/ጽ/ቤቱም ገንዘቡ በአፋጣኝ መመለስ ያለበትና ይህ ካልሆነ ባንኩ በህግ የሚጠየቅ መሆኑንን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት***

በቀን 30/07/09 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 82491 እና913251 የተሰበሰበ ተመላሽ ገንዘብ በተቀፅላ ሌጀር ስህተት ምክንያት ስለሆነ ማስረጃውን ኮፒ አድርገን አያይዘናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

ማስረጃ ለቀረበለት የማስተካከያ ሂሳብ የተሰራ ቢሆንም ከላይ የተሰጠው ምላሽ በተጠየቀው መሰረት ባለመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

**2) ማስረጃ የሌላቸውና ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 48,444,108.39 መኖሩ**

**ግኝት**

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በጊዜ ገደቡ የማይወራረድ ከሆነ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ የአለበት መሆኑንና በዚህ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር ቅ/ጽ/ቤቶች በሰኔ 30/2009 የሂሳብ መግለጫቸው ላይ ሪፖርት ላደረጓቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች በቂ ማስረጃ ያለው ስለመሆኑና በትክክል ተሰብሰቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ በቂ ማስረጃ የሌላቸው ሲሆኑ አብዛኞቹ ሂሳቦች በባለፉት ዓመታት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መሆኑና እርምጃ ሳይወሰድባቸው የቆየ በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ 48,444,108.39 መኖሩንና ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ላይ በድምር መያዙ ለማየት ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 39 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

በመመሪያው መሰረት በተሰብሳቢነት ለመዘገባቸው ሂሳቦች ተገቢው መረጃ ባለመኖሩ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት በተሰብሳቢነት ለመዘገባቸው ሂሳቦች ተገቢው መረጃ ሊኖረውና አስቀድመው በሌጀር ሊመዘገቡ ስለሚገባ የሂሳቡን ምንነት በማጣራት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ

### የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

ሂሳቡ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ (1989 ዓ.ም-1996 ዓ.ም) ባሉት ጊዜያት የተሰራ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ ያልተገኘለትና በየአመቱ ከ2005 ጀምሮ በግኝት እየተያዘ የሚገኝ ሲሆን በበላይ አካል እንዲሰረዝልን በተደጋጋሚ ጥያቄ የቀረበ በመሆኑና ከመሠረዙ በፊት መረጃዎችን እንድናቀብ በተጠየቀው መሠረት ሰነድ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም ሰነዱ ያለበትን ሁኔታ በማጣራት ከሰነዱ ጋር አያይዘን ከመዝገብ እንዲሰረዝልን በድጋሚ ጥያቄ ለማቅረብ የሰነድ አጣሪ ኮሚቴው ሪፖርቱን ያቀረበ ሲሆን በቀጣይ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑ ይታወቅ ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

- በገቢ ሂሳቦች ዋስትና የስራ ሂደት በሂሳብ መደብ 4274 ለተመዘገበው ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ከዲፖዚት አካውንት የተቀረጠና በወቅቱ ማስረጃ ተይዞ ወጪ ላይ ያልተመዘገበ በመሆኑ ተንጠልጥሎ የሚታይ ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ መሆኑ፣
- በግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በሂሳብ መደብ 4201 ተመዝግቦ የሚገኘውን ተሰብሳቢ ሂሳብ በተመለከተ የፌደራል ገቢዎች ባለስልጣን እና የኢትዮጲያ ጉምሩክ ባለስልጣን ሲቀላቀሉ የተፈጠረ በመሆኑ መነሻ ሰነድ የሌለውና ታሪኩን የሚያውቀው ባለመኖሩ በዚህ ሁኔታ ያለ በመሆኑ ከመዝገብ ለማሰረዝ (write off) ለማድረግ ሰነዱ ያልተገኘ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

### የጅማ ቅ/ጽ/ቤት

ግኝቱን አስመልክቶ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ተሰብሳቢ ተብሎ መያዝ ያልነበረበት ነገር ግን እንደተሰብሳቢ የተያዘ በመሆኑ በእኛ አቅም ማስተካከል ያልተቻለ ነው በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት***

- በሂሳብ ኮድ 5217109 ለተባለው ከአደራ ሂሳብ ለተወረሰባቸው በዳይሬክተሩ ውሳኔ መሰረት የተከፈለና በጀት ኮድ 6419 ተይዞ ለባለስልጣኑ መ/ቤት ፋይናንስ ተላልፎ ለቅ/ጽ/ቤቱ የበጀት አካውንት ውስጥ ባለመግባቱ ምክኒያት ተራ ተይዞለት ያለ በጥር 2010 አ.ም እንደሚላክልን የሚጠበቅ ብር 1,953,960.14 ያለ መሆኑ፣
- የሂሳብ ቁጥር 5217311 ላይ የሚታየው ብር 2,280,827.11 በማይታወቅ ተሰብሳቢ ተይዞ ያለው ቀደም ሲል ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለል ከአይቤክስ ወደ ኢፍሚስ የተላለፈው 16 ሚልዮን ውስጥ 14 ሚልዮን ከነበረው በማይታወቅ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ተወራርዶ የቀረው ልዩነት ነው፡፡ ይህም በብሔራዊ ባንክ ያለው የቅርንጫፍ አካውንት ከመከፈቱ በፊት የነበረው የባንክ ምዝገባ እና ሌጀር ሂሳብ ሳይጣጣም ወደ ብሔራዊ ባንክ ሲዞር የነበረ የተፈጠረ የሂሳብ አመዘጋገብ ችግር ስለነበረ ባንክ ምዝገባ የነበረው ግንዛቤም በወቅቱ ሙሉ ምዝገባ ሳይከናወንበት ወደ መንግስት ካዝና ስለተዛወረ ያለው አማራጭ የJV ምዝገባ በማሳለፍ ከማስተካከል ውጭ የተሸለ አማራጭ ያልተገኘለት መሆኑን ይታወቅ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት***

ብር 12,557.82 በdefault የተመዘገበና በስም ያልተገለጸ እንዲሁም ለረዥም ግዜ እየተንከባለለ የመጣ ሲሆን ብር 15,754.80 እና ብር 20,149.12 በሂደት የማጥራት ስራ በመስራት ወደፊት ምላሽ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

ውሳኔ ለማሰጠት መረጃ የማሰባሰብ ስራ በመስራት ላይ እንገኛለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የዋና መ/ቤት***

የተወሰኑት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከማን እንደሚሰበሰቡ በሲስተም የሚታወቁ እና የኢፍ ሚስ ሲስተም ችግር በመኖሩ ለይቶ ለማሳየት ያልተቻለ ቢሆንም በሰነድ ደረጃ ማስረጃው ተገኝቶ ያልታየ በመሆኑ ለወደፊቱ ከማን ከማን እንደሚሰበሰብ በማጣራት ማስረጃውን የሚያቀርቡ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ መሰረት ሂሳቡ ተሰብሳቢ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ የሌለና የግለሰቦቹ ቀደም ሲል የፊናንስ ፖሊሶች የነበሩትም በአሁን ሰዓት አድራሻቸው የማይታወቅ አድራሻቸው የሚታወቁትም ሲጠየቁ የሌለባቸው መሆኑን በመግለጻቸው እና የመረጃው አስተማማኝ ባለመሆኑ ለመሰረዝም ዋና መ/ቤት ያሳወቁ ቢሆንም ሃላፊነት ወስዶ እንዲሰረዝ የሚል አካል ባለመኖሩ ሂሳቡ ሲንከባለል የቆየ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተሰብሳቢነት የተያዙና እየተንከባለሉ የመጡ በአይቤክስ ሲስተም ላይ የሚታይ ሲሆን ፣ ተቋሙ በጋራ የገቢ ሂሳብና የወጪ ሂሳብ ሚሌ በነበረበት እንዲሁም በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በካሽ ጉድለት የሚያሳየው ሚሌ በኮምበልቻ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በነበረበት ሰዓት እንደሆነ በወቅቱ ሲሰሩ ከነበሩ የቅ/ጽ/ቤት ሰራተኛ በስልክ ባገኘው መረጃ አማካይነት መሆኑን የተገለጸላቸው መሆኑን እና ከኮምቦልቻ ወደ ሚሌ እየመጣ ደመወዝ ክፍያ ሲያደርግ በነበረ ካሽሪ ላይ የታየ ጉድለት ሲሆን መረጃውን ለማጣራት ጊዜ ተሰጥቶት በተሻለ በመተንተን የምናጣራው ይሆናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## V) <u>ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ</u>

### 1) <u>በወቅቱ ያልተከፈለ (ያልተወራረደ) ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 33,769,154.94 መኖሩ</u>

***ግኝት***

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከ ሀ-ሠ በተዘረዘረው መሰረት በየቅ/ጽ/ቤቱ በሂሳብ መግለጫ ላይ ለታየው ተከፋይ ሂሳቦች የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ከ 2001 እስከ 2009 ዓ.ም ሳይወራረዱ የቆዩ የተከፋይ ሂሳቦች በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 33,769,154.94 መኖሩ ታውቋል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 40 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

ተከፋይ ሂሳቦች ትክክለኛነታቸው እየተረጋገጠ ምዝገባ ካልተከናወነ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቱንም ላልተፈለገ ዕዳ (ክፍያ) ሊዳርግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ተከፋይ ሂሳቡ በደንብና መመሪያው መሰረት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት መከፈል የሚገባ ሲሆን ሂሳቡ የሚከፈለው አካል ማወቅ ያልተቻለውን ሂሳብ ወደ ገቢ በመቀየር ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

***የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት***

- በግኝቱ ከተገለጹት ተከፋይ ሂሳቦች ውስጥ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የዞረ የፋክስ ሂሳብ ሲሆን በወቅቱ ሰኔ መዝጊያ ላይ የምዝገባ ማስተካከያ መሰራት ሲገባው ባለመሰራቱ እየዞረ የመጣ መሆኑ፣
- አንዳንድ ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከተው ሰራተኛ የተከፈለ ሆኖ በወቅቱ ከመዝገብ መሰረዝ ሲኖርበት ባለመሰረዙ ሲሆን በአጠቃላይ የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ባለመሰራቱ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑን፣
- የተከፋይ ሂሳብ 5006ን በተመለከተ ብር 1,093.20 በ2009 ዓ.ም ለገቢ ሂሳብ መተላለፍ ሲገባው ሳይተላለፍ ለማዕከላዊ ግ/ቤት ፈሰስ የሆነ የዊዞሆልዲንግ ክፍያ ሲሆን በሀምሌ ወር ተጠይቆ የተከፈለ መሆኑን፣
- የተከፋይ ሂሳብ 5007ን በተመለከተ ብር 402.00 በ2009 ዓ.ም የወጪ መጋራት ክፍያ ከደሞዝ ተቀንሶ ሳይከፈል የቀረ ነገር ግን በCPV የተከፈለ ሲሆን የአመዘጋገብ ስህተት የተፈጠረ በመሆኑ በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

- በ5051 በአደራ የተያዘውን ገንዘብ ደንበኞች በወቅቱ መወሰድ ሲገባቸው ያልተወሰዱ በመሆኑ፣
- ከዋጋ እና ታሪፍ ምላሽ እስኪመጣ፣ በጉ/ስ/ስ እና በPCA በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ በማቅረባቸው ምክንያት እና የህግ ማስከበር ዕቃዎቹ ምግብ ነክ በመሆናቸው ምክንያት

የፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመጠቀሚያ ግዚያቸው እንዳያልፍ በጨረታ የተሸጠ በአደራ የተያዘ መሆኑን፣

- በሂሰብ መደብ 5054 ላይ ያለ ተከፋይ ሂሳብ በቀጣይ ከህግ ማስከበር ም/ስ/አስኪያጅ ጋር በጋራ በመነጋገር ውሳኔ የምንሰጥበት መሆኑ ማለትም የሚከፈለው ሰው ካለ አስፈላጊው መረጃ ማያያዝ ወደ ቀጥታ የሚዞር ከሆነ ግን ወደ ቀጥታ የዞረበት መረጃ የምናቀርብ ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***<u>የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ያልተወራረደ ተከፋይ ብር 39,757,294.09 በተመለከተ ብር 27,757,018.08 ስለመወራረዱ መረጃዎች አለመቅረባቸው የተገለፀ ቢሆንም መረጃዎቹ ወጥተው ዝርዝሩ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ቀርቦ በኦዲተሮች እንዲታዩ አድርገናል በማለት በስራ አመራር ሪፖርት ላይ ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ማስረጃ የቀረበለት የተከፋይ ሂሳብ የብር 17,325,355.22 ሲሆን ቀረበ የተባለውም ሰነድ ያልተሟላ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

***<u>የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>***

የሂሳብ አያያዝ ስርዓቱ ከIBEX ወደ IFMIS ሲለወጥ ባለመስተካከሉና ቀደም ሲል ምዝገባ የተከናወነበት ሲስተም IBEX የተዘጋ መሆኑን ተገንዝበን ከሃምሌ 2003 ዓ.ም ጀምሮ በExcel ከእያንዳንዱ ሰራተኛ የተሰበሰበው የረዥም ጊዜ ብድር ተመዝግቦ በማጣራት ላይ የምንገኝ ሲሆን ጥረቱ ካልተሳካ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሂሳቡ ከመዝገብ የሚሰረዝበትን ሁኔታ የምናመቻች ይሆናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ ሲሆን ብር 144.91 ከመዝገብ እንዲሰረዝ የውሳኔ ሃሳብ ለጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ያቀረቡ መሆኑን እና በውስጥ ኦዲት ቡድን በኩል እንዲረጋገጥ የተመራ ሲሆን የውስጥ ኦዲት ቡድኑ ባለማረጋገጡ የተነሳ ተገቢው እርምጃ አለመወሰዱን በስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ላይ ከገለጹት በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ላይም ገልጸዋል፡፡

***<u>የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- የጨረታ መስከበሪያ ተከፋይ የሂሳብ ግለሰቦቹ መጥተው እንዲወስዱ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም በአድራሻቸው ሊገኙ ስላልቻሉ ያልተመለሰ ሂሳብ ሲሆን በቀጣይ ለመመለስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣

- የኪራይ ገቢ ግብር በቅ/ጽ/ቤቱ የገቢ እቅድ ያልተያዘ ሲሆን የኪራይ ገቢ ግብር የመሰብሰብ መብትና ስልጣን የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን በመሆኑ ከዋናው መ/ቤት በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት በተከፋይ ተይዞ የቆየና ወደፊት በምን መልኩ መከናወን እንዳለበት በሚሰጠን አቅጣጫ መሰረት ተገቢው የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

2) **<u>በቂ ማስረጃ የሌላቸው የተከፋይ ሂሳቦች በድምሩ ብር 79,470,004.62 መኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈፀምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚኖርበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር ቅ/ጽ/ቤቶች በሰኔ 30/2009 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ላይ ሪፖርት ላደረጓቸው ተከፋይ ሂሳቦች በቂ ማስረጃ ያላቸውና በትክክል የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እዳ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ማስረጃ ሳይኖረው በሂሳብ ሪፖርት ላይ ሪፖርት የተደረገ ተከፋይ ሂሳብ በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 79,470,004.62 መኖሩ ታይቷል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 41 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

ማስረጃ የሌላቸው ሂሳቦች በተከፋይነት የሚያዙ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ይከፍታል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

በተከፋይ ሂሳብ ለመመዝገብ ሂሳቦቹ ተገቢው ማስረጃ ሊኖረው ስለሚገባ የሂሳቡን ምንነት በማጣራት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ተከፋይ ሂሳቡ በ2005 በጀት አመት የኦዲት ግኝት ወቅት የተገኘ እና እየተንከባለለ የመጣ በበላይ ባለስልጣን በኩል እንዲሰረዝልን ጥያቄ ያቀረብን ቢሆንም መረጃውን አጥርታችሁ አቅርቡ በመባሉ ኮሚቴ ተቋቁሞ መረጃ የማጥራት ስራ እየተሰራ ያለ ሲሆን መረጃውን

አሰባሰበን ለዋናው መ/ቤት ለመላክ በዝግጅት ላይ መሆናችን ይታወቅ፡፡ በተጨማሪም ሂሳቡ ከ10 አመት በላይ የቆየና ትክክለኛ መረጃው ባለመገኘቱ በየአመቱ በኦዲት ግኝት እየተያዘ የመጣ መሆኑ በኦዲት ስብሰባ ላይ ገልጸናል በማልት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

***የጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

ተከፋይ ሂሳቡን አስመልክቶ በቅ/ጽ/ቤቱ በቂ ማስረጃ ሊገኝለት ባለመቻሉና ገንዘቡ በሰኔ 30/2005 ከኢትዮጲያ ንግድ ባንክ ጅማ አብይ ቅርጫፍ ከሚገኘው አካውንታችን ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ፈሰስ የተደረገ በመሆኑ የተፈጠረ ችግር ሲሆን፣ የተከፋይ ሂሳቡን አስመልክቶ በቃለ ጉባዔ እንዲደሰረዝልን የተስማማን ስለሆነ የሚመለከተው አካልም እንዲሰረዝልን ያላደረገ በመሆኑ እስካሁን በሪፖርቱ ላይ ሊታይ እንደቻለ ከሰጡት ምላሽ እና ማስረጃ ብለው ካቀረቡት ሰነድ ለማየት ተችሏል፡፡

***የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት***

አብዛኞቹ ተከፋይ ሂሳቦች ከ2006 ጀምሮ የታዩ ሲሆን ይህም የተፈጠረው ከIBEX ወደ IFMIS ዳታ ሲተላለፍ በመሆኑ IFMIS አስተግባሪዎች ጋር በመነጋገር በቀጣይ የተደረሰበትን የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን፡፡ የድርጊት መርሃ ግብርም በማውጣትና የማስተካከያ እርምጃ በመውስድ የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

***የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት***

ተከፋይ ሂሳቡን በተመለከተ በተቻለ መጠን ጊዜ ሳይሰጥበት ሂሳቡን በማስተካከል ማስተካከያ የተደረገበትን ሪፖርት የምናደርግ ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የዋና መ/ቤት***

በሲስተም በተከፋይ ተመዝግቦ ከአይ ቤክስ ወደ ኢፍሚስ በጥቅል የተላለፈ በመሆናቸው ምክንያት በሀርድ ኮፒ ወይም በማንዋል ለመለየት በማስቸገሩ ማስረጃውን ለማቅረብ ያልተቻለ በመሆኑ ወደፊት ለማን ለማን የሚከፈል እንደሆነ በማጣራት ማስረጃውን የምናቀርብ ይሆናል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ስብሰባ ላይ በተሰጠ ምላሽ መሰረት ማስረጃ ያለ መሆኑን ገልጸው ከመውጫ ስብሰባ በኋላ የሚያቀርቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ይቀርባል የተባለ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ በቀጣይ የስራ ክፍሉ በየትኛው ዲ.ዮን ቁጥር፣ መቼ ጀምሮ፣ ምክንያቱን እና ምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የሚያሳይ ግልፅ የሆነ ማስረጃ በመያዝ የዋስትና ሂሳቦች ላይ በህጉ መሰረት የቆይታ ጊዜው ላይ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በኮድ 5026 ፣ 5028 ብር 354,753.73 በተከፋይ ሂሳቦች ተይዞ ከዚህ በፊት እየተንከባለለ የመጣ ብር 82,455.03 ሲሆን በኮድ 5026 የተያዘው ተከፋይ 272,298.70 ደግሞ በ2009 በጀት ዓመት የየካቲት እና ሰኔ ወር ባለው ጊዜ ውስጥ በአይቤክስ ሲስተም በጀመረበት ጊዜ የምዝገባ ስህተት ሊኖር ይችላል ብለን አምነንበት ከዋናው መ/ቤት ገቢ ሂሳቦች ካሉት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር Ifmis system ከመዘርጋቱ በፊት በዚሁ ልዩነት እንዳለ ሂሳቡን በመዝጋት ለ2010 በጀት ዓመት ሂሳቡን ተናበን እንደምናስተካክል ተነጋግረን ሂሳቡን ዘግተው ሪፖርት የላኩ መሆኑን እና ሂሳብ መደብ 5002 ከ2006 ዓ.ም በፊት፤ 5004 ከ2006 ዓ.ም፤ 5061 ከ2006ዓ.ም በፊት ሲንከባለል የመጣ ተከፋይ ሂሳቦች መሆናቸውን በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

## VI) <u>የሂሳብ ሪፖርትን በተመለከተ</u>

### 1) <u>የ2009 በጀት ዓመት በቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር እኩል አለመሆኑ</u>

**ግኝት**

በ2009 በጀት ዓመት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ተጠቃሎ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ፣

- የወጪ ሂሳብ ብር 12,183.80 በመብለጥ እና ብር 11,538.80 በማነስ፤

- በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ በድምር ብር 488,654.68 በማነስ እና ብር 6,901,617.54 በመብለጥ፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ በድምር ብር 7,043,961.69 በመብለጥ፣ ብር 21,379.07 በማነስ ፡
- የገቢ ሂሳብ በድምር ብር 76,227,364.01 በመብለጥ፣
- የጥሬ ገንዘብ እና ባንክ ሂሳብ ብር 1,099,881.12 ዴቢት በማነስ፣ እንዲሁም ብር ብር 1,873,765.63 ዴቢት በመብለጥ፣
- የተጣራ ሀብት የሂሳብ መግለጫ ድምር ብር 37,840,864.05 በክሬዲት በማነስና 42,613,421.78 ዴቢት በማነስ፣

የሚያሳይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## ስጋት

ባለስልጣን መ/ቤቱ ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛ የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ ላያሳይ ይችላል፡፡እንዲሁም የተዛባ የመረጃ አያያዝ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## የማሻሻያ ሃሣብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ መደብ በሚያሳይ መልኩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## የባለስልጣኑ የፋይናንስና የገቢ ሂሳቦች ዳ/ቶሬቶች ምላሽ

የጥሬ ገንዘብ፣የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ

- ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ለሁለት ዓመት ከ IFMIS system ተጠቃሚ ቅርንጫፎች ወጪ ያሉትን የ13 ቅርንጫፎች opening balance በያመቱ መጀመሪያ ባለመያያዙ ቋሚ የሆኑ የሂሳብ መደቦች (permanent account) ላይ የ IFMIS report እና የቅርንጫፍ የተጠቃለለ ሪፖርት አይናበብም ነበር። በመሆኑም ይህ ልዩነት ምክኒያት በማጣራት ለማስተካከል የ2009 ዓ.ም opening balance ጨምሮ የ3 ዓመት በማዘጋጀት በ2010ዓ.ም የተስተካከለ መሆኑን፣

**የገቢ ሂሳብን በተመለከተ፣**

**<u>የግዥ እና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ምላሽ</u>**

- 1101 ላይ እንደ ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ልዩነት የሌለ ሲሆን
- በሂሳብ መደብ 1489 ላይ ግን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ላይ ያልተስተካከለ ምስገባ በመኖሩ በዋናው መ/ቤት እንደ ሀዋሳ ቀርንጫፍ በመሆን የተመዘገበ ሲሆን ልዩነቱም የተፈጠረው በዚህ ምክኒያት ነው በመሆኑም ሰኔ 30/2009 በdocument number 8363 ማስተካኪያ የተደረሰበትን ሰነድ አያይዘን ልከናል።

**የተጣራ ሀብት በተመለከተ ፣**

- በገቢ ሂሳቦች አስተዳደር በኩል በተሰጠ ምላሽ ብር 663,647 የሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት እና ብር 81,398.50 የኮምቦልቻ ቅ/ፅቤት በድምሩ ብር 745,045.89 በገቢ ሂሳቦች የተጠቃለለ የዕርማት ምዝገባ የሚከናወንለት መሆኑን፣
- በግዥና ፋይናንስ በኩል ከ አዲስ አበባ ውጭ ያሉ የ13 ቅርንጫፎች ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ opening balance ሳይያዝባቸው በየአመቱ ምዝገባ የተደረገ በመሆኑ ልዩነት መፈጠሩን አረጋግጠን በ2010 በጀት ዓመት ሀምሌ 2009 ዓ.ም ላይ ማስተካኪያ የተደረገ መሆኑን ፣

ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

- በሂሳብ ኮድ 1101 ልዩነት የለም ቢባልም በድጋሚ ተጣርቶ ልዩነቱ የሚታይ በመሆኑ ልዩነቱ ስላለመኖሩ ማስረጃ ባለማቅረባቸው፣
- በሂሳብ ኮድ 1489 በዋናው መ/ቤት ማስተካኪያ ቢያደርግም ነገር ግን በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ያልተስተካከለ እና የተጠየቀው የገንዘብ መጠን እና የቀረበው ማስረጃ የማይጣጣም በመሆኑ ፣
- የተጣራ ሀብት በተመለከተ ዴቢትን ክሬዲት ሚዛንን በማጣፋት የጠሰራ ስለሆነ

የተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም

## 2) <u>በቅ/ጽ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 167,544,565.83 መኖሩ</u>

**<u>ግኝት</u>**

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት በቅ/ጽ/ቤቶቹ በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ላይ እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ሪፖርት በተደረገው የሂሳብ መግለጫ ላይ ያልተለመደ ሚዛን(abnormal balance) የሚያሳዩ የሂሳብ መደቦች በ 8 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 167,544,565.83 መኖሩንና ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ ተካክሶ መጥፋቱ ለማየት ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 42 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

እያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ዴቢት እና ክሬዲት ጠብቆ የማይመዘገብ ከሆነ የቅ/ጽ/ቤቱን የሂሳብ መግለጫ የተሳሳተ ያደርገዋል፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

የሂሳብ መደቦቹ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቁበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ተጣርቶ ሊስተካከል ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

***<u>የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- ረዥም ጊዜ ያስቆጠረና የበጀት ካሼሮች በብልጫ የከፈሉ ከ2000 በጀት ዓመት ጀምሮ በሪፖርት እየታየ የመጣ በመሆኑ በቀጣይ ከዋና መ/ቤት ጋር በመነጋገር እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት የሂሳብ መዝጊያ ላይ ትክክለኛ ያልሆነ የባንክ ሚዛን ብር 1,118,824.95 የነበረ ሲሆን በተለያየ ጊዜያት የሂሳብ ሰነዶችን በማፈላለግና የሂሳብ ምዝገባዎችን በማከናወን ወደ ብር 897.52 ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን  አካውንት ቁጥር 1962 በአሁኑ ሰዓት እየተጠቀምንበት ያልሆነ እና የተዘጋ በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ

ሰነዶቹ የቆዩና ብዛት ያላቸው በመሆናቸው ሰፊ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ሰነዶቹን በማፈላለግ የማጥራት ስራ ተጀምሮ በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

- የተጣራ ሀብት የሂሣብ ቁጥር ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን ብር 21,434,133.00 ዴቢት የሚያሳይ መሆኑ ተብሎ የተገለፀውን በተመለከተ የክልሎችና የከተማ መስተዳደሮች ድርሻ ወር ባለቀ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ ተከፋፍሎ ወደ ዋና መ/ቤት የሚላክ በመሆኑ የተሰበሰበው ገቢ ግን በየጊዜው (በየቀኑ) ወደ መንግስት ትሬዥሪ ፈሰስ የሚደረግ የሂሣብ ልዩነት ሊፈጠር ችሏል፡፡ ይህን ጉዳይ በምን መልኩ ማስተካከል እንዳለብን ዋና መ/ቤት ተጠይቆ በአመቱ መጨረሻ ወር (ሰኔ) እስከ 25 ድረስ ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የክልሎችና ከተማ መስተዳደሮች ድርሻ ሰኔ 30 ሳያልፍ እንዲተላለፍ አቅጣጫ ተሰጥቶ ሲሰራ የተጣራ ሀብት የሂሣብ ሚዛን ከብር 21,434,133.00 ወደ ብር 15,704,495.91 ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ በቀጣይ የተጣራ ሀብት የሂሣብ ሚዛን ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን እንዳያሳይ የተሻለ የመፍትሄ አቅጣጫ በፌደራል ዋና ኦዲተር እንዲሰጥበት እንጠይቃለን ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

**<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>**

ባለፉት ዓመታት የኦዲት አስተያየት ላይ ያልተለመደ ሚዛንን አስመልክቶ እርምጃ እንዲወሰድበት አስተያየተ ተሰጥቶበት እርምጃ ያልተወሰደበትን አስመልክቶ በደብዳቤ ቁጥር 8.0/46/22 በቀን 15/07/09 በተጻፈልን የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የማስተካከያ አቅጣጫ ሲሰጥበት ተብሎ በድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ የተገለጸ ቢሆኑም ዳይሬክቶሬቱ እስካሁን ድርስ ምላሽ አለመስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

***<u>የጅማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በሂሳብ መዝጊያ ወቅት ላይ ተከፋይ ሂሳብ ክፍፍል ተደርጎ ከቀን 25-30 ያለው ገንዘብ ስለነበር ሲዘጋ ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ያሳየ ቢሆንም በቀጣይ በጀት ዓመት መነሻ ላይ ክፍፍል ተደርጎ ተላልፏል እነዲሁም በሂደት የሚስተካከል ይሆናል ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት***

***ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን የሚያሳይ የተጣራ ሀብት ብር 6,611,570.23 ጉዳይ የሂሣብ ዝርዝር ሁኔታ ታይቶ በተቻለ መጠን ሂሳቡን ለማስተካከል ጥረት መደረግ ይኖርበታል በማለት ገልጸዋል፡፡***

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

***መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የታየበት ሂሳብ ስራው ችግር ሳይሆን መመንዘሪያ አካውንታችን ተዘግቶ በብሎክ አካውንት በመጠቀማችን የተነሳ እና መረጃ ሳይመጣለት ወደ GOV፤ 1181 (ዲፖዚት) ለማዞር በመቸገራችን የተነሳ እና ሂሳቡን በምንዘጋበት ወቅት ለመዝጊያ የተጠቀምንበት በመሆኑና ለወደፊትም ቢሆን በባንክ ሊስተካከል ካልቻለ የክልሎችን ድርሻ ዊዝሆልድንግ እና የቫት ዊዝሆልዲንግ ተከፋይ ለማሳየት በባንካችን ባላንስ ስለማይኖር ብር ፈሰስ ስለሚሆን (asset equity) አሴት ኢኩቲ ላይ መደበኛ ያልሆነ ባላንስ እንዲታይ የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ ይህንን ነገር ለማስተካከል እንደተቋም ሊወሰድ የሚችል መፍትሄ እስካልመጣ እና የክልሎችን ድርሽ በሲስተም የሚሰራበትን ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ችግሩን ማጥፋት አይቻልም፡፡ ይህ ቸግር ተቋሚዊ ችግር ሲሆን ችግሩንም ለመፍታት ከዋናው መ/ቤት ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በመፍትሄው ዙሪያ ለመነጋገር የተሞከረ ቢሆንም ችግሩን የሚፈታ መፍትሄ ሊቀርብ አልቻለም፤ስለሆነም ይህን ችግር በቅርጫፍ ደረጃ ለመፍታት አይቻልም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡***

***የዋና መ/ቤት***

***ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳይ የB ባንክ ሂሳብ ሌጀር ብር 690,263.24 ወደፊት የማጣራት ስራ ተሰርቶ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል በማለት በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡***

***የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት***

***በገቢና ዋስትና አስተዳደር ቡድን ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት ብር 428,768.51 የሚያሳይ መሆኑን በተመለከተ ችግሩ የተፈፀመው ከረጅም ዓመት በፊት ሲሆን ማስተካከያ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም ችግሩን ለመፍታት ከቅ/ፅ/ቤቱ አቅም በላይ በመሆኑ ለዋና መስሪያ ቤት በደብዳቤ ቁጥር 8.81.1/12/1429 በቀን 23/10/2009 መፍትሄ እንዲሰጥበት የገለፅን ሲሆን በቀጣይ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ማስተካከያ የሚደረግ መሆኑን እንገልፃለን በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡***

***የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት***

የተጣራ ሃብት ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚያሳየው የጋራ ገቢ እና የክልሎች ድርሻ ተከፋይ በሰኔ ወር እስከ 30 ቀን ከግብር ከፋዮች እና ከመንግስት ተቋማት በወሩ በሚሰበሰበው የገቢ ሰነዶች ተጠቃለው ስለማይደርሱ እና በአብዛኛው ገቢ የሚሰበሰበውም በወሩ መጨረሻ ስለሆነ ከወሩ ገቢ የክልሎችን ድርሻ በመለየት የሂሰብ ሥራው የሚጠናቀቀው ከሰኔ ወር በኋላ የወሩ ሪፖርት ሲጠናቀቅ በቀጣይ ወር ከሰኔ በፊት ያሉትን ተከፋይ ሂሳቦችን ቀንሰን የምናስተለለፍ ሲሆን በሰኔ ወር ግን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከገንዘብ/ኢ/ት/ሚ/ር በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ገንዘቡን ሰኔ 30 ላይ ሙሉ በሙል ወደ ትሬዠሪ ፈሰስ የሚያደርገው በመሆኑ የሰኔ ወር ተከፋይ የጋራ ገቢ እና የክልሎች ድርሻ ያልተላለፈ (ያልተከፈለ) ስለሚኖር የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በሚዘጋበት ጊዜ የተጣራ ሀብት (5601) ያልተለመደ ወይም ዴቢት ባላንስ እንዲታይ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ወደፊትም የገንዘቡን መጠን መቀነስ የሚቻል ቢሆንም ይህንን ያልተገባ የሂሳብ ሚዛን ከመታየት ማስቀረት የማይቻል መሆኑ ይታወቅልን በማለት በመውጫ ስብሰባ እንዲሁም በስራ አመራሩ ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

በመውጫ ውይይት ወቅት በተያዘ ቃለ-ጉባኤ በሰኔ ወር የተሰበሰበው የፌደራል እና የክልል ድርሻ የሆነው ገቢ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባስተላለፈው ገንዘቡን በየ3 ቀኑ ፈሰስ እንዲሆን ለባንኮች ስለተሰጣቸው የክልሉ ድርሻ የሆነው ሳንከፍል ጠቅላላ ገንዘቡ ፈሰስ በመሆኑ ተከፋይ ይዘን ስለቀረን 5601 ዴቢት እንዲሆን ተገደናል ይህን የክልሎች ድርሻ በተከፋይ የተያዘው በሐምሌ ወር ስለሚከፈል ነው፡፡ ይህን ለቀጣይ አንድ መፍትሔ የሚሆነው በሰኔ ወር የሚሰበሰብ በሐምሌ ወር ከፍለን ከጨረስን ፈሰስ ቢሆን የተሸለ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 3) <u>በባንክ ማስታረቂያ ላይ የተመለከተው የባንክ ሚዛን እና የመዝገብ ሚዛን በብር 858,906,466.18 ልዩነት የሚያሳይ መሆኑ</u>

***ግኝት***

የመንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት (8) (መ) የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት

በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንዳለበት ያዛል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚዘጋጁ ሂሳብ ሪፖርቶች ከባንክ ማስታረቂያው ጋር እየተመሳከሩ ሪፖርት የሚደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በተዘጋጀው የባንክ ሂሰብ ማስታረቂያ(bank reconciliation) ላይ በመዝግብ ሚዛንና ባንክ ሚዛን መካከል ልዩነት የሚታይ ሲሆን የልዩነቱ ምክንያት ባለመታወቁ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 858,906,466.18 ልዩነት መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 43 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**ስጋት**

የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የመ/ቤቱን ትክክለኛ የሂሳብ እንቅስቃሴ ላያሳይ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

የባንክ ማስታረቂያው ልዩነት ተጣርቶ የባንክ ማስታረቂያውም ሆነ የሂሳብ ሪፖርቱ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

**የቅ/ጽ/ቤቶቹ የሥራ አመራር ምላሽ**

*በአ/አ/ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*

- ይህ ሂሳብ የሚነሳው ከ99 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ባንኩና መዝገብ በዚህ ልዩነት አብሮ ይንከባለል የነበርና JV ሳያልፍለት የቀረ ሰነድ በመሆኑ፣
- ከዚህ በፊት የነበሩት ሰራተኛ ጡረታ በመውጣታቸውና አስታውሰው መረጃ መስጠት ባለመቻላቸው ችግሩ ምን እንደሆነ እስካሁን ለማወቅ ባለመቻሉ፣
- IBEX ከመምጣቱ በፊት ሂሳቡ ከንግድ ባንክ ወደ ብሔራዊ ባንክ ሲተላለፊ እኩል እስከምመጣ መሰራት ሲገባው ባለመሰራቱ፣
- IBEX ላይ የነበረው ባላንስ ወደ IFMIS ሲመጣ ባላንሱ ሳይስተካከል እንዲስተላለፍ በመደረጉ የተፈጠረ ችግር በመሆኑ በቀጣይ ችግሩን ለመፍታት የሚሰራ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

*የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*

ከIFMIS ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር ችግሩ ቅ/ጽ/ቤቱ ስህተት ኑሮበት ሲያስተካክል የገቢ መጠኑ በተሰበሰበበት ቀን ሳይሆን በደረሰበት ቀን ስለሆነ IFMIS ላይ የሚታየው በተስተካከለበት ቀን ይሆናል ነገር ግን የወረቀት ስራው ማስተካከያ ተደርጎለታል በማለት

በስራ አመራር ምላሽ ላይ የገለጹ ሲሆን በመውጫ ስብሰባ ላይም ማስተካከያ የተሰራበት ከስብሰባ በኋላ ቀርቦ እንዲታይ የሚደረግ መሆኑን ከስምምነት ተደርሷል፡፡

**የኦዲተሩ አስተያየት**

በመውጫ ስብሰባ ላይ ተስተካክሏል የተባለው ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብ እና እንዲታይ በተባለው መሰረት በባንክ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የሚታየው ብር 856,391,040.34 ማስረጃ ባለመቅረቡየተሰጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

## 4) ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ በካዝና የሚገኝ ብር 5,000.00 የሚያሳይ CPO በሂሳብ ሪፖርት ተካቶ መገኘቱ፣

**ግኝት**

በ2009 በጀት ዓመት ሰኔ 30 ላይ በውስጥ ኦዲት በኩል በካዝና ወይም ሳጥን ውስጥ የተቆጠረ ገንዘብ በዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ላይ የተገለጸው በእጅ ያለ ገንዘብ ጋር ልዩነት አለመኖሩን ይም ልዩነት ካለም ማስታረቂያ መሰራቱን ለማረጋጋጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ***በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** በ2009 በጀት ዓመት በውስጥ ኦዲት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሪፖርት ዝርዝር መሰረት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ሲዞር የመጣ እርምጃ ሳይወሰድበት የተገኘ በቁጥር 2290514 የ Fraz International plc ብር 5,000.00 CPO በካዝና ውስጥ የሚገኝ መሆኑና ይህም ሂሳብ በሪፖርት የተመለከተ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.3/6 *ቀን 01/06/2010 ግኝት ቁጥር 3.2 ላይ ይገኛል)*

**ስጋት**

ወቅቱን የጠበቀ ለመንግስት መግባት ያለበት ገቢ ተከታትሎ የማይገባ ከሆነ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል ፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ቅ/ጽ/ቤቱ ጉዳን አጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሊያደርግ ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ስህተቱን ለማረም ሰፊ ጥረት አድርገን ሊስተካከል አለመቻሉን እና ግኝቱ እንደደረሰን ግን በ13/04/2010 ዓ.ም በተፃፈ ውስጣዊ ማስታወሻ CPO ከተዘጋጀ ከስድስት ወራት በላይ የቆየና የማያገለግል መሆኑን ተገንዝበን እና ባለቤት ነኝ ብሎ የቀረበ አካል ባለመኖሩ

እንዲወገድ በማለት ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ አቅርበናል በማለት በስራ አመራር ምላሽ ላይ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 5) <u>በአደራ ባንክ ሂሳብ ላይ በሚታየው የክልልና የከተማ መስተዳደር የአደራ ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ባለመያዙ የታየ ልዩነት ብር 12,702,299.06 ስለመኖሩ ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(5) ሠ መሰረት የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴዎች በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ አለባቸው በሚለው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ***ዋና መ/ቤቱ*** ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳደር ለመክፈል ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ሌሎች መ/ቤቱች የሰበሰበው የአደራ ሂሳብ በአደራ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 010019104192 ላይ ብር 110,622,643.26 የሚታይ ሲሆን በ5026 ለክልሎች እና ከተማ መስተዳደር ድርሻ ገቢ በተከፋይ በሪፖርት የተያዘው ሂሳብ ግን ብር 97,920,344.00 በመሆኑ በልዩነት ብር 12,702,299.06 በአደራ ባንክ ሂሳብ የሚታይ ነገር ግን በተከፋይ ያልተያዘ መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.1/25 *ቀን 01/05/2010 ግኝት ቁጥር 2.2 ላይ ይገኛል)*

### <u>ስጋት</u>

በተከፋይነት የሚታየው ሂሳብ ባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ በሚታየው መሰረት ካልሆነ ትክክለኛ የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት እንዳይታይ ከማድረጉም በላይ የክልሎች እና ከተማ መስተዳደር ድርሻ በትክክል እንዳይከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡

### <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአደራ ተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚታየው ሂሳብ በአደራ ባንክ ሂሳብ ላይ በሚታየው መሰረት መሆኑን የሚመለከተው የስራ ክፍል ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ያለበት ሲሆን ያልተመዘገበውም የአደራ ሂሳብ በተከፋይ ሊመዘገብ ይገባል፡፡

### <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

ብር 8,763,811.00 ለገ/ኢ/ት/ሚ ቀርቦ የበጀት ዓመቱ ሂሣብ በሲስተም በመዘጋቱ ወደ ኢፍሚስ ገብቶ በሪፖርት ያልተካተተ ለገ/ኢ/ት/ሚ ማስተካከያ እንዲሰራ ያቀረቡትን ማስረጃ

አያይዘው በቀጣይ የሚስተካከል እንደሆነ መልስ የሰጡ ሲሆን ቀሪው ብር 3,938,488.06 ወደፊት በማጣራት የሚስተካከል መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

## 6) ለምን እንደተከፈተ ሰነድ ያልቀረበለት እና በመመሪያው መሰረት ለገ/ኢ/ት/ሚ በየሶስት ወሩ ሪፖርት ያልተደረገ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሂሳብ ብር 5,927,620.30 መኖሩ

**ግኝት**

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 23/3 ከውጭ አገር ዕቃ ለማስመጣትም ሆነ ለሌሎች ክፍያዎች ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለመክፈት የሚያስችላቸውን ማስረጃ አሟልተው ጥያቄቸውን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ለኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ አክስዮን ማህበር ማቅረብ አለባቸው በሚለው መሰረት እንዲሁም በአንቀጽ 26/1 ሪፖርት ስለማድረግ በሚገልጸው መሰረት ሌተር ኦፍ ክሬዲት እንቅስቃሴዉን በየሩብ ዓመቱ ሚኒስትሩ በሚያዘጋጀው ፎርም መሰርት ለሚኒስተሩ ሪፖርት ማቅረብ እንደሚኖርበት በሚገልጸው መሰረት **ዋና መ/ቤቱ** እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ስደረግ፡- ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሂሳብ ብር 5,927,620.30 ለምን እንደተከፈተ የሚያረጋግጥ ሰነድ ያልቀረበለት እና በየሩብ ዓመቱ እንቅስቃሴው ለሚኒስትሩ ሪፖርት እንደማይደረግ ለማወቅ ተችሏል፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.1/25 ቀን 01/05/2010 ግኝት ቁጥር 2.3 ላይ ይገኛል)*

**ስጋት**

በሌተር ኦፍ ክሬዲት ሰነድ ቀርቦ ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነ ከሚኒስትር መ/ቤቱ ቁጥጥር ውጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

መ/ቤቱ የሌተር ኦፍ ክሬዲት የከፈተበት ሰነድ አደራጅቶ በመያዝ የሌተር ኦፍ ክረዲት እንቅስቃሴ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስተር በመመሪያው መሰረት ሪፖርት ማቃረብ ይኖርበታል፡፡

**<u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

በቀጣይ በማጣራት የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ላይ ገልጸዋል፡፡

**7) <u>የሂሳብ እቅስቃሴ መነሻ ሰነድ ሳይኖር የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ብር 29,567,026.01 መኖሩ</u>**

**<u>ግኝት</u>**

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያየዝ መመሪያ 5/2003 እንቀፅ 6ሐ በሂሳብ ሌጀሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ሂሳቦች ሚዛን ተወስዶ ወርሃዊና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች በወቅቱ መዘጋጀት እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት እና በትክክለኛው የሂሳብ እቅስቃሴ መነሻ ሰነድ በተዘጋጀላቸው መሰረት በሂሳብ መዝገብ የሚመዘገቡ መሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ***በጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት*** ያለምንም ዓይነት የመነሻ ሰነድ የሂሳብ ምዝገባው የተፈፀመበት መነሻ ሰነድ የሌሌው ብር 29,567,026.01 በገቢ የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በዴቢትና በክሬዲት የተመዘገበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡ *(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.22/4 *ቀን 06/07/2010 ግኝት ቁጥር 3.1 ላይ ይገኛል)*

**<u>ስጋት</u>**

ቅ/ጽ/ቤቱ የሚያከናዉነው የሂሳብ ምዝገባ የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ ትክክል መሆኑን ተረጋግጦ የማይመዘገብ ከሆኑ የመንግስት ገንዘብ የሚባክንበት እና የተሳሳተ የሂሳብ መግለጫ ሊዘጋጅ ይችላላ፡፡

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

ቅ/ጽ/ቤቱ የሚያከናዉነው የሂሳብ ምዝገባ የተሟላ የመነሻ ሂሳብ ሰነድ መኖሩን እና
የማፅደቅ እና የመፍቀድ ኃላፍነት የተሰጣቸው የሰራ ሃላፊዎች የተረጋገጠ መሆኑን አለበት፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ምላሽ</u>**

የገቢ ሂሳቦች የምዝገባ ሂሳብ ማስተካከያ የተደረገ ምዝገባ መሆኑን በስራ አመራር ምላሽ ገልጸዋል፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

የመነሻ ሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ማስተካከያ የተሰራበት የማስተካከያ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹ አሳማኝ አይደለም፡፡

## 8) በ<u>ሌጀርና በሂሳብ ሪፖርት መካከል በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ልዩነቶች የሚታዩ መሆኑ</u>

**<u>ግኝት</u>**

*የፌሬራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያየዝ መመሪያ* 5/2003 *እንቀፅ* 6*ሐ በሂሳብ ሌጀሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ሂሳቦች ሚዛን ተወስዶ ወርሃዊና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች በወቅቱ መዘጋጀት እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶች የ*2009 *በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶችን የሚዘጋጁት በመመሪያው መሰረት መሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣* ***በጋላፊ የቅ/ጽ/ቤት*** *ከሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ የተወራረሰ የሂሳብ ሌጀር መዘጋጀት የነበረበት ወጪ፣ ተሰብሳቢ፣ ተከፋይ፣ ባንክ እና የካዝና የሂሳብ ሪፖርቶች በትክክል ሪፖርት ያልተደረጉ በመሆናቸው በሪፖርት የተገለጹት ሂሳቦች ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር* OFAGF-05.22/4 *ቀን 06/07/2010 ግኝት ቁጥር 3.2 ላይ ይገኛል)*

**<u>ስጋት</u>**

*ቅ/ጽ/ቤቱ የሚያዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት በመመሪያው መሰረት በሂሳብ ሌጀር የሚታየዉን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ካልሆነ የቅ/ጽ/ቤቱ ሂሳብ ሪፖርቱ ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡*

**<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

*ቅ/ጽ/ቤቱ የሚያዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው በእለቱ በየፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ ምዝገባ ወደ የሂሳብ ሌጀር በማወራረስ ትክክለኛነቱ በማረጋገጥ የሂሳብ ሪፖርቱ መዘጋጀት አለበት፡፡ ትክክለኛው ሁኔታ ተጣርቶ የሂሳብ ሪፖርቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡*

**<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

*ምላሽ አልተሰጠም*

## VII <u>ንብረት አስተዳደር በተመለከተ</u>

## 1) <u>የቅ/ጽ/ቤቶች ንብረት አስተዳደር በተመለከተ</u>

**<u>ግኝት</u>**

*የንብረት አስተዳደርን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር* 649/2001 *እና በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር* 9/2003 *መሰረት ተገዝተው ወደ መ/ቤቶች*

የገቡ ንብረቶችን በትክክል መግባታቸውን፣ ወጪ መደረጋቸውን እና ምዝገባ መኖሩን የሚያሳይ መዝገብ መቋቋሙን እንዲሁም ንብረቶቹ በአግባቡ መጠበቃቸውን አና ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ የመንግስት ንብረት ለመጠበቅ የተሟላ የቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች፤

- በአላቂ ንብረት ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች ለመቆጣጠር እንዲያመች በየእቃዎች ዓይነት ትክክለኛነት መከታተያ ቢን ካርድ የሌለ መኖሩ፣
- የስቶክ ካርድ አሰራር በተሟላ ሁኔታ የማይጠቀም፣ የስቶክ ቆጠራ ከመዝገብ የማስታረቅ ስራ የማይሰራ መሆኑ፣
- በእያንዳንዱ ሰራተኛ ስር ያለን ንብረት ለመቆጣጠር የተዘጋጀው ዩዘር ካርድ ትክክለኛ መረጃ ያልተያዘ መኖሩ፣
- የተወረሱ እቃዎች ተደባልቆ ከመ/ቤቱ ንብረቶች ጋር የሚገኙ መኖሩ፣
- ቋሚ ንብረቶች የራሳቸው የሆነ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው የሚገኙ መሆኑ፣
- በአላቂ እቃ መጋዘን ውስጥ እቃዎች በየአይነታቸው በዕቃ ማስቀመጫ ሼልፍ ላይ ተደርድረው ለመቆጣጠር በሚያመች መልኩ ያልተቀመጡ መሆኑ
- የተለያዩ ፈርኒቸሮች፣ ህትመቶች እና መዛግብት፤ ኤሌክትሮኒክሶች፡ ኮምፒተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች እና ጎማዎች፣ የብረታ ብረት ቁሳቁሶች በአግባቡ ሳይያዙ ከመኖራቸውም በተጨማሪ ተጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጥ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ እንዲወገድ ያልተደረገእና ንብረቶች መኖራቸው፡-
- በንብረት ገቢ እና ወጪ ደረሰኝ የተመዘገቡ ዕቃዎች በስቶክ መዛግብቶች ላይ ያልተመዘገቡ ንብረቶች መኖራቸው
- በተለያየ ምክንያት ስራቸውን የለቀቁ ሰራተኞች እጅ የነበሩ ንብረቶች ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ያልተደረጉ እና የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መኖራቸው
- የተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እና የተሽከርካሪ ህይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ ያልተያዘ የሚገኝ መሆኑ፡፡
- በየነዳጅ አጠቃቀም ላይ ምዝገባ የማይደረግ እና ቁጥጥሩም የላላ መሆኑ
- የእቃዎች መጋዘን የሌለው እና የራሳቸው ባልሆነ ተንቀሳቃሽ ኮንቴነር ውስጥ ተቀምጦ የሚገኝ ንብረቶች መኖራቸው፣

- በግቢው ውስጥ የሚገኙት ኮንቴይነሮች መቼ እንደገቡ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደቆዩ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በቅ/ጽ/ቤቱ የሌለና ያሉበትን ሁኔታ በሚመለከት ከደረቅ ወደብ አስተዳደር ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥም ስርዓት የላላ መሆኑ

ለማየት ተችሏል፡፡ *(ግኝቶቹ በአባሪ 44 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

**<u>ስጋት</u>**

የመንግስት ንብረት በመመሪያው መሰረት አጠባበቅ የማይደረግላቸው ከሆነ ቢበላሽ፤ ቢጠፉ ወይም ቢጎድል በወቅቱ ለመቆጣጠር ፤ለማስተካከል ተጠያቂነት ለማስፈን የማያስችል ከማድረጉም በተጨማሪም የመንግስት ንብረት ለብልሽት እና ብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>**

በየቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች የቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን የሚወገዱ ንብረቶችም እንዲወገዱ ጥረት በማድረግ በአጠቃላይ በቅ/ጽ/ቤቱ አስተማማኝ የሆነ የንብረት አያያዝ ስርዓት እንዲኖር ሊደረግ ይገባል፡፡በእያንዳንዱ ግለሰብ የታየው የንብረት ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

**<u>የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምለሽ</u>**

***የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት***

- ቋሚ እቃዎች የተወሰኑ ቁጥር ያልተሰጣቸው በመኖሩ በቀጣይ በወቅቱ ከንብረት ክፍል ሲወጣ ቁጥር እየተሰጣቸው እንዲወጣ ክትትል የሚደረግ መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ የሚወገዱ ንብረቶች ለብቻው መጋዘን ያለው ሲሆን ተጠግነው አገልግሎት ላይ የሚወጡ ንብረቶችን በዋናው መጋዘን አስቀምጠን ተጠግኖ ለስራ ለሚፈልግ አካል እየተሰጠ የሚገኝ መሆኑ፣
- በቋሚ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ በ2009 በጀት አመት ቋሚ እቃዎችን ያስወገድን ሲሆን የተሽከርካሪ መለዋወጫ ጎማ ግን በኛ መወገድ ስለማይችል ለዋናው መስሪያ ቤት እንዲወገድ በደብዳቤ ያሳወቅን መሆኑን እንገልጻለን በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

***<u>የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- የንብረት ከቢሮ አደረጃጀትና ጥበት ጋር ተያይዞ የታየ መሆኑን እና አሁን በአንድ መጋዘን ሥር በየዓይነታቸው እንዲቀመጡ የማድረግ ሥራ የተሰራ መሆኑ፣

- እቃዎች ሲገቡና ሲወጡ በትክክለኛው እየተመዘገቡ የሚገኝ ሲሆን መረጃውም በሶፍት ኮፒ እየተያዘ የትኛው እቃ በማን እጅ እንዳለ የሚታወቅበት ሁኔታ ያለ መሆኑን፣
- ለንብረቶቹ ቁጥር ከመስጠት አኳያ ግን በእቅድ ተይዞና በጀት ተመድቦለት ለሁሉም ንብረቶች ቁጥር ለመስጠት  በሂደት ላይ የሚገኙ መሆኑን፣
- ከንብረት አወጋገድ ጋር በተያየዘ በ2008 በጀት ዓመት ንብረት ሽያጭ አስወጋጅ ኮሚቴ ተቋቋሞ በሁለት መንገድ የተወገደ ሲሆን ሌሎች አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎችና የህትመት ውጤቶች በመኖራቸው በበጀት ዓመቱ ለማስወገድ በዝግጅት ላይ እንገኛለን በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በቅ/ጽ/ቤቱ የንብረቶች ላይ ጥብቅ የሆነ የንብረት ቁጥጥር ያለ መሆኑን እና ዕቃዎች ውጪም ሆነ ገቢ ሲሆኑ የሚመዘገቡ እንዲሁም ቢን ካርድን የመጋዘን ጥበት ስላለባቸው ጥቅም ላይ ማዋል ያልቻሉ መሆኑን እና የተወገዱ ንብረቶች ያሉ ሲሆን ያልተወገዱትን ለወደፊቱ ለማስወገድ ቅርጫፍ ጽ/ቤቱ ከሶስተኛ አካላት ጋር በመነጋገር ጥረት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

***<u>የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

የሚወገዱ ንብረቶች አገልግሎት ከሰጡ በኋላ መወገድ ስላለባቸው የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለን ለወደፊት እንሰራለን በማለት ገልጸዋል፡፡

***የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት***

- የባለቤትነት ማረጋገጫ /ሊብሬ/ የሌላት አንድ ተሽከርካሪ በቀጣይ የሚያጣሩ መሆኑን
- በመንግስት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ያልተያዙ ንብረቶችን በተመለከተ የውስጥ ቁጥጥር ድክመት እንዳለ ለዚህም ወደፊት በተሰጠው ግብዓት መሰረት እንደሰራለን በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

የንብረት አስተዳደሩ የተሟላ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ በተመለከተ በቀጣይ በመገምገም አስፈላጊውን ማሻሻያና ማስተካከያ በመውሰድ የሚስተካከል ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት***

- የባለቤትነት ደብተር ኖሮት ተሽከርካሪው የሌለ በተመለከተ ተሽከርካሪው ኮድ 3 መሆኑ አጠራጣሪ መሆኑን እና የርክክብ ሰነዱን በመፈለግ በቀጣይ የቅ/ጽ/ቤቱ የራሱን ስራ የሚሰራ መሆኑን፣
- የቢሮ ንብረት ማስቀመጫ እጥረት በመኖሩ አላቂ እና ቋሚ ንብረቶች ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑን፣
- በ2010 በጀት ዓመት ውስጥ የተለያዩ መወገድ የሚያስፈልጋቸው የመንግስት ንብረቶች 4 ጊዜ ጨረታ ወቶባቸው የሚጫረት ሰው ያልተገኘላቸው በመሆኑ በማኔጅመንት አይተን ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን
- የሚወገዱና የማይወገዱ ንብረቶች በአንድ ላይ ሊቀመጡ የቻሉት የንብረት ማስቀመጫ እጥረት ስላለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***

በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት አስተያየት መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በ2009 በጀት ዓመት እንዲወራረድ የተደረገ መሆኑን እና በ2010 በጀት ዓመት የሚወገዱ ተለይተው የሚወገዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት***

- ቅ/ፅ/ቤቱ የራሱ ቢሮም ሆነ መጋዘን የሌለውና በወደብና ተርሚናል ፅ/ቤት ባገኘው ቢሮ እና በንብረት ማከማቻነት በውሰት የምንጠቀምባቸው ኮነቴነሮችን እንዳይንቀሳቀሱ ተለይተው በተሰጡን ቦታዎች ላይ የተቀመጡና ‹‹ጉምሩክ የማይነሳ›› ብለን ማስታወቂያ የለጠፍን መሆኑን፣
- የ2009 የንብረት ቆጠራ ከሞ/70.ህ ጋር የማስታረቅ ስራዉን ለመስራት የቆጠራ ኮሚቴው ጊዜ መጣበብ የገጠመው በመሆኑ በቀጣይ የማስታረቁን ስራ እንደሚፈጽሙ፣
- ቅ/ፅ/ቤቱ የራሱ ቢሮም ሆነ ሕንፃ የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ለዕቃ ግምጃ ቤት ተብሎ ተልይቶ የተሰጠው መጋዘን የሌለ ስለሆነ ከደረቅ ወደቡ በትብብር በተሰጡን ኮንቴይነሮች ውስጥ ዕቃዎችን በማስቀመጥ እየተጠቀመምንባቸው የምንገኝ ቢሆንም ደረቅ ወደቡ በራሱ ጊዜ ኮነተይነሮቹን በሚሸጥበት ወቅት ኮነቴይነሮቹን ተመላሽ የምናደርግና ዕቃዎችን ከአንዱ ኮንቴይነር ወደ ሌላ ኮነቴይነር አሽጋሽገን የምንሰራ

ስለሆነ ቅ/ፅ/ቤቱ ካለበት የእቃ ማከመቻ መጋዘን አለመኖር የሚወገዱ ንብረቶች ከማይወገዱ ንብረቶች ጋር በአንድ ስቶር ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

- የሚወገዱ ዕቃዎችን በተመለከተ ዝርዝሩ ተለይቶ ለስራ አስኪያጅ ለውሳኔ የቀረበ ሲሆን በስራ አስኪያጅ በኩል ውሳኔ እንዲያገኝ ሲደረግ ለማስወገድ በዝግጅት ላይ ያለን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት***

- ከዚህ በፊት ለጨረታ ወጥቶ ሊሸጥ ያልቻለውን ንብረት በሁለተኛ ዙር ለመሸጥ ኮሚቴው በድጋሚ ስራውን እንዲጀምር የተደረገ ሲሆን ጎማ ነክ እቃዎችን የግዥ ኤጀንሲ መዝግቦ በመያዝ ለመውሰድ በዝግጅት ላይ መሆኑን፣
- አንድ ተሽከርካሪ የማስወገድ ስራ የዋናዉ መስሪያ ቤት መሆኑ እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን አገልግሎት መስጠት እንደማትችል ገልፀን እንድትወገድ የሊቢሬ ርክክብ በሰነድ ከዋናዉ መስሪያ ቤት ጋር የተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የጅማ ቅ/ጽ/ቤት***

ጋምቤላ በ2010 ንብረቶች መረጃ የሚሟላት ስራ የተጓተተ የነበረ ቢሆንም አሁን ዋጋ ተሰርቶለት ሊወገድ እቅድ የተያዘ ሲሆን የተሽከርካሪ መጠለያ ሼድ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ የግንባታ ጥያቄ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም በዚህኛው በጀት አመት መሬት በማግኘት በጀት የተያዘ በመሆኑ በቀጣይ መፍትሔ የሚያገኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***የቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት***

የሚወገዱ ንብረትን በተመለከተ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሰራ ሲሆን በቀጣይ እርምጃ የሚወስዱ ቢሆንም በአጠቃላይ በቅ/ጽ/ቤቱ አቅም ብቻ ሊወገዱ የማይችሉ ንብረቶች እንዳሉ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል በማለት ገልጸዋል፡፡

***የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት***

የቅ/መ/ቤቱ ህንፃው ሲገነባ ግምጃ ቤት ያልተሰራለት በመሆኑና በዋናው መ/ቤት ለመስራት እንዳልተፈቀደላቸው የጠቀሱ ሲሆን የሚወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ ኮሚቴ ተቋቁሞ በሂደት ላይ እንደሚገኙ እና የንብረቶች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ ቅጥር ባይፈፀምልንም ለስራው ይመጥናሉ ያልናቸውን በውስጥ በማሳደግ ስራውን እየሰራን እነገኛለን በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2) በቅ/ጽ/ቤቶች ውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች እና ተሽከርካሪዎች በተመለከተ

### ግኝት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የውርስ መጋዘኖች እንዲሁም ለፍተሻ በጊዜያዊ ንብረት የማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች፣ የህግ ክርክር ያለባቸው ወደ ውርስ ያልዞሩና የፍተሻ ጊዜያቸውን ያልጨረሱ የቋሚ እና አላቂ ንብረቶች፣ አልባሳት፣ ቅባቶች፣ ምግብ ነክ ሸቀጦች፣ መዳህኒት እና ኬሚካሎት አያያዝ እና አጠባበት ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች፤

- በርካታ የምግብ ዘይቶች ፣አዳዲስ የተለያዩ የአዋቂና የህፃናት አልባሳት፣ ሽቶዎች፣ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች፣ የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ፣ የነዳጅ ታንከሮች ከነ መገጣጠሚያቸው፣ የወርቅ ማዕድን ጠቋሚ ማሽን፣ ስኳር ጤፍ፣ ኦሞዎች፣ የምግብ ዘይቶች፣ አዳዲስ የተለያዩ የአዋቂና የህፃናት አልባሳት፣ ጫማዎች፣ ኤሌክትሮኒክሶች፣ ሽቶዎች ብርድ ልብሶች ሌሎች ዕቃዎች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ እና ያልተወገዱ መሆናቸው፣
- የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ሞተር ሳይክሎች እልባት ያላገኙና የውርስ ውሳኔ ያገኑ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የሚገኙ ከመሆኑም ባሻገር ለተሽከርካሪዎች ማስቀመጫ በቂ መጋዘን ባለመኖሩ ፀሐይና ለዝናብ እንዲሁም አቧራ የሚፈራረቅባቸው እና ለአደጋ ተጋልጠው የሚገኙ መኖሩ፣
- ከግቢው ዉጭ የሚገኘው የጊዚያዊ ዕቃዎች መከማቻ መጋዘን ተገቢ ጥበቃ የሌለው እና በቆርቆሮ የተሰራ የሚገኝ በመኖሩ ለስርቆት የተጋለጠ መሆኑ
- የእንሰሳት መድሃኒት፣አሽሽ እና የተለያየ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ንብረቶች ከሳይወገድ ተከማችቶ የሚገኝ መኖሩ፣
- ተሽከርካሪዎች የግብር ዕዳን ለማስመለስ ሲባል ንብረቶቹ የተያዙና በጨረታ እንዲሸጡ የተባሉ ቢሆንም ለሽያጭ ያልቀረቡ እና እልባት ያላገኙ መሆኑ፣
- ተሽከርካሪዎቹ ከመቼ ጀምረው እንደተያዙ የሚያሳይ ማስረጃ የሌላቸው የሚገኙ ከመሆኑን በተጨማሪ በየቅ/ጽ/ቤቶች በቂ መጋዘን ባለመኖሩ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች ተወርሰው እስካሁን ያልተወገዱ እና መጠለያ ያልተሰራላቸው በመሆኑ ለዝናብ ለአቧራ እና ለፀሐይ ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑ፣

- የተወረሱ ንብረቶች ከቅ/ጽ/ቤቶች የሚወገዱ ንብረቶች ጋር በአንድ ላይ ተከማችተው የተገኙ መኖሩ፣
- በመደበኛ በጀት የገንዘብ ማስቀመጫ ካዝና ውስጥ ውሳኔ ያላገኙ የውጪ ሀገር ገንዘቦች የሚገኝ መሆኑ፣
- የውርስ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑ፣
- የተወረሱ ንብረቶች የማይቆጠሩና ከመዛግብት ጋር የማስታረቅ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣
- ቁርጥራጭ ብረቶች፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ሳይወገዱ ተከማችተው የተገኙ መኖሩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤት በሚባል ደረጃ የሚታይ የንብረት አያያዝ ችግሮች ጎልተው የሚታዩ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

*(ግኝቶቹ በአባሪ 45 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)*

## ስጋት

በውርስ መጋዘን እና በጊዜያዊ ንብረት ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ የሚበላሹ ንብረቶች ላይ አፋጣን የማስወገድ ስራ ካልተሰራ እና ለብልሽት የሚዳረጉ ንብረቶች አጠባበቅ ትኩረት ተሰጥቶት የማይጠበቅ ከሆነ ንብረቶቹ ለብልሽት ለጥፋት ከመዳረጋቸውም በላይ መንግስት ከንብረቶቹ የሚያገኘውን ጥቅም ሊያሳጣው ይችላል፡፡

## የማሻሻያ እርምጃ

በውርስ መጋዘን የሚቀመጡ ንብረቶች ንብረቶቹ በአቀማመጥ ችግር ለብልሽት እንዳይዳረጉ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ ሲሆን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ከፀሐይ ከዝናብ እና ከአቧራ ለመጠበት መጠለያ በመስራት ለጥፋት እና ለብልሽት እንዳይዳረጉ የሚወገዱበትን መንገድ በማመቻቸት አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## የቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ምለሽ

### *የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት*

- 2008 አ.ም ጀምሮ ገቢ ተደርጎ ያልተወገዱ ተሽከርካሪዎች ውሳኔ ያልተሰጠባቸው፣ በንብረት ያኙ ኮሚቴ የተያዘ ተሽከርካሪ ጨረታ ወቶ የማስወገድ ስራ እየተሰራ መሆኑ፣ እግዝቢትንነት የተያዙ ተሽከርካሪዎች ውሳኔ በህግ ማስከበር ምክትል ስራ አስኪያጅ በኩል ውሳኔ እንዲሰጥበት ክትትል እየተደረገ መሆኑ፣

- በኮንሶ እና በሃዋሳ የሚገኙ የተወረሱ ሞተር ሳይክሎች በጨረታ እንዲሸጡ 25 ሞተር ጨረታ የወጣ ሲሆን በኮንሶ የሚገኙ ወደ ሃዋሳ መአከላዊ መጋዘን መቶ እንዲሸጡ አቅጣጫ የተቀመጠ መሆኑ፣
- የተሽከርካሪ መጠለያ እንዲሰራ ቢጠየቅም ምላሽ ባመሰጠቱና በአጠቃላይ የተያዙና የተወረሱ እቃዎችን እንዲወገዱ በተደጋጋሚ ጨረታ በማውጣት እያስወገዱ የሚገኙ ሲሆን የተያዙ ተሽከርካሪዎች ላይ ውሳኔ በጣም የሚዘገይ በመሆኑ ህግ ማስከበር እና ምርመራ ክፍል ውሳኔ ባስቸኳይ እንዲሰጡ የክትትል ስራ በእቅድ ተይዞ የሚሰራ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት</u>***

የውርስ መጋዘን ንብረቶችን በተመለከተ ተሽከርካሪዎች ለባለቤቱ ተመላሽ የተደረጉና የተሸጡም እንዳሉ፣ መጠለያ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች በአሁኑ ሰዓት በባህር ዳር ለትንንሽ ተሽከርካሪዎች መጠለያ የተሰራ መሆኑን፣ የመድሀኒት በተመለከተ ከመድሀኒት አቅርቦትና ቁጥጥር ባለስልጣን ተረጋግጠው መወገድ ያለባቸውን በእነሱ በኩል ያሳወቁ ስለመሆኑና ክትትል እተደረገ ሲሆን እጽን በተመለከተ በህግ ክርክር ላይ በመሆኑ ጉዳዩ ሲያልቅ ተገቢው እርምጃ የሚፈጸም ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

በጉምሩክ ዘዋጅ ቁጥር 859/2006 በተሰጠን ስልጣን መሰረት እቃዎችን እየወረስን ሲሆን የማስወገድ ስራውንም እየሰራን ቢሆንም የተሰጠንን የኦዲት አስተያየት ተቀብለን ስራችንን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

***<u>የሚሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

ያልተወገዱ የተወረሱ እና የተተው የጉምሩክ እቃዎች መኖራቸውን በተመለከተ በአምፖሎቹ ውስጥ ያሉት ኬሚካሎች የአየር ብክለትን የሚያመጣ መሆነን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ጋር በመነጋገር እንዲያስወግድ ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑን እና ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ በህግና መመሪያው መሰረት አብዛኞቻቸው በግብር ይግባኝ ላይ ያሉ መሆናቸው ውሳኔ ሲያገኙ አስፈላጊው እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

***<u>የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>***

- የምግብ ዘይት ለአለ በጅምላ በድርድር ለመሸጥ የተቆጣጣሪ መ/ቤት የጥራት ማረጋገጫ ለማግኘት በሂደት ላይ ያለ፣ አልባሳት ሸቶዎችና ፈርኒቸር የጨረታ ዋጋ ተጠይቆላቸው ጨረታ ለማውጣት በሂደት ላይ ያለ፣ የወርቅ ማዕድን ጠቋሚ ማሽን ሁለት ጊዜ ጨረታ

ወጥቶ ባለመሸጡ ለውሳኔ ለስራ አስኪያጅ የቀረበ መሆኑ፤ የብረት ፌሮዎችና የኤሌክትሪክ ገመድ በድርድር ለመሸጥ አስወጋጅ ኮሚቴ እየተሰራ መሆኑንና አወጋገዱ አስቸጋሪ በመሆኑ (ከጥራት በታች በመሆኑ) የገለጹ ሲሆን፣

- ቆጠራ በ2010 በጀት ዓመት ለማድረግ በእቅድ የተያዘ መሆኑን፣ የኤርትራ ናቅፋ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አልቀበልም በማለቱ በብሔራዊ ባንክ ገቢ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣ ሰራተኛ ለመቅጠር በሰው ሀብት ወይም ለማሳደግ በእቅድ የተያዘ መሆኑን እና በበጀት እጥረት ምክንያት ለተሸከርካሪዎች መጠለያ ለመስራት ባለመቻሉ በቀጣይ ለመስራት በሂደት ላይ የሚገኙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት

- በአሁኑ ሰዓት እየተጠቀምንበት ያለው መጋዘን ንብረትነቱ የሌላ ድርጅት በመሆኑ ለውርስ እቃና ለጉምሩክ ፍታሻ ዕቃ ተለይቶ ባለመሰራቱ በአንድ ላይ መሆኑን እና ቅ/መ/ቤቱ አዲስ መጋዘን ያሰራ በመሆኑ በ2010የሚስተካከል መሆኑን፣
- መኪናዎቹ ሆነ ዕቃዎቹ የህግ ሂደታቸው ሳይጠናቀቅ መሸጥም ሆነ ማስወገድ አይቻልም የይመለሱ ውሳኔ ቢሰጥ ተቋሙን /መንግስትን/ ስለሚጎዳ እና ፍርድ ቤቱ እቃው እንዳይበላሽ ተሸጦ ገንዘቡ በዲፖዚት ይቀመጥ ካለ በዚሁ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን፣
- መድሐኒትን በተመለከተ አስወጋጅ ኮሚቴ ለህብረተሰቡ ጤና ጠንቅ ስለሆነ ጥበቃ የሚደረግበትን ቦታ እያፈላለገ ሲሆን በእኛ በኩል የሚወገዱ እቃዎችን እንዲወገዱ ማስተላለፋቸውን፣
- መኪናዎቹ በዘላቂነት መጠለያ ለመስራት አልተቻለም የተሰራውም በቂ አለመሆኑን እና የሚያዙ መኪናዎች በየጊዜው ስለሚጨምር ይህንንም ጉዳይ የመ/ቤቱ የስራ ሃላፊዎች የሚያውቁት ሲሆን  በእኛ በኩል ሪፖርት ከማድረግ ውጪ መወሰን አንችልም በማለት ገልጸዋል፡፡

## VIII) <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ</u>

### 1) <u>የባለፈው ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች መኖራቸው</u>

**<u>ግኝት</u>**

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 17(3) መሰረት ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በባለፉት በጀት ዓመታት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

**<u>በሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ</u>**

- የእርጅና ቅናሽ በትክክል ባለመሰላቱ እና የመጨረሻ ሚዛን በትክክል ወደ ሚቀጥለው ዓመት ያልተላለፈ እንዲሁም የጥገናና የማሻሻያ የወጪ ስሌታቸው በትክክል ባለመቀመጡ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 479,671.99 መኖሩ፣ **(ግኝቶቹ በአባሪ 46 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)**
- የ2007 እና 2008 ዓመታዊ ንግድ ትርፍ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክሳቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች 20 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ያላሳወቁ መሆኑ፣ **(ግኝቶቹ በአባሪ 47 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)**
- በገቡት የክፍያ ስምምነት መሰረት የተወሰነባቸውን ግብር እና ታክስ ያልከፈሉ ***በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት*** ከ 4 ግብር ከፋዮች ብር 13,157,750.61 መኖሩ፣ (ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF05.16/5 ቀን 28/05/10 ቁጥር 7.1 ላይ ይመልከቱ)
- በንግድ ትርፍ መግለጫ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ መካከል በታየ ልዩነት በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 22,684,650.33 ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣ ***(ግኝቶቹ በአባሪ 48 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***
- ንብረቱ በእግድ ላይ የሚገኝና ግብሩ ያልተሰበሰበ ***ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 1,022,255.63 መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF05.16/5 ቀን 28/05/10 ግኝት ቁጥር 7.1 ላይ ይመልከቱ)***

- በትርፍና ኪሳራ ማሳወቂያው ላይ ከአባሪ/annex 3 እስከ 5 በተቀመጠው መሰረት የወጪ ዝርዝር በሂሳብ መግለጫው ላይ ባለመቅረቡ ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 10,303,603.17 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF05.5/9 ቀን 22/06/10 ግኝት ቁጥር 9.1 ላይ ይመልከቱ)***
- የዓመታዊ ንግድ ትርፍም ሆነ ወርሃዊ ተእታ ሲያሳውቁ የሽያጭ ማጠቃለያ (ዜድ ሪፖርት) ያልቀረበ በ 2 ቅ/ጽ/ቤት 26 ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣

***(ግኝቶቹ በአባሪ 49 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***

- የሽያጭ ገቢን በማሳነስ ***ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 10,916.438,018.16 ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF05.5/9 ቀን 22/06/10 ግኝት ቁጥር 9.1 ላይ ይመልከቱ)***
- ማስረጃ ሳይቀርብለት ተቀናሽ የተደረገ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) ትክክለኛ ስሌት መሰረት በንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያ ላይ ያላሳወቁ በመሆኑ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,995,905.81 ያሳወቁት ሽያጭ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡ ***(ግኝቶቹ በአባሪ 50 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***
- በታክስ ኦዲት ውሳኔ መሰረት ከ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,245,650.64 ያልተሰበሰበ ቀሪ ሂሳብ መኖሩ፣ ***(ግኝቶቹ በአባሪ 51 በተገለጹት የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ ይገኛሉ)***
- ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በተሰጣቸው ቀነ ገደብ እና የግብር ውሳኔ መሰረት ያልከፈሉ ***ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 14,707,028.62 እና ብር 44,975,596.36 በድምር ብር 59,682,624.98 ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8ቀን 13/07/10 ግኝት ቁጥር 7 ላይ ይመልከቱ)***
- የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ዓመታዊ ንግድ ትርፍ ከዜድ ሪፖርት ጋር በታየ ልዩነት ***ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 47,910.35 መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8ቀን 13/07/10 ግኝት ቁጥር 7 ላይ ይመልከቱ)***
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ ግብር ***ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 151,613.99 መኖሩ፡፡ ***(ዝርዝሩ***

***በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8ቀን 13/07/10 ግኝት ቁጥር 7 ላይ ይመልከቱ)***

- ግብር ከፋዮች ያልተሰበሰበ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 259,513.51 መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8 ቀን 13/07/10 ግኝት ቁጥር 7 ላይ ይመልከቱ)***
- የታክስ ማዕከል ያልተቀየረላቸው ***በጅማ ቅ/ጽ/ቤት*** 221 ግብር ከፋዮች መኖሩ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.14/5 ቀን 07/06/10 ግኝት ቁጥር 7.1 ላይ ይመልከቱ)***
- ***ምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት*** በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ መሰረት ያልተሰበሰበ ግብር ብር **31,151,339.07** መኖሩ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ በብልጫ ብር 365,849.22 ተቀናሽ የተደረገ ስለመኖሩ እና የውሳኔ ማስታወቂያ ያልወጣለትና ግብሩም ያልተሰበሰበ ብር 2,121,118.39 መኖሩ በኦዲት ወቅት መታየቱ፣ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.20/8 ቀን 13/07/10 ግኝት ቁጥር 7 ላይ ይመልከቱ)***

በአጠቃላይ በግኝቶቹ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>**የጉምሩክ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ**</u>

<u>***የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት***</u>

- በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ትክክለኛው የትራንስፖርት ማስከፈያ መረጃ ባለመቅረቡ በድህረ ዕቃ ኦዲት ውሳኔ መሰረት ብር 39,430.01 እና ለዋጋ ትመና የተላለፈ ብር 261,700.00 ድምር ብር 301,130.01 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በ2007 በጀት ዓመት በጊዜያዊነት ዋስትና አስይዘው ወደ ሀገር ውስጥ ላስገቡት ኮንቴነሮች በጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው ከሀገር ባለማስወጣታቸው ወደ ቀጥታ ገቢ ያልዞረ የዋስትና ሂሳብ ብር 3,251,500.00 መኖሩ፣
- በ2008 በደንብ መተላለፍ የታየ ብር 4,684,058.75 በዋና መ/ቤት ቅሬታ ላይ የሚገኝ እና ብር 2,804,803.78 መለያ ቁጥሩ ተዘግቷል የተባለ ብር 403,591.24 በድምር ብር 7,892,453.77 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ የሚገኝ መኖሩ፣

- ከ2008 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት መሰረት በዋናው መ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ እና በክርክር ላይ የሚገኙ የ5 ድርጅቶች ብር 45,153,531.80 መኖሩ፣
- በድህረ ዕቃ ኦዲት መሰረት መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ከሁለት ግብር ከፋዮች በድምር ብር 4,171,944.75 ቀሪ ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑ በአጠቃላይ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.1/20 ቀን 10/02/10 ገጽ ቁጥር 9.1 ላይ ይመልከቱ)***

**<u>ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

- ሳይፈቀድ የገባ USED LAUNDARY MACHIN በህግ አግባብ ጉዳዩ ተቋጭቶ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብና ውሳኔ ሳያገኝ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑ
- በተለያየ ምክንያት ያልተሰበሰበ ብር 401,501.71 እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠበት ቀረጥና ታክስ ያለ መሆኑ በአጠቃላይ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.19/8 ቀን 21/05/10 ገጽ ቁጥር 6.1 ላይ ይመልከቱ)***

**<u>የወጪ ሂሳብን በተመለከተ</u>**

**<u>ዋና መ/ቤት</u>**

- አቅራቢው በወቅቱ ባለማቅረቡ ለዘገየበት የተያዘ የቅጣት ሂሳብ ያለአግባብ የተከፈለው ብር 403,137.20 ተመላሽ አለመደረጉ፣
- ከመመሪያው ውጪ የተከፈለ የምሳ አበልን ብር 1,989.50 ተመላሽ አለመደረጉ፣
- መመሪያው ከሚፈቅደው ወጪ ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 60,545.00 እርምጃ አለመወሰዱ፣
- በዱቤ ከተሸጡ የተወረሱ ዕቃዎችን ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 621,050,644.38 መኖሩን፣
- የተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ወይም ጉዳያቸው ያላለቀ 19 ተሽከርካሪዎች መኖራቸን፣
- በስራ ላልተገኙ ሰራተኞች ያለአግባብ ከተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ ያልተደረገ ብር 324.12 መኖሩ፣

- በማነስ ተመዝግቦ የተገኘው እስካሁን የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት በብር 2,080,670.72 መኖሩ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-14310፣ 4-12137፣ 4-15028፣ 4-16059 የሆነ መኪና ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከ6 ወር በጥገና ላይ ያሉ ተብሎ የተገለጸው በአሁን ሰዓት በግቢ ውስጥ ቆሞ የሚገኝ አገልግሎት የማይሰጥ 4-15028 ሲሆን 4-14310 እና 4-16059 የሚወገዱ ተብለው በሰነድ የተያዙ ነገር ግን ያልተወገዱ የሰሌዳ ቁጥር 4-12137 ተሸከርካሪ አሁንም በጥገና ላይ የሚገኝ መሆኑን በአጠቃላይ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ የቆየ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.1/25 ቀን 01/05/10 ግኝት ቁጥር 6.1 እና 6.2 ላይ ይመልከቱ)***

**<u>ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

ከሰራተኞች መቆረጥ የሚገባው የደመወዝ የስራ ግብር ብር 34,109.40 ያልተሰበሰበ ስለመሆኑ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን ተገቢውር እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡ ***(ዝርዝሩ በሥራ አመራር ደብዳቤ ቁጥር OFAGF-05.10/13 ቀን 22/05/10 ግኝት ቁጥር 6 ላይ ይመልከቱ)***

**<u>ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

